በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የገንዘብ ሚኒስቴር
FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
## MINISTER OF FINANCE

ቁጥር / Ref. No. 7/ሬ/1/2/46
ቀን / Date 1/11/2016

ለገቢዎች ሚኒስቴር
ለጉምሩክ ኮሚሽን
<u>አዲስ አበባ</u>

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ 27 ቀን 2016 ዓ.ም ባካሄደው 36ኛ መደበኛ ጉባዔው በተዘጋጀው የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ላይ በስፋት ከተወያየ በኋላ አዋጅ ቁጥር 1341/2016 ሆኖ በሥራ ላይ እንዲውል አፅድቆታል፡፡

ስለዚህ አዋጁ በምክር ቤቱ ከፀደቀበት ጊዜ ጀምሮ በሥራ ላይ እንዲውል እንዲደረግ እያሳሰብን ለአፈፃፀም እንዲያመች በም/ቤቱ የፀደቀውን የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ከዚህ ጋር አባሪ አድርገን መላካችንን እንገልፃለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

እዮብ ተካልኝ (ዶ/ር)
ሚኒስትር ዴኤታ

ግልባጭ፣

ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ (ከአባሪ ጋር)
<u>አዲስ አባባ</u>

ለሕግ ጉዳዮች መምሪያ (ያለ አባሪ)
ለታክስ ፖሊሲ መምሪያ (ያለ አባሪ)
<u>ገንዘብ ሚኒስቴር</u>

Letter/tw

# አዋጅ ቁጥር 1341/2016

## የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ

ቁጠባንና ኢንቨስትመንትን የማበረታታት ሚና ያለው፤ የካፒታል ዕቃዎችን ሳይጨምር በዕቃ እና አገልግሎት ፍጆታ ላይ የተጣለው የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ከወጣ ወዲህ በኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ረገድ የተደረጉ ለውጦችን በተለይም የኤሌክትሮኒክስ ግብይትን እና በዓለም አቀፍ ደረጃም ተቀባይነት ያገኙ አዳዲስ እሳቤዎችን በአገራችን የሕግ ማዕቀፍ ውስጥ በማካተት ታክሱ ለኢኮኖሚው ዕድገት የሚፈለገውን እገዛ እንዲያደርግ ማስቻል ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፤

መሰረታዊ የሆኑ የተጨማሪ እሴት ታክስ ድንጋጌዎችን በአዋጁ ውስጥ በማካተት እና ዝርዝር ድንጋጌዎችን ለደንብና መመሪያ በመተው አዋጁ በቀላሉ ለመረዳት የሚያስችል አወቃቀር እንዲኖረው እንዲሁም ለአፈፃፀም ግልፅ እና ምቹ እንዲሆን ማድረግ በሚያስችል አኳኋን መቅረፅ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ከታክሱ ነፃ የመሆን መብት አተገባበር የመብቱ ተጠቃሚ እንዲሆን የታሰበውን የህብረተሰብ ክፍል ማእከል ያደረገ እና በግብአት ታክስና በውጤት ታክስ መካከል ያለውን ሰንሰለት የጠበቀ እንዲሆን በማድረግ ፍትሐዊነትንና የዜጎችንም ሆነ የንግድ ማኅበረሰቡን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ በማስፈለጉ፣

በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 99 መሠረት ሚያዝያ 3 ቀን 1994 ዓ.ም በተካሄደው የፌዴሬሽን እና የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤቶች 2ኛ ዓመት የሥራ ዘመን 2ኛ የጋራ ስብሰባ እና በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 55(1) መሠረት በተሰጠ ሥልጣን የሚከተለው ታውጇል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 1341/2016 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ ወይም የሐረጉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፤ በዚህ አዋጅ ውስጥ፤

1/ **"የሒሣብ ጊዜ"** ማለት በቀን መቁጠሪያ ሰነድ የተመለከተው እያንዳንዱ ወር ነው። የነሐሴ እና የጳጉሜ ወራቶች በአንድነት ተጠቃለው እንደ አንድ ወር ይቆጠራሉ።

2/ **"ማስተካከያ የሚደረግበት ሁኔታ"** ማለት አንድን አቅርቦት በሚመለከት፦

ሀ) አቅርቦቱ ሲሠረዝ፣

Ministry of Finance ARCHIVE 2

ለ) የአቅርቦቱ ሁኔታ መሠረታዊ ነው ሊባል በሚችል ደረጃ ሲቀየር ወይም ሲለወጥ፣

ሐ) የዋጋ ቅናሽ በመደረጉ ወይም በሌላ ማናቸውም ምክንያት ለአቅርቦቱ የሚፈፀመው ክፍያ ሲለወጥ፣ ወይም

መ) ለአቅራቢው የተፈጸመውን የዕቃ አቅርቦት በሚመለከት፤ የተሸጠው ዕቃ ወይም የዕቃው ከፊል ለአቅራቢው ሲመለስ፣ ነው።

3/ "**አስተዳደራዊ መቀጫ**" ማለት በፌዴራል የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 ክፍል አሥራ አምስት ምዕራፍ ሁለት የተጣለው አስተዳደራዊ መቀጫ ነው።

4/ "**ወኪል**" ማለት አንድን ሰው በሚመለከት በዚህ ሰው ስም እና ትዕዛዝ የሚሠራ ማናቸውም ሰው ነው።

5/ "**የካፒታል ዕቃ**" ማለት ማናቸውም ሰው ለሚያከናውነው ታክስ የሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ጥቅም ላይ የሚውል፣ ከአንድ ዓመት ላላነሰ ጊዜ ኤኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያለው እና ዕቃዎችን ለማምረት ወይም አገልግሎቶችን ለመስጠት የዋለ ዕቃ ሲሆን፣ የንግድ ዕቃዎችን አይጨምርም።

6/ "**ኮሚሽን**" ማለት የአስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር በመወሰኛ አዋጅ ቁጥር 1263/2014 የተቋቋመው የጉምሩክ ኮሚሽን ነው።

7/ "**የግብይት ዋጋ**" ማለት ለዕቃና ለአገልግሎት የሚከፈለው ጠቅላላ ገንዘብ ሲሆን በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5 የተተረጎመውን ያካትታል።

8/ "**የክሬዲት ሰነድ**" ማለት የተመዘገበ ሰው በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፫ በተጣለበት ግዴታ መሠረት የሚሰጠው ሰነድ ነው።

9/ "**ተቀናሽ የሚሆን ግዥ**" ማለት የተመዘገበን ሰው በሚመለከት፣

ሀ) በሌላ የተመዘገበ ሰው ለዚህ ሰው የተፈፀመ ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት፣

ለ) በቀጥታ በገዢው ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት፤ ወይም

ሐ) ይህ ሰው ወደ አገር ያስገባው ዕቃ ነው።

10/ "**የጉምሩክ ሕግ**" ማለት

ሀ) የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 (እንደተሻሻለ)፣ እና

ለ) በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 (እንደተሻሻለ) መሠረት የወጣ ማንኛውም ደንብ ወይም መመሪያ፣ ነው።

11/ **"የዴቢት ሰነድ"** ማለት የተመዘገበ ሰው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 53 በተጣለበት ግዴታ መሠረት የሚሰጠው ሰነድ ነው፡፡

12/ **"ቀረጥ"** ማለት በጉምሩክ ሕግ እና የአለም አቀፍ የተዋሃደ የሸቀጦች አሰያየምና አመዳደብ ሥርዓትን ተከትሎ በወጣው የጉምሩክ የታሪፍ ደንብ መሠረት በገቢና ወጪ ዕቃዎች ላይ የሚጣልና የሚሰበሰብ ክፍያ ነው፡፡

13/ **"የኤሌክትሮኒክ የማከፋፈያ ገበያ"** ማለት አቅራቢው በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ከሩቅ የሚሰጥ አገልግሎትን ወይም በኤሌክትሮኒክ ዘዴ የሚታዘዝን ዕቃ በማከፋፈያ መንገዱ አንቀሳቃሽ አማካኝነት ለሦስተኛ ወገን (ለተቀባዩ) የሚያቀርብበት ድረ-ገጽ፤ የኢንተርኔት ፖርታል፤ ጌትዌይ፤ በኤሌክትሮኒክ መንገድ ግብይት የሚፈፀምበት መደብር፤ የገበያ ቦታ፤ የማከፋፈያ መድረክ ወይም ሌላ ተመሳሳይ መንገድ ነው፡፡

14/ **"በኤሌክትሮኒክ ዘዴ የሚታዘዝ ዕቃ"** ማለት በኤሌክትሮኒክ የመገናኛ ዘዴ የግዢ ትእዛዝ የተሰጠበት ዕቃ ነው፡፡

15/ **"ተቀጣሪ"** ማለት ራሱን ችሎ የሚሰራን የስራ ተቋራጭ ሳይጨምር በሌላ ሰው መሪነትና ቁጥጥር ሥር ሆኖ አገልግሎት ለመስጠት በቋሚነት ወይም በጊዜያዊነት የተቀጠረ ሰው ሲሆን የድርጅት ዳይሬክተርን ወይም በድርጅቱ አመራር ውስጥ ኃላፊነት የተሰጠውን ሌላ ሰው እንዲሁም ተሿሚንና የሕዝብ ተመራጭን ጨምሮ የመንግሥት የሥራ ኃላፊን ያጠቃልላል፡፡

16/ **"ቀጣሪ"** ማለት ተቀጣሪን የቀጠረ ወይም ለተቀጣሪው ደመወዝ የሚከፍል ሰው ነው፡ :

17/ **"ከታክሱ ነፃ የሆነ ወደአገር የሚገባ ዕቃ"** ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 11 በተደነገገው መሠረት ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነፃ የተደረገና ከዚህ አዋጅ ጋር በተያያዘው አባሪ 3 የተመለከተው ወደአገር የሚገባ ዕቃ ነው፡፡

18/ **"ከታክስ ነፃ የተደረገ አቅርቦት"** ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 10 በተደነገገው መሠረት ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነፃ የተደረገና ከዚህ አዋጅ ጋር በተያያዘው አባሪ 2 የተመለከተው አቅርቦት ነው፡፡

19/ **"የፋይናንስ ኪራይ"** ማለት አከራዩ

ሀ) ቀደም ሲል ይዞት የሚገኘውን የካፒታል ዕቃ ወይም

ለ) በተከራዩ መራጭነት አቅራቢ ተብሎ ከሚጠራው ሦስተኛ ወገን የሚገዛውን የካፒታል ዕቃ፤ ተከራዩ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ተከፍሎ የሚያልቅ በሁለቱ ወገኖች ስምምነት የተወሰነ ክፍያ በየተወሰነ ጊዜ በመፈፀም እንዲጠቀምበት የሚያከራይበት፤ የኪራይ ስምምነቱ ጸንቶ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ አከራዩ በካፒታል ዕቃው ላይ ሙሉ የባለቤትነት መብት ይዞ የሚቆይበትና የኪራይ

ዘመኑ ሲያበቃ ሁለቱም ወገኖች ከተስማሙ ተከራዩ የካፒታል ዕቃውን ሊገዛ የሚችልበት የኪራይ አይነት ነው፡፡

20/ "**ዕቃ**" ማለት ግዙፋዊ ህልዎት ያለው ማናቸውም የሚንቀሳቀስ ወይም የማይንቀሳቀስ ንብረት ሲሆን፣ የሚከተሉትን አይጨምርም፣

ሀ) ገንዘብን፣ ወይም

ለ) በገመድ፣ በኬብል፣ በሬዲዮ፣ በብርሃን ወይም በሌላ ማናቸውም የኤሌክትሮማግኔቲክ ዘዴ ወይም በተመሳሳይ ሌላ የቴክኒክ ዘዴ የሚተላለፍን ምርት፡፡

21/ "**የመንግሥት ተቋም**" ማለት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በፌዴራል ወይም በክልል መንግሥት ወይም በከተማ አስተዳደር በጀት የሚተዳደር የመንግስት መስሪያ ቤት ነው፡፡

22/ "**የዱቤ ግዢ ስምምነት**" ማለት አከራይና ተከራይ ባደረጉት ስምምነት መሰረት አከራይ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ የሚደረግ ክፍያ እየተከፈለው አንድ የተወሰነ የካፒታል ዕቃን ተከራዩ እንዲጠቀምበት የሚፈቅድበት፣ እያንዳንዱ የኪራይ ክፍያ በተደረገ ቁጥር ለክፍያው ተመጣጣኝ በሆነ መቶኛ ልክ ለተከራዩ የባለቤትነት መብት የሚተላለፍበትና ተከራዩ የመጨረሻውን ክፍያ እንደፈፀመም በካፒታል ዕቃው ላይ ሙሉ የባለቤትነት መብት ወዲያውኑ የሚያገኝበት የኪራይ አይነት ነው፡፡

23/ "**ወደ አገር ማስገባት**" ማለት ማናቸውንም ገቢ ዕቃ ወደ ጉምሩክ ክልል ማምጣት ወይም እንዲገባ ማድረግ ነው፡፡

24/ " **አስመጪ**" ማለት እቃን ወደአገር ከማስገባት ጋር በተያያዘ፤የእቃው ባለቤት የሆነ ሰው ወይም እቃው ወደአገር በሚገባበት ጊዜ በይዞታው ስር ያለ በእቃው ላይ ጥቅም ያለው ማናቸውም ሰው ነው፡፡

25/ "**የአገር ውስጥ ጥቅል የቱሪዝም አገልግሎት**" ማለት በኢትዮጵያ ውስጥ የሚሰጥን የመኝታ፤ የምግብ፤ የትራንስፖርት፣ የጉብኝት ወይም ሌሎች የቱሪስት አገልግሎቶችን የሚጨምር አገልግሎት ነው፡፡

26/ "**የግብዓት ታክስ**" ማለት ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገበን ሰው በሚመለከት፡-

ሀ) ተቀናሽ የሚሆን ግዢ ላይ ሊከፈል የሚገባውን ማንኛውንም አስተዳደራዊ ቅጣት እና ወለድ ሳይጨምር ይህ ሰው ተቀናሽ የሚሆን ግዢ በሚፈጽምበት ጊዜ የከፈለው የተጨማሪ እሴት ታክስ፤ እና

ለ) ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም የተመዘገበው ሰው የግብዓት ታክስ ሆኖ እንዲቆጠር የተወሰነ የገንዘብ መጠን ነው፡፡

27/ "**የግብአት ታክስ ተቀናሽ**" ማለት በግብአት ላይ የተከፈለና በዚህ አዋጅ ተቀናሽ እንዲሆን የተፈቀደ ታክስ ነው፡፡

28/ "**ከፍተኛ ግብይት ያለው ያልተመዘገበ ሰው**" ማለት፡

ሀ) ጠቅላላ ዓመታዊ የአቅርቦት መጠኑ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ 2 ከተመለከተው የገንዘብ መጠን በላይ የሆነ፤እና

ለ) ለታክሱ ያልተመዘገበ ሰው ወይም የመንግስት ተቋም ነው፡፡

29/ "**ገንዘብ**" ማለት፡-

ሀ) በገንዘብ ቅርስ ሰብሳቢነት የተሰማሩ ከሚይዙት፣ በኢንቬስትመንት መልክ ከሚያዝ ወይም ሌሎች ስለገንዘብ የመመራመር ፍላጐት ባላቸው ከሚያዘው ውጪ ያለ በኢትዮጵያ ውስጥ ወይም በሌላ አገር ሕጋዊ መገበያያ የሆነ ሣንቲም ወይም ወረቀት፣

ለ) የሀዋላ ወረቀት፣ የባንክ ድራፍት፣ የቃል ኪዳን ሰነድ፣ የፖስታ ቤት ሀዋላ ወይም የገንዘብ ክፍያ ማዘዣ፣

ሐ) የገንዘብ ዋጋ ያለው እና መንግሥት ለሽያጭ የሚያቀርበው ወይም የሚያወጣው እና በሕግ መሠረት የተጣሉ ክፍያዎችን ለመሰብሰብ የሚያገለግል ቴምብር፣ ቅጽ ወይም ካርድ፣ወይም

መ) ክፍያን ለመፈፀም እንዲያገለግል የተሰጠ ማናቸውም፣

(i) ክሬዲት ካርድ ወይም ዴቢት ካርድ፣ ወይም

(ii) ማናቸውም ሰው በሚያንቀሳቅሰው የባንክ ሒሣብ ገቢ ወይም ወጪ በማድረግ የተከፈለ ክፍያ፡፡

30/ "**የውጤት ታክስ**" ማለት የተመዘገበን ሰው በሚመለከት፣

ሀ) የተመዘገበ ሰው ከሚያከናውነው ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ሊሰበስብ የሚችለው የተጨማሪ እሴት ታክስ፣ እና

ለ) የተመዘገበ ሰው ላገኘው በቀጥታ በገዢው ታክስ ለሚከፈልበት አቅርቦት ሊከፍል የሚገባው የተጨማሪ እሴት ታክስ፣ ወይም

ሐ) ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም የተመዘገበው ሰው የውጤት ታክስ ሆኖ እንዲቆጠር የተወሰነ የገንዘብ መጠን ነው፡፡

31/ "**አስቀድሞ ክፍያ የተፈፀመበት የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት**" ማለት የስልክ ካርድ፣ የቅድሚያ ክፍያ ካርድ፣ ሒሣብ የመሙያ ካርድ ወይም ማናቸውም ሌላ አስቀድሞ ክፍያ የተፈፀመበት የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሲሆን፣ በኤሌክትሮኒክ መንገድ የሚፈፀመውንም ይጨምራል፡፡

32/ "**ተቀባይ**" ማለት አቅርቦትን በሚመለከት አቅርቦቱ የተፈፀመለት ሰው ነው፡፡

33/ "**የተመዘገበ ሰው**" ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገበ ወይም የመመዝገብ ግዴታ ያለበት ሰው ነው፡፡

34/ "**የምዝገባ የገንዘብ መጠን**" በዚህ በአዋጅ አንቀጽ 12(2) የተመለከተው የምዝገባ የገንዘብ መጠን ነው፡፡

35/ "**ከሩቅ የሚሰጥ አገልግሎት**" ማለት ከኢትዮጵያ ውጪ በሚገኝ የንግድ ስራ ቦታ ባለ አቅራቢ በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚገኝ ተቀባይ የተሰጠ አገልግሎት ነው፡፡

36/ "**በቀጥታ በገዢው ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት**" ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 በተደነገገው መሠረት የአቅርቦቱ ተጠቃሚ ራሱ በቀጥታ ታክሱን የሚከፍልበት አቅርቦት ነው፡፡

37/ "**አገልግሎት**" ማለት ከዕቃ ወይም ከገንዘብ ውጪ የሆነ ማናቸውም ነገር ነው፡፡

38/ "**አቅራቢ**" ማለት አቅርቦትን በሚመለከት አቅርቦቱን የሚያከናውነው ሰው ነው፡፡

39/ "**አቅርቦት**" ማለት የዕቃ አቅርቦት፣ የአገልግሎት አቅርቦት ወይም በቀጥታ በገዥው ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ነው፡፡

40/ "**የዕቃ አቅርቦት**" ማለት፣

ሀ) የዕቃ ሽያጭ፣ ልውውጥ ወይም የዕቃ ባለቤት የሆነ ሰው ዕቃውን በማስተላለፍ ረገድ ያለውን መብት በመጠቀም የሚያከናውነው ሌላ የማስተላለፍ ተግባር፣ ወይም

ለ) በዱቤ ግዥ ስምምነት ወይም በፋይናንስ ኪራይ ስምምነት አማካኝነት ዕቃዎችን በዱቤ የመግዛት ወይም የመከራየት ተግባር፡፡

41/ "**የአገልግሎት አቅርቦት**" ማለት ከዕቃ ወይም ከገንዘብ አቅርቦት ውጪ ያለ ሌላ ማናቸውም ተግባር ሲሆን፣ የሚከተሉትን ይጨምራል፡

ሀ) ማናቸውንም መብት መስጠት፣ ማስተላለፍ፣ ማቋረጥ ወይም መብት መጠቀምን መተው፣

ለ) የመገልገያ ቦታን ወይም ጥቅምን ለሌላ ማመቻቸት፣

ሐ) ማናቸውንም ሁኔታ መፍቀድ ወይም አንድን ድርጊት ከመፈፀም መታቀብ፣

መ) ከሙቀት ወይም ከኤሌክትሪክ የሚመነጭን ኃይል፣ ጋዝ ወይም ውሃ ማስተላለፍ ወይም ማቅረብ፣ ወይም

ሠ) አንድን ምርት በገመድ፣ በኬብል፣ በሬዲዮ፣ በብርሃን ወይም በሌላ የኤሌክትሮማግኔቲክ ዘዴ ወይም በተመሳሳይ የቴክኒክ ዘዴ ማስተላለፍ፡፡

42/ "**የታክስ ባለሥልጣን**" ማለት የአስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 1263/2014 የተቋቋመው የገቢዎች ሚኒስቴር ወይም በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 መሠረት የተጨማሪ እሴት ታክስን ለማስተዳደር በገቢዎች ሚኒስቴር ውክልና የተሰጠው የክልል መንግሥት ወይም የከተማ አስተዳደር ግብር ሰብሳቢ አካል ነው፡፡

43/ "**የታክስ ክፍልፋይ**" ማለት ከዚህ በታች በተመለከተው ቀመር የሚከናወን የክፍልፋይ ስሌት ነው፡፡

$$ሀ/(100 + ሀ)$$

ለዚህ ስሌት አፈፃፀም "ሀ" ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 8(2) (ለ) መሠረት ተፈፃሚ የሚሆነው የተጨማሪ እሴት ታክስ መጣኔ ነው፡፡

44/ "**የታክስ ደረሰኝ**" ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 52 በተጣለበት ግዴታ መሠረት የተመዘገበ ሰው የሚሰጠው ሰነድ ነው፡፡

45/ "**ታክስ የሚከፈልበት እንቅስቃሴ**" የሚለው ሐረግ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 7 የተሰጠውን ትርጉም ይይዛል፡፡

46/ "**ታክስ የሚከፈልበት ወደአገር የሚገባ ዕቃ**" ማለት

ሀ) ከታክሱ ነፃ ከሆነ፤ ወይም

ለ) የኤሌክትሮኒክ ገበያ አቅራቢ ወይም የኤሌክትሮኒክ የማከፋፈያ ገበያ ስራን የሚያከናውን የተመዘገበ ሰው ዕቃው ወደአገር ከመግባቱ በፊት ከተጠቃሚው የተጨማሪ እሴት ታክስ ከሰበሰበበት በኤሌክትሮኒክ ዘዴ የታዘዘ ዕቃ፤ ውጪ ያለ ዕቃ ነው፡፡

47/ **"ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት"** ማለት

ሀ) ከታክስ ነፃ ከተደረገ አቅርቦት ውጪ ታክስ የሚከፈልበትን የሥራ እንቅስቃሴ በማከናወን ሂደት በኢትዮጵያ ውስጥ የተመረተ ዕቃ ወይም አገልግሎት አቅርቦት፣ ወይም

ለ) በዚህ አዋጅ ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት እንደሆነ የሚቆጠር አቅርቦት፣ ነው።

48/ **"የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት"** ማለት መልዕክት፣ጽሁፍ፤ ስዕል፣ ድምፅ ወይም ማናቸውንም ሌላ መረጃ በገመድ፣ በሬዲዮ፣ በብርሃን፣ በኬብል ወይም በሌላ የኤሌክትሮማግኔቲክ ዘዴ ወይም በተመሳሳይ የቴክኒክ ዘዴ ማስተላለፍ፣ ማሠራጨት ወይም መቀበል ሲሆን፣

ሀ) የማስተላለፍ፣ የማሠራጨት ወይም የመቀበል አቅምን የመጠቀም መብትን የማዘዋወር ወይም የማስተላለፍ፣ ወይም

ለ) ከዓለም ዐቀፍ ወይም ከአገር አቀፍ የመረጃ መረብ ጋር የማገናኘት አገልግሎትን፣ ይጨምራል።

ሆኖም የጽሑፍ፣ የስዕል፣ የድምፅ ወይም የመረጃ አቅርቦትን አይጨምርም።

49/ **"የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት አቅራቢ"** ማለት በኢትዮጵያ ወይም በሌላ አገር የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ለመስጠት ፈቃድ የተሰጠው ሰው ነው።

50/ **"የንግድ ዕቃ "** ፦

ሀ) ማንኛውም የተመረተ፣ የተፈበረከ፣ የተገዛ ወይም ለማምረት፣ ለመሸጥ ወይም ለመለወጥ በማናቸውም ሁኔታ የተገኘን ዕቃ፣

ለ) በማምረት ወይም በመፈብረክ ሂደት ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውል ማንኛውም ጥሬ ዕቃ ወይም አላቂ ዕቃ፣ ወይም

ሐ) ለጭነት ወይም ለሥራ የሚያገለግሉ እንስሳትን ሳይጨምር ማንኛውንም እንስሳ፣ ይጨምራል።

51/ **"የተጨማሪ እሴት ታክስ"** ማለት በዚህ አዋጅ የተጣለው የተጨማሪ እሴት ታክስ ነው፡ ፡

52/ **"ቫውቸር"** ማለት በአምጪው ለእቃ ወይም ለአገልግሎት አቅርቦት ክፍያ ለመፈጸም ብቻ ሊውል የሚችል ቫውቸር፤ ቴምብር፤ ምትክ ሰነድ፣ ኩፓን ወይም ሌላ ተመሳሳይ ነገር ሲሆን፤በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ የሚሰጡትን እና የቴሌኮሚኒኬሽን የቅድሚያ ክፍያ ካርድን ይጨምራል፤ ሆኖም የፖስታ ቴምብርን አይጨምርም።

53/ "**የዜሮ መጣኔ አቅርቦት**" በዚህ አዋጅ አንቀጽ 9 በተደነገገው መሠረት ዜሮ መጣኔ ተፈፃሚ እንዲሆንበት የተደረገ ከዚህ አዋጅ ጋር በተያያዘው አባሪ 1 የተመለከተ አቅርቦት ነው፡፡

54/ በዚህ አዋጅ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ እና ትርጉም ያልተሰጣቸው ቃላትና ሐረጐች በታክስ አስተዳደር አዋጅ ትርጉም የተሰጣቸው ከሆነ በታክስ አስተዳደር አዋጁ የተሰጣቸው ትርጉም ይኖራቸዋል፡፡

55/ በወንድ ፆታ የተገለፀ ማናቸውም ድንጋጌ የሴት ጾታንም ይጨምራል፡፡

56/ ሰው ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡ ፡

## 3. የተፈፃሚነት ወሰን

በዚህ አዋጅ የተጣለው የተጨማሪ እሴት ታክስ በኢትዮጵያ የግዛት ክልል ውስጥ በሚከናወን ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት፤ ታክስ የሚከፈልበት ወደአገር የሚገባ ዕቃ እንዲሁም በቀጥታ በገዢው ታክስ በሚከፈልበት ኢትዮጵያ ውስጥ ቋሚ የስራ ቦታ በሌለው ሰው ከውጭ አገር ሆኖ ኢትዮጵያ ውስጥ ላለ ሰው በሚከናወን ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## 4. ታክሱን የመሰብሰብ ስልጣን

በዚህ አዋጅ የተጣለው የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚወሰነው እና የሚሰበሰበው እንደአግባብነቱ በገቢዎች ሚኒስቴር ወይም በጉምሩክ ኮሚሽን ይሆናል፡፡ ሆኖም የገቢዎች ሚኒስቴር ስለእርሱ ሆነው የተጨማሪ እሴት ታክስን እንዲወስኑ እና እንዲሰበስቡ ለክልል እና ለከተማ አስተዳደር የገቢዎች ቢሮዎች ውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

## 5. የግብይት ዋጋ

1/ በዚህ አንቀጽ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የአንድ አቅርቦት የግብይት ዋጋ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ጠቅላላ ድምር ይሆናል፡፡

ሀ) ማናቸውም ሰው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ለአቅርቦቱ የከፈለው ወይም የሚከፍለው የገንዘብ መጠን፣

ለ) ማናቸውም ሰው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ለአቅርቦቱ በዓይነት የከፈለው ወይም የሚከፍለው ትክክለኛ የገበያ ዋጋ፣

ሐ) የዕቃ አቅርቦትን በሚመለከት የዕቃው አቅርቦት ለተፈጸመበት የእቃ መያዣ የተከፈለውን ወይም የሚከፈለውን እና የዕቃው መያዣ ሲመለስ ተመላሽ የሚደረገውን ተቀማጭ ገንዘብ፤

መ) ለአቅርቦቱ የተከፈለው ወይም የሚከፈለው የአገልግሎት ክፍያ፣ እና

ሠ) በአቅርቦቱ ምክንያት የተከፈለው ወይም የሚከፈለው ማናቸውም ቀረጥ፣ የኤክሳይዝ ታክስ፣ ሱር ታክስ፣ የአገልግሎት ክፍያ እና ሌሎች ክፍያዎች፣

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው የአቅርቦቱ የግብይት ዋጋ በአቅርቦቱ ላይ የተከፈለውን ወይም ሊከፈል የሚገባውን የተጨማሪ እሴት ታክስ አይጨምርም፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ከተመለከተው የአቅርቦቱ የግብይት ዋጋ ላይ አቅርቦቱ በተከናወነ ጊዜ የተፈቀደው የዋጋ ቅናሽ ወይም ተመላሽ ተቀናሽ መደረግ አለበት፡፡

4/ አቅርቦቱ ከተከናወነ በኋላ ከአቅርቦቱ ዋጋ ላይ የተፈቀደው ተቀናሽ፣ ተመላሽ ወይም ሌላ ማስተካከያ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 43 እና 44 በተመለከተው የማስተካከያ ድንጋጌ መሠረት ሊሰላ ይገባል፡፡

5/ አቅራቢው የተቀማጩን ገንዘብ ለአቅርቦቱ ክፍያ እንዲውል ካላደረገ በስተቀር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)(ሐ) የተመለከተውን የተቀማጭ ገንዘብ ሳይጨምር የአቅርቦት የግብይት ዋጋ በተቀማጭ ገንዘብነት የተከፈለውን ወይም የሚከፈለውን የገንዘብ መጠን አይጨምርም፡፡

6/ ከአቅርቦት ጋር በተያያዘ የተከፈለ ወይም ሊከፈል የሚገባ መያዣ ለአቅራቢው ቀሪ እንዲሆን ከተደረገ የአዋጁ አንቀጽ 35 ድንጋጌ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

7/ የአዋጁ አንቀጽ 20(7) ተፈፃሚ የሚሆንበትን የዱቤ ግዢ ስምምነት ወይም የፋይናንስ ሊዝ በሚመለከት የዕቃው አቅርቦት ዋጋ በስምምነቱ ወይም በኪራዩ ውል መሠረት የሚከፈለውን የፋይናንስ አገልግሎት ክፍያ አይጨምርም፡፡

8/ ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም፡-

ሀ) **"የኤክሳይዝ ታክስ"** ማለት በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 1186/2012፣ እና በማሻሻያው የተጣለው የኤክሳይዝ ታክስ ነው፡፡

ለ) **"ሱር ታክስ"** ማለት ወደአገር በሚገቡ ዕቃዎች ላይ ሱር ታክስ ለማስከፈል በወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 133/1999 የተጣለ ሱር ታክስ ነው፡፡

6. <u>በቀጥታ በገዢው ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት</u>

1/ በቀጥታ በገዢው ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት የሚባለው የሚከተለው የአገልግሎት አቅርቦት ነው፡፡

ሀ) የተመዘገበ ሰው ቢሆንም ባይሆንም፤ አቅርቦቱ የተከናወነው ከኢትዮጵያ ውጪ ባለ፤ በኢትዮጵያ ውስጥ በቋሚነት በሚሠራ ድርጅት አማካኝነት ታክስ የሚከፈልበትን የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ በማያከናውን ሰው አማካኝነት ከሆነ፣

ለ) አቅርቦቱ የተሰጠው ለተመዘገበ ሰው፤ ለመንግስት ተቋም ወይም ከፍተኛ ግብይት ላለው ያልተመዘገበ ሰው ከሆነ፣ እና

ሐ) አቅርቦቱ በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኝ የንግድ ሥራ ቦታ ቢሰጥ ኖሮ ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት የሆነ እንደሆነ ነው፡፡

2/ የተመዘገበ ወይም ከፍተኛ ግብይት ያለው ያልተመዘገበ ሰው በኢትዮጵያ ውስጥ እና ከኢትዮጵያ ውጪ ታክስ የሚከፈልበት የሥራ እንቅስቃሴ የሚያከናውን ሆኖ፤ ከኢትዮጵያ ውጪ የሚያከናውነው የስራ እንቅስቃሴ (ከዚህ በኋላ "የውጭ አገር የስራ ክፍል" ተብሎ የሚጠራው) ኢትዮጵያ ውስጥ ላለው የስራ እንቅስቃሴ (ከዚህ በኋላ "ኢትዮጵያ የሚገኝ የስራ ክፍል" ተብሎ ለሚጠራው) የውስጥ አገልግሎት የሚሰጥ ከሆነ፤ የተሰጠው የውስጥ አገልግሎት ከታክሱ ነፃ የተደረገ ካልሆነ በስተቀር በቀጥታ በገዢው ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ይሆናል፡፡

3/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ተግባራዊ በሚሆንበት ጊዜ ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም በውጭ አገር የስራ ክፍል እና በኢትዮጵያ የስራ ክፍል መካከል የተደረገው አቅርቦት በሁለት ግንኙነት ባላቸው ሰዎች መካከል የተከናወነ ግብይት ሆኖ ይቆጠራል፡፡

## 7. <u>ታክስ የሚከፈልበት እንቅስቃሴ</u>

1/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም ማናቸውም በተከታታይነት ወይም በመደበኛነት እና በሙሉ ወይም በከፊል የግብይት ዋጋን በማስከፈል አንድ ሰው ለሌላ ሰው የሚያቀርበው ወይም ለማቅረብ የሚፈልገው ዕቃ ወይም አገልግሎት ታክስ የሚከፈልበት እንቅስቃሴ ይሆናል፡፡

2/ ማናቸውም ሰው ታክስ የሚከፈልበትን እንቅስቃሴ በማስጀመር፣ በማቋረጥ ወይም መልሶ በማደራጀት ረገድ የሚያከናውነው ማናቸውም ሥራ ታክስ የሚከፈልበትን የሥራ እንቅስቃሴ በማከናወን ሂደት የተከናወነ እንደሆነ ይቆጠራል፡፡

3/ የሚከተሉት ታክስ የሚከፈልበት የሥራ እንቅስቃሴ ሆነው አይቆጠሩም፡፡

ሀ) ተቀጣሪ የሚያከናውነው ሥራ

ለ) ማናቸውም ግለሰብ ለትርፍ ጊዜ ማሳለፊያ ወይም ለመዝናናት የሚያከናውነው እንቅስቃሴ፣ ወይም

ሐ) ከግለሰብ ውጪ ማናቸውም ሌላ ሰው ለማህበርተኞቹ ወይም ለባለቤቶቹ ወይም ግንኙነት ላላቸው ሰዎች ጥቅም የሚያከናውነው የትርፍ ጊዜ ማሳለፊያ ወይም የመዝናኛ እንቅስቃሴ።

## ክፍል ሁለት

## ታክስ ስለመጣል እና ከታክስ ነፃ ስለማድረግ

### 8. የተጨማሪ እሴት ታክስ ስለመጣል

1/ ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ላይ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) በተመለከተው የማስከፈያ መጣኔ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተጥሏል።

ሀ) በተመዘገበ ሰው የሚከናወን ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት፤

ለ) ማናቸውም ሰው ወደአገር በሚያስገባው ዕቃ፤ እና

ሐ) ለተመዘገበ ሰው፣ ለመንግሥት ተቋም ወይም ከፍተኛ ግብይት ላለው ያልተመዘገበ ሰው የሚቀርብ በቀጥታ በገዢው ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት።

2/ የተጨማሪ እሴት ታክስ የማስከፈያ መጣኔ የሚከተለው ይሆናል፣

ሀ) የዜሮ የማስከፈያ መጣኔ ተፈፃሚ በሚደረግባቸው አቅርቦቶች ላይ፣ ዜሮ በመቶ፣ ወይም

ለ) በሌሎች ማናቸውም አቅርቦቶች 15 በመቶ።

3/ ታክስ በሚከፈልበት አቅርቦት፣ ወደአገር በሚገባ ዕቃ ወይም በቀጥታ በገዢው ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ላይ የሚከፈለው የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚሰላው በዕቃው ወይም ወደ አገር በሚገባው አቅርቦት ዋጋ ላይ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተመለከተውን የማስከፈያ መጣኔ ተፈፃሚ በማድረግ ይሆናል።

4/ ታክስ በሚከፈልበት አቅርቦት ላይ ተጨማሪ እሴት ታክስ የመክፈል ግዴታ የሚቋቋመው አቅርቦቱ በተከናወነ ጊዜ ሲሆን፣ ታክሱ አቅርቦቱን ባከናወነው የተመዘገበ ሰው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 59(1) መሠረት ገቢ መደረግ አለበት።

5/ በማናቸውም ሕግ የተመለከተው ቢኖርም፣ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የተመዘገበው ሰው ታክስ በሚከፈልበት አቅርቦት ላይ የከፈለውን

የተጨማሪ እሴት ታክስ የአቅርቦቱ ተጠቃሚ ከሆነው ሰው መልሶ የመጠየቅ መብት አለው፡፡

6/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 የተመለከተው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 14(2) በተደነገገው መሠረት በታክሱ ባለስልጣን የተመዘገበ ሰው ከመመዝገቡ በፊት ያከናወነውን ታክስ የሚከፈልበት እንቅስቃሴ በሚመለከት ተፈፃሚ አይሆንም፡፡

7/ ወደአገር በሚገባ አቅርቦት ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ የመክፈል ግዴታ የሚቋቋመው አቅርቦቱ ወደአገር በገባበት ጊዜ ሲሆን፣ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 28 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፤አስመጪው ታክሱን በዚህ አዋጅ አንቀጽ 59(3) በተደነገገው መሠረት መክፈል አለበት፡፡

8/ በቀጥታ በገገርው ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ የመክፈል ግዴታ የሚቋቋመው አቅርቦቱ በተከናወነ ጊዜ ሲሆን፣ አገልግሎቱን ያገኘው የተመዘገበ ሰው፤ የመንግሥት ተቋም ወይም ከፍተኛ ግብይት ያለው ያልተመዘገበ ሰው ታክሱን በዚህ አዋጅ አንቀጽ 59(1) ወይም (2) በተደነገገው መሠረት መክፈል አለበት፡፡

## 9. <u>ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈፃሚ የሚሆንበት አቅርቦት</u>

1/ ከዚህ አዋጅ ጋር በተያያዘው አባሪ 1 የተመለከቱ አቅርቦቶች ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈፃሚ ይደረግላቸዋል፡፡

2/ በአቅርቦቱ ላይ ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈፃሚ እንዲሆን ያደረገ የተመዘገበ ሰው በታክሱ ባለስልጣን ተቀባይነት ያላቸውን አቅርቦቱ ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈፃሚ እንዲሆንለት ለማድረግ ያስቻሉትን የሰነድ ማስረጃዎች መቀበል እና መያዝ አለበት፡፡

## 10. <u>ከታክስ ነፃ የሆኑ አቅርቦቶች</u>

1/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ከዚህ አዋጅ ጋር በተያያዘው አባሪ 2 የተዘረዘሩ አቅርቦቶች ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነፃ ተደርገዋል፡፡

2/ አንድ አቅርቦት ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈፃሚ የሚደረግለት እንዲሁም ከታክሱ ነፃ የተደረገ ከሆነ ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም ዜሮ የማስከፈያ ልክ ብቻ ተፈፃሚ እንዲሆንለት ይደረጋል፡፡

## 11. <u>ከታክሱ ነፃ የሆነ ወደአገር የሚገባ ዕቃ</u>

ከዚህ አዋጅ ጋር በተያያዘው አባሪ 3 የተዘረዘሩ ወደአገር የሚገቡ ዕቃዎች ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነፃ ተደርገዋል፡፡

## ክፍል ሦስት

የገንዘብ የሪፐብሊክ ኢትዮጵያ ፌደራል ዲሞክራቲክ አስተዳደር አገልግሎት 2 ሚኒስቴር

## ስለ መመዝገብ

### 12. የመመዝገብ ግዴታ

1/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 7 እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ማናቸውም ሰው ከዚህ በታች የተዘረዘረውን የሚያሟላ ከሆነ የመመዝገብ ግዴታ አለበት።

ሀ) በማናቸውም የ12 ወራት ጊዜ መጀመሪያ በዚህ ሰው የሚከናወነው ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ጠቅላላ ድምር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ከተመለከተው የገንዘብ መጠን ሊበልጥ እንደሚችል የሚያሳምን ምክንያት ሲኖር፣ ወይም

ለ) በማናቸውም የ12 ወራት ጊዜ መጨረሻ ወይም ከዚህ ባነሰ ጊዜ ውስጥ በዚህ ሰው የተከናወነው ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ጠቅላላ ድምር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ከተመለከተው የገንዘብ መጠን የሚበልጥ ሆኖ ሲገኝ።

2/ ለተጨማሪ እሴት ታክስ የመመዝገብ ግዴታ የሚኖረው ብር 2,000,000 (ሁለት ሚሊዮን ብር) የጠቅላላ አቅርቦት ድምር ሲኖር ወይም ሚኒስቴሩ በመመሪያ የሚወስነው ሌላ ታክስ የሚከፈልበት የአቅርቦት የገንዘብ መጠን ያለው ሰው ነው።

3/ የታክሱ ባለስልጣን አንድ ሰው የመመዝገብ ግዴታ ከሚያስከትለው የገንዘብ መጠን መድረሱን በሚያሰላበት ጊዜ ከዚህ ሰው ጋር ግንኙነት ያለው ሰው ያከናወነውን ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ጨምሮ መደመር አለበት።

4/ አንድ ሰው የመመዝገብ ግዴታ የሚያስከትለው የገንዘብ መጠን ላይ መድረሱ በሚሰላበት ጊዜ የሚከተሉት ታክስ የሚከፈልባቸው አቅርቦቶች ከግምት ውስጥ አይገቡም።

ሀ) ይህ ሰው ለሚያከናውነው ታክስ የሚከፈልበት እንቅስቃሴ ጥቅም ላይ የዋለን የካፒታል ዕቃ ሽያጭ የሚመለከት ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት፣

ለ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ አንድ ሰው የሚያከናውነውን ታክስ የሚከፈልበት እንቅስቃሴ በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ በመሸጡ ምክንያት ወይም ታክስ የሚከፈልበትን እንቅስቃሴ በዘላቂነት በማቆሙ ምክንያት የሚኖረውን ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት፣

5/ የአንድ ሰው ታክስ የሚከፈልበት እንቅስቃሴ ወይም የዚህ ሰው ከፊል ታክስ የሚከፈልበት እንቅስቃሴ ታክስ የሚከፈልበትን እንቅስቃሴ በሙሉ ወይም በከፊል ገዝቶ መሸጥ በሚሆንበት ጊዜ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4(ለ) ድንጋጌ ታክስ የሚከፈልበትን እንቅስቃሴ በሙሉ ወይም በከፊል ገዝቶ በመሸጥ ተግባር ላይ ተፈፃሚ አይሆንም።

6/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የመመዝገብ ግዴታ ያለበት ሰው የመመዝገብ ግዴታ ከሚኖርበት ቀን አንስቶ በ7 ቀናት ውስጥ የፀደቀውን ቅጽ በመጠቀም ወይም በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ለታክሱ ባለስልጣን የምዝገባ ማመልከቻ ማቅረብ አለበት።

7/ የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 8 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ታክስ የሚከፈልበትን አቅርቦት የሚያከናውን የመንግሥት ተቋም በዚህ አንቀጽ መሰረት የመመዝገብ ግዴታ የለበትም፤ ሆኖም በዚህ አዋጅ አንቀጽ 13 መሠረት በፈቃደኝነት ለመመዝገብ ሊያመለክት ይችላል።

8/ የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (7) ድንጋጌ ከንግድ ስራ ወይም በተመሳሳይ አቅርቦት ስራ ላይ ከተሰማራ የንግድ ስራ ጋር ተወዳዳሪ በሆነ አኳኋን በመደበኛነት ታክስ በሚከፈልበት አቅርቦት ስራ ላይ የተሰማራን የመንግስት ተቋም አይጨምርም።

## 13. <u>በፈቃደኝነት ስለመመዝገብ</u>

1/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 12 መሠረት የመመዝገብ ግዴታ የሌለበት ሰው ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት የሚያከናውን ከሆነ ወይም ለማከናወን ያቀደ ከሆነ በፈቃደኝነት ለመመዝገብ ለታክሱ ባለስልጣን ማመልከቻ ሊያቀርብ ይችላል።

2/ አንድ ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የምዝገባ ማመልከቻ ሊያቀርብ የሚችለው የዚህ ሰው በዓመቱ ያከናወነው ወይም ሊያከናውን የሚችለው ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦቱ ዋጋ ከብር 1,000,000 (አንድ ሚሊዮን ብር) ወይም ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ከሚወስነው ሌላ የገንዘብ መጠን የሚበልጥ ሲሆን፣ ነው።

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የሚቀርበው ማመልከቻ የፀደቀውን ቅጽ በመጠቀም መቅረብ አለበት።

## 14. <u>የምዝገባ አፈፃፀም</u>

1/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 12 መሠረት የምዝገባ ማመልከቻ የቀረበለት የታክስ ባለስልጣን አመልካቹ የመመዝገብ ግዴታ ያለበት መሆኑን ሲያምንበት ይመዘግበዋል።

2/ የታክሱ ባለስልጣን በዚህ አዋጅ አንቀጽ 12 መሠረት የመመዝገብ ግዴታ ያለበት ሰው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 12(6) በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ለመመዝገብ ማመልከቻ ያላቀረበ መሆኑን ሲያረጋግጥ በራሱ ውሳኔ እንዲመዘገብ ያደርጋል።

3/ የታክሱ ባልስልጣን በዚህ አዋጅ አንቀጽ 13 መሠረት የምዝገባ ማመልከቻ ያቀረበ ሰው የሚከተሉትን ሁኔታዎች ማሟላቱን ሲያረጋግጥ መመዝገብ አለበት።

ሀ) አመልካቹ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 13(2) የተመለከቱትን ሁኔታዎች የሚያሟላ ከሆነ፣

ለ) አመልካቹ ታክስ የሚከፈልበትን የስራ እንቅስቃሴ የሚያከናውንበት አድራሻ ያለው ወይም ታክስ የሚከፈልበት የስራ እንቅስቃሴ የኢንተርኔት አድራሻን፣የማህበራዊ ሚዲያ አድራሻን ወይም ሌላ የኤሌክትሮኒክ መድረክ በመጠቀም የሚያከናውን ከሆነ፤፣

ሐ) አመልካቹ ታክስ የሚከፈልበትን እንቅስቃሴ ማከናወን የጀመረ ከሆነ፣

(1) የሥራ እንቅስቃሴውን የሚያሳዩ ተገቢ ሰነዶችን የያዘ ከሆነ፣ እና

(2) በታክስ ሕጐች የተጣሉበትን ግዴታዎች የተወጣ ከሆነ፣ እና

መ) ተገቢ የሆነ ሰነዶችን መያዝ እና በቋሚነት እና አስተማማኝ በሆነ ሁኔታ የተጨማሪ እሴት ታክስ ገቢን ማሳወቅን ጨምሮ አመልካቹ በዚህ አዋጅ እና አዋጁን መሠረት በማድረግ በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች የተጣሉበትን ግዴታዎች የሚወጣ መሆኑን የሚያሳምኑ መረጃዎች ያሉ ከሆነ ነው።

4/ የታክሱ ባለሥልጣን በዚህ አዋጅ አንቀጽ 12 እና 13 መሠረት የምዝገባ ማመልከቻ ከቀረበለት ቀን አንስቶ በ21 ቀናት ውስጥ በቀረበው ማመልከቻ ላይ የሰጠውን ውሳኔ የሚገልፅ ምላሽ ለአመልካቹ መስጠት አለበት።

5/ የታክሱ ባለስልጣን በዚህ አንቀጽ መሠረት ለተመዘገበው ሰው በደንቡ የተዘረዘሩ መረጃዎችን የያዘ የተጨማሪ እሴት ታክስ የምስክር ወረቀት መስጠት አለበት።

6/ ከአንድ የንግድ ሥራ ቦታ በላይ ታክስ የሚከፈልበት እንቅስቃሴ የሚያከናውን የተመዘገበ ሰው የፀደቀውን ቅጽ በመጠቀም ለእያንዳንዱ የንግድ ሥራ ቦታ የሚያገለግል የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ይፋዊ ቅጂ እንዲሰጠው ለታክሱ ባለስልጣን ማመልከቻ ማቅረብ የሚችል ሲሆን፣ የታክሱ ባለስልጣንም ይፋዊ ቅጂ ወይም ቅጂዎችን መስጠት አለበት።

7/ ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም አንድ ሰው "የተመዘገበ ሰው" ነው ሊባል የሚችለው፡-

ሀ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ወይም (3) መሠረት ለተመዘገበ ሰው በዚህ ሰው የተጨማሪ እሴት ታክስ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ላይ ከተመለከተው ቀን ጀምሮ፣ወይም

ለ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ለተመዘገበ ሰው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 12(1) በተደነገገው መሠረት ይህ ሰው የመመዝገብ ግዴታ ከተጣለበት የመጀመሪያ ቀን ጀምሮ ነው።

## 15. የተመዘገበ ሰው ግዴታዎች

መዝገብ
የሪከርድ
አስተዳደር
አገልግሎት
2
ሚኒስቴር

1/ ታክስ የሚከፈልበትን የስራ እንቅስቅሴ በማይንቀሳቀስ የስራ ቦታ የሚያከናውን ማናቸውም የተመዘገበ ሰው:-

ሀ) ታክስ የሚከፈልበትን እንቅስቃሴ በሚያካሂድበት ዋንኛ የስራ ቦታ በግልፅ በሚታይ ሥፍራ ዋናውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ የምስክር ወረቀት የመለጠፍ፣

ለ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 14(5) መሠረት የተሰጠውን የተጨማሪ እሴት ታክስ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ቅጂ ታክስ የሚከፈልበት እንቅስቃሴ በሚያካሂድባቸው ሌሎች የስራ ቦታዎች ሁሉ በግልፅ በሚታይ ሥፍራ የመለጠፍ፣ ግዴታ አለበት::

2/ የተመዘገበ ሰው ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገበበትን ዝርዝር መረጃ ታክስ የሚከፈልበትን ስራ በሚያከናውንበት ዌብሳይት፤ የማህበራዊ ሚዲያ እና ሌላ የኤሌክትሮኒክ መድረክ ላይ ማስፈር አለበት::

3/ በታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀጽ ፲ ከተዘረዘሩት መረጃዎች በተጨማሪ በሚከተሉት መረጃዎች ላይ ለውጥ ሲያጋጥም የተመዘገበ ሰው ይህንኑ በ30 ቀን ጊዜ ውስጥ ለታክሱ ባለስልጣን ማስታወቅ አለበት::

ሀ) የተመዘገበው ሰው የስልክ ቁጥር፣ የፋክስ ቁጥር፣ የኤሌክትሮኒክ እና ሌሎች የግንኙነት አድራሻዎች፣

ለ) አዳዲስ ቅርንጫፎችን ወይም የሥራ ክፍሎችን መክፈትና መዝጋትን እንዲሁም የኢንተርኔት፤ የማህበራዊ ሚዲያ ወይም ለንግድ ስራ እንቅስቃሴ ጥቅም ላይ የሚውል ሌላ የኤሌክትሮኒክ መድረክ አድራሻ መለወጥን ጨምሮ የተመዘገበው ሰው ታክስ የሚከፈልበትን እንቅስቃሴ በሚያከናውንበት ቦታ ወይም በሚያከናውንባቸው ቦታዎች፣

ሐ) የተመዘገበው ሰው የንግድ ሥራ ባህሪ፣ እና

መ) በሚኒስቴሩ በሚወጣ መመሪያ የሚዘረዘሩ ሌሎች መረጃዎች::

## 16. <u>የተመዘገበ ሰው ታክስ የሚከፈልበትን አቅርቦት ሲያቆም ስለሚሰጥ ማስታወቂያ</u>

1/ የተመዘገበ ሰው ታክስ የሚከፈልበትን አቅርቦት ማከናወኑን ሲያቆም ይህንኑ ለታክሱ ባለስልጣን ማስታወቅ አለበት::

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የተመዘገበ ሰው የሚሰጠው ማስታወቂያ፣

ሀ) በተፈቀደው ቅጽ በመጠቀም የሚቀርብ፣

ለ) የተመዘገበው ሰው ታክስ የሚከፈልበትን አቅርቦት ማከናወኑን ያቆመበትን ቀን፣

ሐ) በዚህ አንቀጽ ተራ ፊደል (ለ) ከተመለከተው ቀን ጀምሮ በሚቆጠር 12 ወራት ውስጥ የተመዘገበው ሰው ታክስ የሚከፈልበትን አቅርቦት ለማከናወን ፍላጐት ያለው ወይም የሌለው መሆኑን የሚገልጽ ሲሆን፣ እና

መ) የተመዘገበው ሰው ታክስ የሚከፈልበትን አቅርቦት ካቆመበት ቀን አንስቶ በ7 ቀናት ውስጥ መቅረብ አለበት፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ የታክሱ ባለስልጣን ታክስ የሚከፈልበትን አቅርቦት ማከናወኑን ያቆመን የተመዘገበ ሰው የተጨማሪ እሴት ታክስ የምዝገባ የምስክር ወረቀት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የሚቀርብለትን ማስታወቂያ መሠረት በማድረግ ወይም በራሱ አነሳሽነት ለተመዘገበው ሰው የጽሑፍ ማስታወቂያ በመስጠት ለመሠረዝ ይችላል፡፡

4/ የታክሱ ባለስልጣን የተመዘገበው ሰው ታክስ የሚከፈልበትን አቅርቦት ማከናወኑን ካቆመበት ቀን አንስቶ በ12 ወራት ጊዜ መልሶ የሚጀምር መሆኑን የሚያሳምን በቂ ምክንያት ካገኘ፤ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት ምዝገባውን በመሰረዝ ፈንታ የተመዘገበውን ሰው የተጨማሪ እሴት ታክስ የምዝገባ የምስክር ወረቀት የማገድ ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል፡፡

5/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት የተሰጠ የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ የምስክር ወረቀትን የመሠረዝ ውሳኔ ተፈፃሚ የሚሆነው የተመዘገበው ሰው ታክስ የሚከፈልበትን አቅርቦት ማከናወን ካቆመበት የሒሣብ ጊዜ የመጨረሻ ቀን ወይም በስረዛው ውሳኔ ማስታወቂያ ከተገለፀው ቀን ጀምሮ ይሆናል፡፡

6/ ታክስ የሚከፈልበትን አቅርቦት የማከናወኑን ተግባር በጊዜያዊነት ያቋረጠ የተመዘገበ ሰው የፀደቀውን ቅጽ በመጠቀም ምዝገባው ለ12 ወራት እንዲታገድለት ሊያመለክት ይችላል፡፡

7/ የታክሱ ባለስልጣን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 መሠረት ማመልከቻ ያቀረበው የተመዘገበ ሰው ታክስ የሚከፈልበትን አቅርቦት ማከናወኑን ያቋረጠ መሆኑን እና ማመልከቻው ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ በሚቆጠር የ12 ወራት ጊዜ ውስጥ መልሶ ታክስ የሚከፈልበትን አቅርቦት የሚያከናውን መሆኑን ሲያምንበት ምዝገባውን ሊያግድ ይችላል፡፡

8/ የተመዘገበ ሰው ምዝገባ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 ወይም 7 መሠረት ሊታገድ የሚችለው በደንቡ በሚዘረዘሩ ሁኔታዎች እና ግዴታዎች እንዲሁም የታክሱ ባለስልጣን ለተመዘገበው ሰው በሚሰጠው የእገዳ ማስታወቂያ በሚዘረዘሩ ሁኔታዎች እና ግዴታዎች መሰረት ይሆናል፡፡

17. **<u>የመመዝገብ ግዴታን ከሚያስከትለው የገንዘብ መጠን በታች በመሆን ምክንያት ስለሚቀርብ የምዝገባ ሥረዛ ማመልከቻ</u>**

1/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የተመዘገበው ሰው የሚያከናውነው ዓመታዊ ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ዋጋ የመመዝገብ ግዴታን ከሚያስከትለው የገንዘብ መጠን ሲወርድ የተመዘገበው ሰው የተፈቀደውን ቅጽ በመጠቀም ምዝገባው እንዲሰረዝለት ሊያመለክት ይችላል።

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ምዝገባ እንዲሰረዝ ጥያቄ ሊቀርብ የሚችለው ምዝገባው ከተከናወነበት ቀን ጀምሮ ከሚቆጠር የ2 ዓመት ጊዜ በኋላ ነው።

3/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ቢኖርም ለተጨማሪ እሴት ታክስ የመመዝገብ ግዴታ ያለበት መሆኑን በማመን በስህተት የተመዘገበ ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የምዝገባ ሥረዛ ማመልከቻውን ከተመዘገበበት ቀን በኋላ የመጀመሪያውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ገቢ ማስታወቂያ ማቅረብ ከሚገባው ቀን በፊት ሊያቀርብ ይችላል።

4/ የታክሱ ባለስልጣን የተመዘገበው ሰው በአንድ ዓመት ውስጥ ያከናወነው ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ዋጋ የመመዝገብ ግዴታን ከሚያስከትለው የገንዘብ መጠን በታች መሆኑን ሲያምንበት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ምዝገባው እንዲሠረዝ ተገቢውን ማመልከቻ ላቀረበው የተመዘገበ ሰው የጽሁፍ ማስታወቂያ በመስጠት ምዝገባውን ሊሰርዝ ይችላል።

5/ የታክሱ ባለስልጣን የተመዘገበው ሰው በአንድ ዓመት ውስጥ ያከናወነው ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ጠቅላላ ዋጋ የመመዝገብ ግዴታን ከሚያስከትለው የገንዘብ መጠን በታች ሲሆን፣ እንዲሁም የታክሱ ባለስልጣን ከሚከተሉት ሁለቱ ወይም ከሁለቱ አንዱ መፈፀማቸውን ሲያምንበት፤

ሀ) የተመዘገበው ሰው ተገቢ የሆኑ የተጨማሪ እሴት ታክስ መረጃዎችን ወይም በዚህ አዋጅ የተመለከቱ ሰነዶችን ያለመያዙን ፤

ለ) የተመዘገበው ሰው በመደበኛነት እና በአስተማማኝነት የተጨማሪ እሴት ታክስ ገቢውን የማያስታውቅ መሆኑን ሲያምንበት፣ በራሱ ተነሳሽነት ለተመዘገበው ሰው የጽሑፍ ማስታወቂያ በመስጠት ምዝገባውን ሊሠርዝ፣ ይችላል።

6/ በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚከናወን የምዝገባ ሥረዛ ተፈፃሚ የሚሆነው በሥረዛ ማስታወቂያው ከተመለከተው ቀን ጀምሮ ይሆናል።

18. **<u>ምዝገባው የተሰረዘበት ሰው ግዴታዎች</u>**

1/ አንድ ሰው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 16 ወይም 17 መሠረት የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ የተሰረዘበት እንደሆነ፣

ሀ) ታክስ የሚከፈልበትን የስራ እንቅስቃሴ ለማከናወን የሚጠቀምባቸውን ማናቸውንም ሰነዶች እና ማናቸውንም ዌብሳይት፤ ማህበራዊ ሚዲያ ወይም ሌላ የኤሌክትሮኒክ መድረክ ጨምሮ በማናቸውም መልኩ ይህ ሰው ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገበ መሆኑን የሚገልፁ ድርጊቶችን ወዲያውኑ ማቆም፣

ለ) ምዝገባው ከተሰረዘበት ቀን አንስቶ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ወይም የታክሱ ባለስልጣን በሚሰጠው የጽሑፍ ማስታወቂያ በሚገለጽ ቀደም ያለ ሌላ ጊዜ ውስጥ፣ የፀደቀውን ቅጽ በመጠቀም የመጨረሻውን የተጨማሪ እሴት ታክስ የገቢ ማስታወቂያ ማቅረብ እና የሚፈለግበትን የተጨማሪ እሴት ታክስ መክፈል፣ እና

ሐ) የተሰጠውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ዋና የምዝገባ የምስክር ወረቀት እና የዚህን የምስክር ወረቀት ይፋዊ ቅጂዎች ወዲያውኑ ለታክሱ ባለስልጣን የመመለስ፣ ግዴታ አለበት፡፡

2/ የተመዘገበ ሰው የተጨማሪ እሴት ታክስ ገቢውን በማስታወቅ እና የተጨማሪ እሴት ታክስን በመክፈል ረገድ ያለበትን ግዴታ ጨምሮ ምዝገባው ፀንቶ በነበረበት ጊዜ ውስጥ ካከናወናቸው ተግባራት ወይም ካልፈፀማቸው ግዴታዎች ጋር በተያያዘ የሚኖርበት ግዴታ እና ተጠያቂነት ምዝገባው በመሰረዙ ምክንያት ቀሪ አይሆንም፡፡

3/ ምዝገባው በሚሰረዝበት ቀን ያልተቀናነሰው የግብአት ታክስ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 49 በተመለከተው መሠረት እንዲፈጸም ይደረጋል፡፡

## 19. <u>ምዝገባ በሚሠረዝበት ጊዜ እንደተከናወኑ ስለሚቆጠሩ ታክስ የሚከፈልባቸው አቅርቦቶች</u>

1/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 17 እና 18 መሠረት የተመዘገበ ሰው የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ የተሰረዘ እንደሆነ ምዝገባው በተሰረዘ ጊዜ በእጁ የሚገኙትን የንግድ ዕቃዎች እና የካፒታል እቃዎች አቅርቦት እንዳከናወነ ይቆጠራል፡፡ ሆኖም እነዚህ ዕቃዎች ታክስ የሚከፈልባቸው አቅርቦቶች እንደሆኑ የሚቆጠረው የተመዘገበው ሰው እነዚህን የንግድ ዕቃዎች ወይም የካፒታል ዕቃዎች ሲገዛ ወይም ወደአገር ሲያስገባ ለከፈለው የተጨማሪ እሴት ታክስ ተቀናሽ (ክሬዲት) ያገኘ ወይም የንግድ ዕቃዎችን በሚመለከት ለእነዚህ ዕቃዎች ማምረቻ የዋሉ ግብአቶችን ሲገዛ ወይም ወደአገር ሲያስገባ ለከፈለው የተጨማሪ እሴት ታክስ ተቀናሽ ያገኘ እንደሆነ ነው፡፡

2/ የተመዘገበው ሰው ምዝገባው ከመሰረዙ በፊት ባለው ጊዜ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የንግድ ዕቃዎች ወይም የካፒታል ዕቃዎች ታክስ የሚከፈልባቸው አቅርቦቶች እንዲሆኑ የማድረግ ተግባር ያከናወነ እንደሆነ ተፈፃሚ ይቆጠራል፡፡

3/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ተፈፃሚ ሲሆን፣ ምዝገባው በተሰረዘ ጊዜ የንግድ ዕቃዎች በእጁ የሚገኙ የተመዘገበ ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) በተመለከተው ጊዜ እነዚህን ዕቃዎች በሚገዛበት ወይም ወደአገር በሚያስገባበት ጊዜ ለከፈለው የግብአት ታክስ ካገኘው ቅናሽ ለእነዚህ የንግድ ዕቃዎች ማምረቻ በዋለው ግብዓት ላይ ለከፈለው የተጨማሪ እሴት ታክስ ካገኘው ቅናሽ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ የውጤት ታክስ እንደተቀበለ ይቆጠራል።

4/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ የተመዘገበ ሰው ምዝገባ በሚሰረዝበት ጊዜ በእጁ የሚገኙ የካፒታል ዕቃዎችን በሚመለከት ተፈፃሚ በሚደረግበት ጊዜ የተመዘገበው ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) በተመለከተው ጊዜ በእጁ ለሚገኙ የካፒታል ዕቃዎች ከዚህ በታች በተመለከተው ቀመር መሠረት የውጤት ታክስ እንደተቀበለ ይቆጠራል።

$$ሀ \times {}^{ለ}/_{ሐ}$$

ሀ) የተመዘገበው ሰው የካፒታል ዕቃዎችን በገዛበት ጊዜ ያገኘው የግብአት ታክስ ተቀናሽ፣

ለ) በገቢ ግብር አዋጅ በተደነገገው መሠረት የሚወሰን የተመዘገበው ሰው ምዝገባ በተሰረዘበት ጊዜ የካፒታል ዕቃዎች ያላቸው የተጣራ የመዝገብ ዋጋ፣ እና

ሐ) ለካፒታል ዕቃዎቹ የተደረገው የመጀመሪያው ወጪ።

## ክፍል አራት

## ስለ አቅርቦት

20. **ቅይጥ አቅርቦቶች**

1/ አገልግሎትን ከማቅረብ ጋር በተያያዘ የሚከናወን የዕቃ አቅርቦት የአገልግሎት አቅርቦት እንደሆነ ተደርጐ ይወሰዳል።

2/ ከዕቃ አቅርቦት ጋር በተያያዘ የሚከናወን የአገልግሎት አቅርቦት የዕቃ አቅርቦት እንደሆነ ተደርጐ ይወሰዳል።

3/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 27(1) (ሀ) መሠረት ከውጭ አገር የተሰጠ አገልግሎት ዋጋ ውስጥ የአገልግሎት አቅርቦት ዋጋ የተካተተ ከሆነ የአገልግሎቱ አቅርቦት ከውጭ አገር የተሰጠ አገልግሎት እንደሆነ ተደርጐ ይወሰዳል።

የፍትህ ሚኒስቴር
የሪከርድ እስ.ዶ.ዶ.ር አገልግሎት 2

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ አንድ አቅርቦት የዕቃ አቅርቦት እና የአገልግሎት አቅርቦት ከሆነ፣ የታክሱ ባለስልጣን ምክንያታዊ በሆነ መንገድ አቅርቦቱ የዕቃ አቅርቦት ወይም የአገልግሎት አቅርቦት ተደርጐ የሚወሰድበትን ሁኔታ በመመሪያ ይወስናል።

5/ አቅርቦቱ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን በሙሉ ወይም በከፊል የሚይዝ በሚሆንበት ጊዜ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 ድንጋጌ ተፈፃሚ ይሆናል።

ሀ) አቅርቦቱ የተጨማሪ እሴት ታክስ የማስከፈያ መጣኔ ተፈፃሚ የሚደረግበት ሲሆን፣

ለ) አቅርቦቱ ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈፃሚ የሚደረግለት ሲሆን፣

ሐ) አቅርቦቱ ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነፃ በሚሆንበት ጊዜ።

6/ በዚህ አንቀስ ንኡስ አንቀጽ 7 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፤በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (5) የተደነገገው የተሟላ ሲሆን፤ አንድ ግብይት የማይቀር የሌላ ግብይት አካል ሆኖ፤ የማይቀረው ግብይት የሌላኛው ግብይት አካል ካልሆነ በስተቀር እያንዳንዱ የአቅርቦቱ ክፍል ራሱን የቻለ አቅርቦት እንደሆነ ይቆጠራል።

7/ በዱቤ ግዥ ወይም በፋይናንስ ሊዝ ውል ለሚቀርብ ዕቃ ራሱን የቻለ ክፍያ ሆኖ የተካተተ እና ለአቅርቦቱ ተጠቃሚ የተገለፀ የወለድ ክፍያን የሚጨምር ሲሆን፣ የዚህ ዓይነቱ አቅርቦት የዕቃ አቅርቦት እና የፋይናንስ አገልግሎትን የያዘ ሁለት አቅርቦት እንደሆነ ተደርጐ ይወሰዳል።

## 21. <u>አቅርቦት ተከናወነ የሚባልበት ጊዜ</u>

1/ በዚህ አዋጅ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ አቅርቦቱ ተከናወነ የሚባለው ከሚከተሉት በቀደመው ጊዜ ነው።

ሀ) ለአቅርቦቱ የታክስ ደረሰኝ በተሰጠበት ቀን፣

ለ) ለአቅርቦቱ ማናቸውም ዓይነት ክፍያ (ከፊል ክፍያን ጨምሮ) በተፈፀመበት ቀን፣

ሐ) ከሚከተሉት አንዱ በተፈፀመበት ቀን፣

(i) የዕቃ አቅርቦትን በሚመለከት፣ የዕቃው ርክክብ በተፈፀመበት ወይም ዕቃው ለአቅርቦቱ ተቀባይ ዝግጁ በሆነበት ቀን፣ ወይም

(ii) የአገልግሎት አቅርቦትን ወይም በቀጥታ በገቢው ታክስ የሚከፈልበትን አቅርቦት በሚመለከት፣ አገልግሎት የመስጠቱ ተግባር ሲጠናቀቅ።

2/ የዕቃው አቅርቦት በሣንቲም፣ በወረቀት ገንዘብ ወይም ገንዘብን በሚተካ ነገር በሚሠራ ማሽን፣ የመቁጠሪያ መሣሪያ ወይም ሌላ መሣሪያ አማካኝነት የሚፈፀም ከሆነ፣ በአቅራቢው ወይም አቅራቢውን በሚወክለው ሰው አማካኝነት ሣንቲሙ፣ የወረቀት ገንዘቡ ወይም ገንዘብን የሚተካው ነገር ከማሽኑ፣ ከመቁጠሪያ መሣሪያው ወይም ከሌላ መሣሪያ በወጣበት ቀን አቅርቦቱ እንደተከናወነ ይቆጠራል፡፡

3/ ማናቸውም በተወሰነ ጊዜ ልዩነት የሚከናወን አቅርቦት፡-

ሀ) በኪራይ ውሉ ወይም በስምምነቱ መሠረት ወይም እንደሁኔታው በሕግ በተወሰነው መሠረት ክፍያው የሚፈፀመው ለውሉ ከፊል ጊዜ በተከታታይነት ከሆነ የዚህ አይነቱ አቅርቦት በተወሰነ ጊዜ ልዩነት በተከታታይነት ክፍያው የሚፈፀም ራሱን የቻለ አቅርቦት እንደሆነ፣ እና

ለ) እያንዳንዱ ተከታታይ አቅርቦት ክፍያው ሊፈጸም በሚገባው ቀን ወይም ክፍያው በተፈፀመበት ቀን ከሁለቱ በቀደመው እንደተከናወነ፣ ይቆጠራል፡፡

4/ ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም "**በተወሰነ ጊዜ ልዩነት የሚከናወን አቅርቦት**" ማለት

ሀ) በዱቤ ግዥ ወይም በፋይናንስ ሊዝ ውል መሠረት የሚቀርብ ዕቃ፣ ወይም

ለ) የሚከተሉትን የሚያሟላ የአገልግሎት አቅርቦት፣

(1) በዕቃ ኪራይ ውል የተሰጠ (በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) የተመለከተውን ሊዝ ሳይጨምር)፤ ወይም

(2) ክፍያው በተወሰነ ጊዜ ልዩነት እንዲፈጸም በሚያዝ ውል ወይም ሕግ መሠረት በየደረጃው የሚፈፀም አቅርቦት፡፡

22. <u>የአቅርቦት እሴት</u>

1/ በዚህ አዋጅ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የአቅርቦት እሴት ነው የሚባለው ለአቅርቦቱ የተከፈለው የግብይት ዋጋ ነው፡፡

2/ የተመዘገበ ሰው አቅርቦቱን ያከናወነው ግንኙነት ላለው ሰው ከአቅርቦቱ ትክክለኛ የገበያ ዋጋ በታች በሆነ ዋጋ (በነፃ የተከናወነ አቅርቦት ጭምር) የሆነ እንደሆነ የአቅርቦቱ ዋጋ እንደሆነ የሚቆጠረው አቅርቦቱ በተከናወነ ጊዜ ያለው የአቅርቦቱ ትክክለኛ የገበያ ዋጋ ይሆናል፡፡

3/ በዚህ አዋጅ በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር በነፃ የተከናወነ አቅርቦት ዋጋ ዜሮ ይሆናል፡፡

4/ የተመዘገበ ሰው ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ሲያከናውን የተጨማሪ እሴት ታክሱን መጠን ለይቶ ያላሳየ እንደሆነ የአቅርቦቱ ዋጋ በሚከተለው ቀመር መሠረት ይሰላል፡፡

$ሀ - (ሀ \times ለ)$

በዚህ ቀመር ውስጥ

ሀ) ለአቅርቦቱ የተከፈለው ጠቅላላ ዋጋ እና

ለ) የታክሱ ክፍልፋይ፣ ነው።

5/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ የተመዘገበ ሰው ለሌላ የተመዘገበ ሰው የሚያከናውነውን ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት በሚመለከት ተፈፃሚ በሚደረግበት ጊዜ፣ አቅርቦቱን የተቀበለው የተመዘገበ ሰው የግብአት ታክስ የሚሰላው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት በሚወሰነው የዕቃው ዋጋ ይሆናል።

6/ ከውጭ አገር በገባ የዕቃ አቅርቦት ላይ የተከፈለው ዋጋ ከዕቃው የጉምሩክ ዋጋ በታች የሆነ እንደሆነ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ የዕቃው የጉምሩክ ዋጋ የአቅርቦቱ ዋጋ እንዲሆን ሊያደርግ ይችላል።

23. <u>በኢትዮጵያ የተከናወነ የዕቃ አቅርቦት</u>

1/ የዕቃ አቅርቦት በኢትዮጵያ ውስጥ ተከናውኗል ለማለት የሚቻለው፣

ሀ) የትራንስፖርት አገልግሎትን የሚጨምር የዕቃ አቅርቦት ሲሆን፣ የትራንስፖርት አገልግሎቱ ከኢትዮጵያ የሚነሳ ሲሆን፣ ወይም

ለ) ለሌላ ማናቸውም የዕቃ አቅርቦት፣ አቅራቢው ዕቃዎቹን በኢትዮጵያ ውስጥ ለገበያ ዝግጁ ሲያደርግ ይሆናል።

2/ ታክስ የሚከፈልበትን የስራ እንቅስቃሴ ከኢትዮጵያ ውጪ የሚያከናውን እና በኢትዮጵያ ውስጥ ቋሚ የስራ ቦታ የሌለው ሰው በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ የታዘዘን ዕቃ በኢትዮጵያ ውስጥ አቅርቧል የሚባለው የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲሟሉ ይሆናል፤

ሀ) አቅራቢው ኢትዮጵያ ውስጥ እቃዎችን የሚያስረክብ ወይም ግዢ የሚፈጽም፣ የሚያመቻች ወይም የሚያሰናዳ ሲሆን፤

ለ) አቅርቦቱ የተከናወነው በኤሌክትሮኒክ የማከፋፈያ ገበያ ሲሆን፤

ሐ) የኤሌክትሮኒክስ ማከፋፈያ ገበያውን የሚያስተዳድረው ሰው ዕቃውን ለማቅረብ ወይም አቅርቦቱን ለማመቻቸት የሚያስፈልገውን ግዥ ከኢትዮጵያ የሚፈፅም ከሆነ፤ እና

መ) ዕቃዎቹ በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 1186/2012 (እንደተሻሻለ) መሠረት የኤክሳይዝ ታክስ ያልተጣለባቸው ወይም የጉምሩክ ቀረጥ የማይከፈልባቸው ከሆነ፡
:

3/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ተፈፃሚ በሚሆንበት ሁኔታ የኤሌክትሮኒክ ማከፋፈያው ገበያ አንቀሳቃሽ ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም የዕቃ አቅርቦት እንደፈፀመ ይቆጠራል።

## 24. <u>በኢትዮጵያ የተከናወነ የአገልግሎት አቅርቦት</u>

1/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የአገልግሎት አቅርቦት በኢትዮጵያ ውስጥ ተከናውኗል ለማለት የሚቻለው አገልግሎቱ የተሰጠበት የአቅራቢው የንግድ ሥራ ቦታ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ ሲሆን ነው።

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም የሚከተሉት ሁኔታዎች ከተሟሉ በቀጥታ በገዢው ታክስ የሚከፈልበትን አቅርቦት ሳይጨምር ታክስ የሚከፈልበትን የስራ እንቅስቃሴ ከኢትዮጵያ ውጪ የሚያከናውን እና በኢትዮጵያ ውስጥ ቋሚ የሥራ ቦታ የሌለው ሰው የሚያከናውነው የአገልግሎት አቅርቦት በኢትዮጵያ ውስጥ እንደተከናወነ ይቆጠራል፤

ሀ) አገልግሎቱ በአካል በኢትዮጵያ ውስጥ የተከናወነ ሆኖ አቅርቦቱ በተሰጠ ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጥ በነበረ ሰው ከሆነ፣

ለ) አገልግሎቱ በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኝ የማይንቀሳቀስ ንብረት ጋር የተገናኘ ከሆነ፤

ሐ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) በተደነገገው መሠረት አገልግሎቱ በኢትዮጵያ ነዋሪ ለሆነ ሰው ከሩቅ የሚሰጥ አገልግሎት ሲሆን፣

መ) አገልግሎቱ በጥቅል የሚሰጥ የቱሪዝም አገልግሎት ወይም በጥቅል ከሚሰጥ የቱሪዝም አገልግሎት ጋር የተያያዘ የውክልና ወይም የምዝገባ አገልግሎት ሲሆን፤

ሠ) አገልግሎቱ በኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ መጠቀም የሚቻል የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ከሆነ፤ ወይም

ረ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሠ) የተመለከተውን ሳይጨምር የአለምአቀፍ የስልክ አገልግሎት ተጠቃሚ በሆነ ሰው ሞባይል ላይ የተጫነው የደንበኛ ማንነት ሞጁል ካርድ የሚያሳየው የሞባይል የአገር መለያ ቁጥር የኢትዮጵያ ከሆነ የቴሌኮሚኒኬሽን አገልግሎት እንደተሰጠ ይቆጠራል።

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) (ሐ) አፈፃፀም ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት መለኪያዎች ውስጥ ቢያንስ ሁለቱ ከተሟሉ ከሩቅ የሚሰጥ አገልግሎት ተጠቃሚ የሆነ ሰው በኢትዮጵያ ነዋሪ እንደሆነ ይቆጠራል።

ሀ) ለአገልግሎቱ ተቀባይ የክፍያ መጠየቂያ የሚላክበት አድራሻ፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ከሆነ፤

ለ) የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ለክፍያ የሚጠቀምበትን የባንክ ሒሣብ ወይም በባንኩ ዘንድ የሚገኘውን የክፍያ መጠየቂያ አድራሻ ጨምሮ የተጠቃሚው የባንክ ሂሳብ በኢትዮጵያ ውስጥ ከሆነ፤፣

ሐ) ለተጠቃሚው የስልክ አገልግሎት የሚሰጥበት የማይንቀሳቀስ ስልክ መስመር ወይም ሌላ የቦታ መለያ ዘዴ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ ከሆነ፤

መ) የአለም አቀፍ የስልክ አገልግሎት ተጠቃሚ የሆነ ሰው በሚገለገልበት የደንበኛ ማንነት ሞጁል ካርድ ላይ የተጫነው የተንቀሳቃሽ ስልክ የአገር መለያ ቀጥር የኢትዮጵያ ከሆነ፣

ሠ) የአገልግሎቱ ተጠቃሚ አገልግሎቱን የሚያገኝበት መሳሪያ የኢንተርኔት ፕሮቶኮል አድራሻ ወይም ሌላ የቦታ አድራሻ መለያ የኢትዮጵያ ከሆነ፤ ወይም

ረ) ሌላ ማናቸውም የአገልግሎቱ ተጠቃሚ የኢትዮጵያ ነዋሪ መሆኑን የሚያረጋግጥ ለንግድ አግባብነት ያለው መረጃ::

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ከተዘረዘሩት መለኪያዎች ውስጥ ሁለቱ የአገልግሎቱ ተጠቃሚ በኢትዮጵያ ነዋሪ መሆኑን የሚደግፉ እና ሁለቱ ደግሞ በሌላ አገር ነዋሪ መሆኑን የሚደግፉ በሚሆንበት ጊዜ የአገልግሎቱን ተጠቃሚ አድራሻ ለመወሰን የበለጠ አስተማማኝ ናቸው የሚላቸውን መሠረት በማድረግ አቅራቢው የአገልግሎቱን ተጠቃሚ አድራሻ ይወስናል::

5/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) አፈፃፀም በንኡስ አንቀጽ (3) ከተመለከቱት መለኪያዎች ውስጥ አስተማማኝ ከሆነው በመጀመር አስተማማኝነትን መሠረት በማድረግ በቅደም ተከተል ተዘርዝረዋል::

6/ አቅራቢው የአገልግሎቱ ተጠቃሚ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (3) መሰረት በኢትዮጵያ ነዋሪ መሆኑን ከወሰነ በኋላ፤ የአገልግሎቱ ተጠቃሚ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 65 መሰረት ካላስታወቀው በስተቀር የአገልግሎቱ ተጠቃሚ አቅርቦቱን በተመለከተ በገዢው የሚሰበሰብ ታክስ የማይመለከተው እንደሆነ መቁጠር አለበት::

## 25. በኤሌክትሮኒክ የማከፋፈያ ገበያ አማካኝነት ከሩቅ የሚከናወን የአገልግሎት አቅርቦት

1/ ይህ አንቀጽ ተፈፃሚ የሚሆነው የሚከተሉት ሲሟሉ ይሆናል፣

ሀ) አቅራቢው ("እውነተኛ አቅራቢ" ተብሎ የሚታወቀው) ከሩቅ የሚከናወነውን አቅርቦት የሚያከናውነው በኤሌክትሮኒክ የማከፋፈያ ገበያ አማካኝነት ሲሆን፣

ለ) የኤሌክትሮኒክ የማክፋፈያ ገበያ ሥራ የሚያከናውነው ሰው (ከዚህ በኋላ "የስራ አንቀሳቃሽ" ተብሎ የሚጠራ) በኢትዮጵያ ውስጥ የንግድ ሥራ ቦታ የሌለው ከሆነ፤

ሐ) የስራው አንቀሳቃሽ ከሚከተሉት አንዱን የሚያከናውን ከሆነ፤

(i) የአቅርቦቱን ዋጋ ከአቅርቦቱ ተጠቃሚ እንዲጠየቅ የሚያደርግ፤፣

(ii) አቅርቦቱን ለአቅርቦቱ ተጠቃሚ የሚያደርስ ወይም እንዲደርስ የሚያደርግ ወይም

(iii) በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ አቅርቦቱ የሚከናወንባቸውን የውል ቃሎችና ሁኔታዎች የሚወስን፣ እና

መ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፬(፫) በተደነገገው መሰረት የአቅርቦቱ ተጠቃሚ የኢትዮጵያ ነዋሪ እና ያልተመዘገበ ሰው፤ የመንግስት ተቋም ወይም ከፍተኛ ያልተመዘገበ ሰው፤ ከሆነ ነው።

2/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌዎች ሲሟሉ የኤሌክትሮኒክ ማከፋፈያ ገበያውን ሥራ የሚያከናውነው ሰው ታክስ የሚከፈልበትን የሥራ እንቅስቃሴ በማከናወን ሂደት ከሩቅ የሚከናወን የአገልግሎት አቅርቦት ወይም በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ የሚታዘዝ ዕቃ አቅርቦት እንደፈፀመ ተቆጥሮ የአዋጁ አንቀጽ 24(2) ድንጋጌ ተፈፃሚ ይሆናል።

3/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች ዋንኛው አቅራቢ የተመዘገበ ሰው በሚሆንበት ጊዜ ተፈፃሚ አይሆኑም።

## ክፍል አምስት

## ዕቃን ወደአገር ስለማስገባት

### 26. ዕቃ ወደአገር ገባ የሚባልበት ጊዜ

1/ ዕቃ ወደአገር ገብቷል የሚባለው:-

ሀ) በጉምሩክ አዋጅ መሠረት ለአገር ውስጥ ፍጆታ ወደአገር የሚገቡ ዕቃዎችን በሚመለከት፣ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓትን ባጠናቀቁበት ቀን፣ ወይም

ለ) ለሌሎች ማናቸውም ዕቃዎች፣ ዕቃዎቹ ወደ ኢትዮጵያ በገቡበት ቀን፣ ይሆናል።

2/ ወደ ቦንድድ የጉምሩክ መጋዘን የገባ እና የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓትን አጠናቆ ለአገር ውስጥ ፍጆታ እንዲውል ያልወጣ ዕቃን በሚመለከት ለአገር ውስጥ ፍጆታ እንዲውል

የሪቨርና አስተዳደር አገልግሎት

ከመጋዘን ከመውጣቱ በፊት የተከናወነ አቅርቦት ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም ከግምት ውስጥ የሚገባ አይሆንም፡፡

3/ ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም "የተፈቀደ የጉምሩክ መጋዘን" የሚለው ሀረግ በጉምሩክ አዋጅ የተሰጠውን ትርጉም ይይዛል፡፡

27. <u>ወደአገር የገባ ዕቃ እሴት</u>

1/ በዚህ አንቀጽ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ወደአገር የገባ ዕቃ እሴት የሚከተሉት ድምር ይሆናል፡፡

ሀ) ወደአገር የገባው ዕቃ ቀረጥ የሚከፈልበት ቢሆንም ባይሆንም በጉምሩክ አዋጅ መሠረት የሚወሰነው የዕቃው ዋጋ፣ እና

ለ) ወደአገር በገባው ዕቃ ላይ የሚከፈል የጉምሩክ ቀረጥ፣ የኤክሳይዝ ታክስ እና ሌላ ማናቸውም ታክስ እንዲሁም ማናቸውም ክፍያ፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)(ለ) መሠረት የሚወሰነው የዕቃው እሴት የተጨማሪ እሴት ታክስን ወይም በዕቃው ላይ የሚከፈልን ወይም የተከፈለን የገቢ ግብር የቅድሚያ ክፍያን አይጨምርም፡፡

3/ ወደአገር በገባው ዕቃ ላይ፣

ሀ) የቅርጽ ወይም የባህሪ ለውጥ፣ እና

ለ) ዕቃው ወደውጭ ከተላከበት ጊዜ አንስቶ የባለቤትነት ለውጥ፣

እስካልተደረገ ድረስ ለጥገና፣ ለዕድሳት ወይም ለማሻሻያ ወደውጭ አገር የተላከ ዕቃ ተመልሶ ወደአገር በሚገባበት ጊዜ ለተጨማሪ እሴት ታክስ ክፍያ መሠረት የሚሆነው በጥገናው፣ በዕድሳቱ ወይም በማሻሻያው ምክንያት የታከለው ተጨማሪ እሴት ይሆናል፡፡

4/ የዚህ አዋጅ አንቀጽ 26(2) ተፈጻሚ የሚደረግበት ወደአገር የሚገባ እቃ እሴት ነው ተብሎ የሚወሰደው ከሚከተሉት ከፍተኛው ይሆናል፦

ሀ) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) መሰረት የሚወሰነው እሴት፤ ወይም

ለ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 26(2) መሰረት የሚወሰነው የእቃው አቅርቦት እሴት፤

5/ ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም "የገቢ ግብር የቅድሚያ ክፍያ" የሚባለው በገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 85 መሠረት ወደአገር በሚገባ ዕቃ ላይ የሚከፈለው ግብር ነው፡፡

28. <u>ወደአገር በሚገቡ የካፒታል ዕቃዎች ላይ ሊከፈል የሚገባው የተጨማሪ እሴት ታክስ እንዲዘገይ ስለማድረግ</u>

1/ የተመዘገበ ሰው የፀደቀውን ቅጽ በመጠቀም ወደአገር በሚያስገባቸው የካፒታል ዕቃዎች ላይ ሊከፈል የሚገባው የተጨማሪ እሴት ታክስ እንዲዘገይ ለኮሚሽኑ ማመልከቻ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

2/ ኮሚሽኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ማመልከቻ ሲቀርብለት፣ የሚከተሉት ሁኔታዎች መሟላታቸውን ሲያምንበት ክፍያው እንዲዘገይ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

ሀ) የተመዘገበው ሰው ተገቢውን መረጃ የሚይዝ፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ ገቢውን በወቅቱ የሚያስታውቅ እና በዚህ አዋጅ የተጣሉበትን ሌሎች ግዴታዎች የሚወጣ፣

ለ) የተመዘገበው ሰው የሚፈለግበት የተጨማሪ እሴት ታክስ ወይም ሌላ የግብር ዕዳ የሌለ፣ እና

ሐ) አመልካቹ ሰው፣

(i) በታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀጽ 110 መሠረት የሚፈለግበት አስተዳደራዊ መቀጫ የሌለ፣

(ii) በታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀጽ 118፣ 119፣ 121 ወይም 125 መሠረት ለተመለከቱት ጥፋቶች ተከሶ ያልተፈረደበት፣ ወይም

(iii) በተመሳሳይ ጥፋት ምክንያት በጉምሩክ አዋጅ መሠረት አስተዳደራዊ ቅጣት የማይፈለግበት ወይም በወንጀል ያልተቀጣ፡፡

3/ ኮሚሽኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ፈቃድ ከመስጠቱ በፊት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ማመልከቻ ያቀረበው የተመዘገበ ሰው በታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀጽ 35 መሠረት ዋስትና እንዲያቀርብ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

4/ ኮሚሽኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ማመልከቻ ያቀረበው ሰው ማመልከቻውን ባቀረበ በ14 ቀናት ውስጥ በጥያቄው መሠረት የተሰጠውን ውሳኔ እንዲያውቅ ማድረግ አለበት፡፡

5/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (6) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የሚሰጠው ፈቃድ ተፈፃሚ የሚሆነው፡-

ሀ) በፈቃዱ ለተመለከቱ ወደአገር ለሚገቡ የካፒታል ዕቃዎች፣ ወይም

ለ) በፈቃዱ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ወደአገር ለሚገቡ የካፒታል ዕቃዎች፣ ይሆናል፡
፡

6/ የተመዘገበው ሰው፡-

ሀ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ቁጥር (2) የተቀመጡትን ቅድመ ሁኔታዎች ካጓደለ፣ ወይም

ለ) የካፒታል ዕቃዎቹን ለሌላ ሰው ካስተላለፈ ወይም ካስወገደ፣

ኮሚሽኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የሰጠውን ፈቃድ ሊሰርዝ ይችላል

7/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ፈቃድ የተሰጠው የተመዘገበ ሰው ዕቃው ወደአገር በገባበት የሒሣብ ጊዜ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 48 መሠረት ሊከፈል የሚገባውን የተጣራ የተጨማሪ እሴት ታክስ ስሌት በሚያከናውንበት ጊዜ በፈቃዱ በተመለከተው ታክስ በሚከፈልበት የካፒታል ዕቃ ላይ ሊከፈል የሚገባውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ማካተት አለበት፡፡

8/ በዚህ አንቀጽ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ሚኒስቴሩ ወደአገር በሚገቡ የካፒታል ዕቃዎች ላይ ሊከፈል የሚገባው የተጨማሪ እሴት ታክስ እንዲዘገይ የሚደረግበትን ሁኔታ በመመሪያ ሊወሰን ይችላል፡፡

9/ ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም "የካፒታል ዕቃ" የሚለው ሐረግ የተመዘገበው ሰው ታክስ የሚከፈልበትን የሥራ እንቅስቃሴ በማከናወን ሂደት ለሽያጭ የሚያውለውን ወደአገር የሚገባ የካፒታል ዕቃ አይጨምርም፡፡

## ክፍል ስድስት

## ተቀናሽ የግብዓት ታክስ

### 29. ተቀናሽ እንዲሆን የተፈቀደ የግብዓት ታክስ

1/ በዚህ አዋጅ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ አቅርቦቱ ወይም ወደአገር የማስገባቱ ተግባር በተከናወነበት ጊዜ ግገርው የተፈፀመው ታክስ ለሚከፈልበት አቅርቦት መሆኑ ለተረጋገጠ ተቀናሽ ለሚደረግ ግዥ የተመዘገበ ሰው የከፈለው የግብአት ታክስ ተቀናሽ ይደረጋል፡፡

2/ የተመዘገበ ሰው በአንድ የሒሣብ ጊዜ ውስጥ ያከናወነው ተቀናሽ የሚደረግ ግዥ በከፊል ታክስ ለሚከፈልባቸው አቅርቦቶች በከፊል ደግሞ ለሌሎች አቅርቦቶች የዋለ ከሆነ ተቀናሽ የሚደረገው የግብአት ታክስ የሚሰላው በሚከተለው ቀመር መሠረት ይሆናል፡
፡

የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት 2 ሚኒስቴር

ሀ x (ሐ-ለ)/ሐ

ለዚህ ቀመር አፈፃፀም፦

ሀ) የተመዘገበው ሰው በአንድ የሒሣብ ጊዜ ውስጥ ባከናወነው በከፊል ታክስ ለሚከፈልባቸው አቅርቦቶች በከፊል ደግሞ ለሌሎች አቅርቦቶች በዋለው ተቀናሽ የሚደረግ ግዥ ላይ የከፈለው የግብአት ታክስ ጠቅላላ ድምር፣

ለ) የተመዘገበው ሰው በአንድ የሒሣብ ጊዜ ውስጥ ያከናወነው ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ጠቅላላ ዋጋ ድምር፣

ሐ) የተመዘገበው ሰው በአንድ የሒሣብ ጊዜ ውስጥ ያከናወነው ጠቅላላ አቅርቦት ዋጋ ድምር፣

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተመለከተው የለ/ሐ ክፍልፋይ፦

ሀ) 0.95 ወይም ከዚያ በላይ ከሆነ የተመዘገበው ሰው ባከናወነው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) በተመለከተው ተቀናሽ የሚደረግ ግዥ ላይ የከፈለው የግብአት ታክስ ሙሉ በሙሉ ተቀናሽ ይደረጋል።

ለ) ከ0.05 በታች ከሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) በተመለከተው ተቀናሽ የሚደረግ ግዥ ላይ የከፈለው የግብዓት ታክስ ተቀናሽ አይደረግም።

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የግብአት ታክስ ተቀናሽ የሚደረገው ተቀናሽ የሚደረገው ግዥ አቅርቦት በተከናወነበት ወይም ወደአገር በገባበት የሒሣብ ጊዜ ውስጥ መሆን አለበት።

5/ በዚህ አዋጅ መሠረት ተቀናሽ እንዲሆን የተፈቀደ የግብአት ታክስ ያለው የተመዘገበ ሰው የአንድን የሒሣብ ጊዜ የገቢ ማስታወቂያ በሚያዘጋጅበት ጊዜ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 የተመለከተው ሰነድ በእጁ የሌለ ከሆነ፣ የግብአት ታክስ ተቀናሽ ሊደረግ የማይችል ስለሆነ፣ ተቀናሹ የሚደረገው የተመዘገበው ሰው ሰነዱ በእጁ የገባበት የመጀመሪያው የሒሣብ ጊዜ ይሆናል።

6/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) አፈፃፀም ተፈላጊ የሚሆኑት ሰነዶች የሚከተሉት ናቸው፦

ሀ) ወደአገር ከገባ ዕቃ ጋር በተያያዘ ተቀናሽ የሚደረግን ግዥ በሚመለከት በኮሚሽኑ የተሰጠ የጉምሩክ ዲክላራሲዩን ወይም ወደአገር በገባው ዕቃ ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ የተከፈለ መሆኑን የሚያረጋግጥ ሌላ ሰነድ፣

ለ) ታክስ ከሚከፈልበት አቅርቦት ጋር በተያያዘ ተቀናሽ የሚደረግን ግዥ በሚመለከት ታክስ ከሚከፈልበት አቅርቦት ግዥ ጋር በተያያዘ የተጨማሪ እሴት ታክስ የተከፈለበት የታክስ ደረሰኝ፣

ሐ) በቀጥታ በገቢው ታክስ ከሚከፈልበት አቅርቦት ጋር በተያያዘ ተቀናሽ የሚደረግ ግዥን በሚመለከት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 52(4) መሠረት የአገልግሎቱ ተቀባይ ያዘጋጀው የታክስ ደረሰኝ፣

መ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 43(3) (ለ) ከተመለከተው የግብአት ታክስ ጋር በተያያዘ የተፈቀደውን የግብአት ታክስ ተቀናሽ በሚመለከት በአዋጁ አንቀጽ 43(3)(ሀ) መሠረት ሊዘጋጅ የሚገባው የዴቢት ሰነድ፣

ሠ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 44(2) የተፈቀደውን የግብአት ታክስ ተቀናሽ በሚመለከት በአዋጁ አንቀጽ 44(3)(ሀ) መሠረት ለአቅርቦቱ ተቀባይ የሚሰጠው የክሬዲት ሰነድ ቅጂ፣ ወይም

ረ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 46(3) (ለ) የተፈቀደውን የግብአት ታክስ ተቀናሽ በሚመለከት በአዋጁ አንቀጽ 46(3) (ሀ) መሠረት የሚዘጋጀው የዴቢት ሰነድ።

7/ በማናቸውም ምክንያት የተመዘገበው ሰው በአንድ የሒሣብ ጊዜ ተቀናሽ ሊደረግ የሚገባን የግብዓት ታክስ በዚያው የሒሣብ ጊዜ ባቀረበው የተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ ውስጥ ያልጠየቀ እንደሆነ፣ በሚቀጥለው የሒሣብ ጊዜ በሚያቀርበው የተጨማሪ እሴት ታክስ የሂሳብ ማስታወቂያ ውስጥ ሊጠይቅ ይችላል። ሆኖም በዚህ ዓይነት የተቀናሽ ጥያቄ ሊቀርብ የሚችለው ተቀናሹ ሊጠየቅ ከሚገባበት የሒሣብ ጊዜ ጀምሮ ከ12 ወራት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ነው።

30. <u>ተቀባይነት የሌለው የግብዓት ታክስ ተቀናሽ</u>

1/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የተመዘገበ ሰው ከዚህ በታች ለተዘረዘሩት የከፈለው የግብአት ታክስ ተቀናሽ አይደረግም።

ሀ) የተመዘገበው ሰው የመንገደኛ ተሽከርካሪ ግብይት ወይም ኪራይ ላይ የተሰማራ እና ተሽከርካሪው የተገዛው እና ፈቃድ የተሰጠው ለዚህ ታክስ የሚከፈልበት የሥራ እንቅስቃሴ ካልሆነ በስተቀር የመንገደኞች ተሽከርካሪ ግዥ ወይም ከእነዚህ ተሽከርካሪዎች መለዋወጫ ወይም ጥገና ወይም ዕድሳት ጋር በተያያዘ የከፈለው ታክስ፤

ለ) ከዚህ በታች ከተመለከቱት በስተቀር፤ የተመዘገበው ሰው ለመዝናኛ ወይም የመዝናኛ አገልግሎት ለመስጠት ያከናወነው ግዥ ከሆነ፤ እና

(i) የመዝናኛው አገልግሎት የተሰጠው ማናቸውም ሰው ታክስ የሚከፈልበትን መደበኛ የመዝናኛ አገልግሎት በሚሰጥበት ሁኔታ ከሆነ እና የመዝናኛ አገልግሎቱ ግንኙነት ላለው ሰው ወይም ለሰራተኛ የተሰጠ ካልሆነ፤

(ii) የመዝናኛ አገልግሎቱ የተሰጠው የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ስራውን ለማከናወን ወይም የቀጣሪውን ስራ ለማከናወን ከመኖሪያ ቤቱ ርቆ ባለበት ጊዜ ከሆነ፤ ወይም

(iii) ታክስ የሚከፈልበት የስራ እንቅስቃሴ የትራንስፖርት አገልግሎትን የሚያካትት ሆኖ የመዝናኛው አገልግሎት የትራንስፖርቱ አካል ሆኖ ለመንገደኞች የተሰጠ ከሆነ፤ ወይም

ሐ) የተመዘገበው ሰው የአንድ ክበብ፣ ማህበር ወይም የስፖርት፣ የማህበራዊ ወይም የመዝናኛ ባህርይ ያለው ስብስብ አባል በመሆኑ ምክንያት የተፈፀመ ግዥ::

2/ የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) (ሐ) ድንጋጌ ታክስ የሚከፈልበት የስፖርት፣ የማህበራዊ ወይም የመዝናኛ አቅርቦት የሚያከናውን የተመዘገበ ሰው እነዚህን አገልግሎቶች ለመስጠት ላከናወነው ታክስ ተቀናሽ የሚደረግበት ግብይት የግብአት ታክስ ተቀናሽ የማግኘት መብቱን የሚያሳጣ አይሆንም::

3/ በኢትዮጵያ ውስጥ ቋሚ የንግድ ሥራ ቦታ ሳይኖረው ታክስ የሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ የሚያከናውን የተመዘገበ ሰው ከሚያከናውነው ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ጋር በተያያዘ ማናቸውንም አይነት የግብአት ታክስ ተቀናሽ ሊያገኝ አይችልም:
:

4/ ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም፣

**"መዝናኛ"** ማለት ማናቸውም የምግብ፣ የመጠጥ፣ የመኝታ፣ የማዝናናት ወይም የመስተንግዶ አገልግሎት ነው::

**"የመንገደኛ ተሽከርካሪ"** ማለት ድርብ ጋቢና ያለውን ተሽከርካሪ ጨምሮ ከነአሽከርካሪው ስምንት ወይም ከዚያ በታች የሆኑ መንገደኞችን እንዲጭን ተደርጐ የተመረተ ወይም ማሻሻያ የተደረገበት ተሽከርካሪ ነው::

## 31. <u>አዲስ የተመዘገበ ሰው የግብዓት ታክስ ተቀናሽ</u>

1/ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ አዲስ የተመዘገበ ሰው በተመዘገበበት ቀን በእጁ በሚገኝ እና ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ታክስ

የሚከፈልበትን አቅርቦት ለማከናወን በሚውሉ የንግድ ዕቃዎች ወይም የካፒታል ዕቃዎች ላይ የከፈለው የግብዓት ታክስ ተቀናሽ እንዲደረግለት ለመጠየቅ ይችላል፡፡

ሀ) የተመዘገበው ሰው የንግድ ዕቃዎቹን ወይም የካፒታል ዕቃዎቹን ከተመዘገበበት ቀን በፊት ባለው የመጨረሻ ቀን በእጁ የያዘ ከሆነ፣

ለ) የተመዘገበው ሰው የንግድ ዕቃዎቹን ወይም የካፒታል ዕቃዎቹን ያገኘው ተቀናሽ በሚደረግ ግዥ ከሆነ፣

ሐ) ተቀናሽ የሚደረገው ግዥ የተፈፀመው፣

(i) የንግድ ዕቃዎችን በሚመለከት፣ ከተመዘገበበት ቀን በፊት ባለው የ6 ወር ጊዜ ውስጥ ከሆነ፣

(ii) የካፒታል ዕቃዎችን በሚመለከት፣ ከተመዘገበበት ቀን በፊት ባለው የ3 ዓመት ጊዜ ውስጥ ከሆነ፣ እና

መ) የተመዘገበው ሰው የታክሱን ባለስልጣን በሚያረካ አኳኋን ተቀናሽ ለሚደረገው ግዥ የግብአት ታክስ የከፈለ መሆኑን እና የከፈለውን ታክስ መጠን የሚያሳይ የታክስ ደረሰኝ ወይም ሌላ የሰነድ ማስረጃ ካቀረበ፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚደረገው የግብአት ታክስ ተቀናሽ የተመዘገበው ሰው ከተመዘገበበት ቀን ቀጥሎ ባለው የመጀመሪያ የሂሳብ ጊዜ መቅረብ አለበት፡፡

3/ የዚህ አዋጅ አንቀጽ 29 እና 30 ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ለንግድ እቃዎች ተፈጻሚ በሚሆንበት ሁኔታ የተመዘገበው ሰው የግብአት ታክስ ተቀናሽ ማግኘት የሚችለው በተመዘገበበት ቀን በእጁ የሚገኙ የንግድ ዕቃዎችን በገዛበት ጊዜ ለከፈለው የግብአት ታክስ ይሆናል፡፡

4/ የዚህ አዋጅ አንቀጽ 29 እና 30 ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ መሠረት የተመዘገበው ሰው በተመዘገበበት ቀን በእጁ የሚገኙ የካፒታል ዕቃዎችን በሚመለከት ለተመዘገበው ሰው ተቀናሽ የሚደረገው የግብአት ታክስ የሚሰላው በሚከተለው ቀመር መሠረት ይሆናል፡፡

$$\text{ሀ} \quad \frac{(\text{ሐ}-\text{ለ})}{\text{ሐ}}$$

ለዚህ ቀመር አፈፃፀም፡-

ሀ) የተመዘገበው ሰው የካፒታል ዕቃዎቹን በገዛበት ጊዜ የከፈለው የተጨማሪ እሴት ታክስ፣

ለ) በገቢ ግብር አዋጅ መሠረት የሚወሰነው ይህ ሰው በተመዘገበበት ቀን የካፒታል ዕቃዎቹ ያላቸው የተጣራ የመዝገብ ዋጋ፣ እና

ሐ) ለካፒታል ዕቃዎቹ የተደረገው የመጀመሪያው ወጪ::

5/ የዚህ አዋጅ አንቀጽ 29(5) ድንጋጌ በዚህ አንቀጽ መሠረት ተቀናሽ የሚደረገውን የግብዓት ታክስ በሚመለከት ተፈፃሚ አይሆንም::

## ክፍል ሰባት

## ልዩ ሁኔታዎች

### 32. ለራስ የሚደረግ አቅርቦት

1/ የዕቃዎቹን ግዥ ሲፈጽም ወይም ወደአገር ሲያስገባ የከፈለው የግብአት ታክስ ተቀናሽ የተደረገለት የተመዘገበ ሰው ዕቃዎቹን የግብአት ታክስ ተቀናሽ ለማይፈቀድለት ተግባር ያዋለ እንደሆነ ይህ ተግባር ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት እንደሆነ ተደርጎ ይወሰዳል፡ ፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በተመዘገበ ሰው የተከናወነ ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት የግብአት ታክስ ተቀናሽ ለማይፈቀድለት ተግባር በዋለ ጊዜ እንደተከናወነ ይቆጠራል::

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በተከናወነ ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት የተመዘገበው ሰው የተቀበለው የውጤት ታክስ እንደሆነ የሚቆጠረው የተመዘገበው ሰው የግብአት ታክሽ ተቀናሽ ለማይደረግበት አቅርቦት ያዋለውን ዕቃ በገዛበት ወይም ወደአገር ባስገባበት ጊዜ የከፈለው የግብአት ታክስ ነው::

4/ ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም "የግብአት ተቀናሽ የማይፈቀድለት ተግባር" ማለት ዕቃን በሚመለከት ዕቃውን ታክስ ከሚከፈልበት አቅርቦት ውጪ ለሆነ አላማ ማዋል ነው::

### 33. ያገለገሉ ዕቃዎች አቅርቦት

1/ ይህ አንቀጽ ተፈፃሚ የሚሆነው የሚከተሉት ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ ይሆናል፡ ፡

ሀ) ያገለገሉ ዕቃዎች አቅራቢ ያገለገሉ ዕቃዎችን ካልተመዘገበ ሰው በሚገዛበት ጊዜ፣

ለ) ያገለገሉ ዕቃዎች አቅራቢ ያገለገሉትን ዕቃዎች ወደአገር ያስገባ ካልሆነ፤

ሐ) ያገለገሉ ዕቃዎች አቅራቢ ያገለገሉ እቃዎችን የገዛው ከታክስ ነፃ በሆነ ወይም ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈፃሚ በሚደረግበት ግብይት ካልሆነ፣ እና

መ) ያገለገሉት ዕቃዎች አቅራቢ፡

(i) ያገለገሉትን እቃዎች በሚከፈልበት አቅርቦት በሽያጭ ወይም በለውጥ ያቀረበ ከሆነ፣ እና

(ii) ያገለገሉትን ዕቃዎች በገዛበት ጊዜ በነበሩበት ሁኔታ መልሶ የሚሸጥ ከሆነ።

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተዘረዘሩት ሁኔታዎች በተሟሉ ጊዜ ያገለገሉ ዕቃዎች አቅራቢ፣

ሀ) ያገለገሉትን ዕቃዎች የግብአት ተቀናሽ በሚፈቀድለት ግዥ እንደገዛቸው፣

ለ) ያገለገሉትን ዕቃዎች በገዛበት ጊዜ ላገለገሉት ዕቃዎች ከከፈለው ዋጋ ጋር ተመጣጣኝ በሆነ የታክስ ክፍልፋይ የግብአት ታክስ እንደከፈለ ተቆጥሮ፤ እና

ሐ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (ለ) መሠረት ያገለገሉ ዕቃዎችን አቅርቦት ባከናወነበት የሒሣብ ጊዜ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ለ) መሠረት በግብዓት ላይ ለከፈለው ታክስ የግብአት ታክስ ተቀናሽ ይፈቀድለታል።

3/ ማናቸውም አቅራቢ ላልተመዘገበ ሰው ላከናወነው አቅርቦት በከፊል ክፍያ መልክ የተቀበለው ያገለገሉ ዕቃዎችን (ከዚህ በኋላ "ዕቃን በዕቃ መገበያየት" ተብሎ የሚጠቀስ) በሚሆንበት ጊዜ ዕቃን በዕቃ በመገበያየት በተከናወነው አቅርቦት የተሸጡ ያገለገሉ ዕቃዎችን ዋጋ ለመወሰን ጥቅም ላይ የዋለው ትክክለኛ የገበያ ዋጋ አቅራቢው እነዚህን ዕቃዎች ለመግዛት ያወጣውን ወጪ ለመወሰን ጥቅም ላይ ከዋለው ትክክለኛ የገበያ ዋጋ ጋር እኩል እንደሆነ ይቆጠራል።

4/ ካልተመዘገበ ሰው ያገለገሉ ዕቃዎችን የሚገዛ ያገለገሉ ዕቃዎች አቅራቢ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ የተገለፁትን ማስረጃዎችን መያዝ አለበት።

5/ ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም፡-

**"ያገለገለ ዕቃ"** ማለት ከማይንቀሳቀስ ንብረት እና ከቁም እንስሳት በስተቀር ባልተመዘገበ ሰው በኢትዮጵያ ውስጥ ቀደም ሲል ጥቅም ላይ የዋለ የነበረ ዕቃ ነው።

"ያገለገሉ ዕቃዎች አቅራቢ" ማለት በሚገዛቸው ጊዜ በነበሩበት ሁኔታ ላይ ያሉ ያገለገሉ ዕቃዎችን ባሉበት ሁኔታ በመሸጥ እና ወይም በመለወጥ ሥራ ላይ የተሰማራ የተመዘገበ ሰው ነው፡፡

34. <u>የዕድል ሙከራ ጨዋታ አቅርቦት</u>

1/ የዕድል ሙከራ ጨዋታን በሚመለከት የተመዘገበ ሰው በሚያከናውነው በእያንዳንዱ ታክስ የሚከፈልበት ጨዋታ ሳይሆን በእያንዳንዱ የሒሣብ ጊዜ ውስጥ ካከናወነው ጨዋታ በሚገኘው ትርፍ ላይ በመመስረት የሚከፈለው የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚሰላበት ዘዴ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ይወሰናል፡፡

2/ የተመዘገበ ሰው ለዕድል ሙከራ ጨዋታው በአቅርቦትነት ባዋላቸው የዕድል ሙከራ ማጫወቻ አቅርቦቶች ላይ የከፈለው የግብአት ታክስ ተቀናሽ አይደረግም እንዲሁም አቅርቦቱን ያከናወነው የተመዘገበ ሰው ለአቅርቦቱ የታክስ ደረሰኝ መስጠት የለበትም፡፡

35. <u>ውርስ የተደረገ ተቀማጭ ገንዘብ</u>

1/ ማናቸውም አቅራቢ ከዕቃ ወይም ከአገልግሎት አቅርቦት ጋር በተያያዘ ተቀማጭ ገንዘብ የተቀበለ እና ይህም ተቀማጭ ገንዘብ በአቅራቢው ውርስ የተደረገ እንደሆነ፣ ተቀማጩ ገንዘብ ውርስ በተደረገበት ጊዜ አቅራቢው የአገልግሎት አቅርቦት እንዳከናወነ ይቆጠራል፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው የአገልግሎት አቅርቦት እና ውርስ የተደረገው የተቀማጭ ገንዘብ አቅርቦት አንድ ዓይነት ባህሪ ያላቸው እንደሆኑ ተደርገው ይወሰዳሉ፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው የአገልግሎት አቅርቦት እሴት የሚከተለው ይሆናል፡፡

ሀ) ተቀማጩ ገንዘብ ውርስ በተደረገ ጊዜ የተመዘገበ ሰው የነበረን አቅራቢ በሚመለከት፣ በተወረሰው ተቀማጭ ገንዘብ መጠን ላይ ከተቀማጩ ገንዘብ ጋር እኩል የሆነ የገንዘብ መጠን ሲቀነስ እና በታክሱ ክፍልፋይ ሲበዛ፣ ወይም

ለ) ሌላ ማናቸውንም አቅራቢ በሚመለከት ውርስ የተደረገው ተቀማጭ ገንዘብ መጠን፡
፡

4/ ይህ አንቀጽ ለዕቃ ማሸጊያነት ለሚውሉ ዕቃዎች የሚሰጠውን ተቀማጭ ገንዘብ አይጨምርም፡፡

36. <u>የሙበት፤ የምርጫ እና የቫውቸር አቅርቦት</u>

1/ ይህ አንቀጽ ተፈፃሚ የሚሆነው የሚከተሉት ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ ነው፡፡

ሀ) የመብት፣ የምርጫ ወይም የቫውቸር አቅርቦት ሲኖር፣ እና

ለ) መብቱን ወይም ምርጫውን በመጠቀም ሂደት ወይም ለተከታታይ አቅርቦት ክፍያ ቫውቸሩን በሙሉ ወይም በከፊል በመመለስ ሂደት ሌላ አቅርቦት ("ተከታይ አቅርቦት") ተፈጽሞ ከሆነ፡፡

2/ ይህ አንቀጽ ተፈፃሚ በሚሆንበት ጊዜ የመብት፣ የምርጫ ወይም የቫውቸር አቅርቦቱ ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ከሆነ፣ ለተከታይ አቅርቦት የሚፈፀመው ክፍያ ለተከታዩ አቅርቦት ወይም ከመብቱ ወይም ምርጫው አቅርቦት ጋር በተያያዘ በተጨማሪነት ከሚፈፀመው ክፍያ መጠን ሊበልጥ አይችልም፡፡

3/ ይህ አንቀጽ ተፈፃሚ በሚሆንበት ጊዜ የመብት፣ የምርጫ ወይም የቫውቸር አቅርቦቱ ታክስ የማይከፈልበት አቅርቦት ከሆነ እና ተከታይ አቅርቦቱ ብቻ ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ከሆነ ለተከታዩ አቅርቦት የሚፈፀመው ክፍያ ለመብቱ፣ ለምርጫው ወይም ለቫውቸሩ አቅርቦት የተፈፀመን ክፍያ ይጨምራል፡፡

4/ ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም ቫውቸርን ማዘጋጀት የአገልግሎት አቅርቦት እንደሆነ ይቆጠራል፡

5/ ይህ አንቀጽ የዚህ አዋጅ አንቀጽ 37 ተፈጻሚ የሚሆንበትን ቫውቸር በሚመለከት ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

## 37. ላልተገለፁ አቅርቦቶች የሚውል ቫውቸር

1/ የሚከተሉት ሁኔታዎች ተሟልተው ከተገኙ ቫውቸር ማዘጋጀት ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት እንደሆነ አይቆጠርም፦

ሀ) ቫውቸሩ በእጁ የሚገኝ ሰው ቫውቸሩን በማስረከብ እስከተወሰነ የገንዘብ መጠን ድረስ ዋጋ ያላቸውን ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች የሚያገኝበት ከሆነ፣

ለ) ቫውቸሩን መጠቀም የሚቻልባቸው እቃዎች እና አገልግሎቶች የተለየ የተጨማሪ እሴት ታክስ አፈጻጸምን የሚከተሉ ከሆነ እና

ሐ) ቫውቸሩ የተወሰነ የገንዘብ መጠን ይዞ የሚታተም ከሆነ፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ቫውቸር ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈጻሚ ከሚደረግበት በስተቀር የተመዘገበ ሰው ለሚያከናውነው አቅርቦት በክፍያ መልክ የሚሰጥ ከሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (ሐ) የተመለከተው የገንዘብ መጠን ሁለት መልኮች እንዳሉት ሆኖ ይቆጠራል፡፡

ሀ) ለአቅርቦቱ ሙሉ ዋጋ ወይም ከፊል ዋጋ ክፍያ የሚውለው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (ሐ) በተመለከተው የገንዘብ መጠን ላይ ተሰልቶ ሊከፈል የሚገባው የታክስ ክፍልፋይ መጠን ተቀናሽ ይደረጋል፣ እና

ለ) በአቅርቦቱ ላይ የሚከፈለው የተጨማሪ እሴት ታክስ በሙሉ ወይም ከፊሉ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (ሐ) በተመለከተው የገንዘብ መጠን ላይ በማስከፈያው ታክስ ክፍልፋይ መሠረት እንዲሰላ ይደረጋል፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) የተጠቀሰው ቫውቸር በሙሉ ወይም በከፊል ጥቅም ላይ ከመዋሉ በፊት ጊዜው ያለፈ እንደሆነ፤

ሀ) በቫውቸሩ ጊዜ ማለፍ የቫውቸሩ አቅራቢ ቫውቸሩ ለተሰጠው ሰው የአገልግሎት አቅርቦት እንዳከናወነ ይቆጠራል፤

ለ) በዚህ ንኡስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) የተመለከተው አገልግሎት አቅርቦት ተፈጽሟል የሚባለው የቫውቸሩ መጠቀሚያ ጊዜ ባለፈበት ቀን ነው፤እና

ሐ) በዚህ ንኡስ አንቀጽ (ሀ) የተመለከተው አቅርቦት ዋጋ፤

(i) የቫውቸሩ የመጠቀሚያ ጊዜ ባለፈበት ቀን የተመዘገበ ሰው የነበረን አቅራቢ በሚመለከት ጥቅም ላይ ካልዋለው የቫውቸሩ ዋጋ ላይ፤ ጥቅም ላይ ያልዋለው የቫውቸሩ ዋጋ ሲባዛ በታክስ ክፍልፋይ የሚገኘው ወጤት ተቀንሶ፤ ወይም

(ii) ለሌላ ማናቸውም አቅራቢ ጥቅም ላይ ያልዋለው የቫውቸሩ ዋጋ፡፡

4/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) ተፈፃሚ የሚሆነው የሚከተሉት ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ ይሆናል፡-

ሀ) የተመዘገበ ሰው ያለአንዳች ክፍያ ቫውቸር ሲሰጥ፣

ለ) ቫውቸሩ የተሰጠው ሰው ቫውቸሩን በመጠቀም ዕቃዎችንና አገልግሎቶችን በቅናሽ ዋጋ ከሌላ አቅራቢ መግዛት የሚችል ሲሆን፣ እና

ሐ) ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈፃሚ ከሚሆንበት በስተቀር ቫውቸሩ ታክስ የሚከፈልበትን አቅርቦት ለመግዛት የሚውል በሚሆንበት ጊዜ፡፡

5/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) የተዘረዘሩት የተሟሉ በሚሆንበት ጊዜ፤ የአቅርቦቱ ዋጋ እንደሆነ የሚወሰደው የቫውቸሩን የገንዘብ ዋጋ በታክስ ማስከፈያው መጣኔ በማባዛት የሚገኘውን ውጤት ከቫውቸሩ ዋጋ ላይ በመቀነስ የሚገኘውን ሒሳብ ይጨምራል፡፡

6/ አቅራቢው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) የተመለከተውን ቫውቸር ለተመዘገበው ሰው በሚመልስበት ጊዜ የተመዘገበው ሰው ለአቅራቢው በከፈለው የገንዘብ መጠን ልክ የግብዓት ታክስ ተቀናሽ ያገኛል፡፡

7/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (6) መሠረት ተቀናሽ የሚደረገው የግብአት ታክስ ለአቅራቢው የተከፈለው የገንዘብ መጠን በታክሱ ክፍልፋይ ሲባዛ የሚገኘው ውጤት ሲሆን፣ የግብዓት ታክሱ ተቀናሽ የሚደረገው ለአቅራቢው ክፍያ በተፈፀመበት የሒሣብ ጊዜ ይሆናል፡፡

## 38. <u>በቅድመ - ክፍያ የሚቀርብ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት</u>

1/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ አንቀጽ ተፈፃሚ የሚሆነው፡-

ሀ) የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት አቅራቢ የቅድሚያ ክፍያ በማስከፈል የሚሰጠውን የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት፣ ወይም

ለ) በቅድመ-ክፍያ የሚቀርብን የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት በማቅረብ ረገድ አከፋፋይ፣ ወኪል ወይም የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት አገናኝ ሆኖ የሚሰራ ሰው የሚያቀርበውን አገልግሎት በሚመለከት ነው፡፡

2/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ አንድ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት አቅራቢ ለሌላ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት አቅራቢ የሚሰጠውን እና በዚህ አዋጅ መሠረት ከሚከናወን መደበኛ የሥራ እንቅስቃሴ ጋር የተገናኘን አቅርቦት በሚመለከት ተፈፃሚ አይሆንም፡፡

3/ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት አቅራቢ በቅድመ - ክፍያ የሚቀርብን የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ከችርቻሮ መሸጫ ዋጋ በታች በሆነ የቅናሽ ዋጋ ለቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት አገናኝ በሚያቀርብ ጊዜ የአቅርቦቱ ዋጋ የሚሰላው የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት አገናኙ አቅርቦቱን በችርቻሮ መሸጫ ዋጋ እንደገዛ ተቆጥሮ ነው፡፡

4/ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት አገናኝ በቅድመ - ክፍያ የሚቀርብን የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት የሚገዛ እና የሚሸጥ በሚሆንበት ጊዜ፡-

ሀ) የሚፈፀመው ግዥ እንዳልተፈፀመ፣እና

ለ) የሚሸጠው አገልግሎት እንዳልቀረበ፣ ተደርጎ ይቆጠራል፡፡

5/ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት አቅራቢ በቅድመ - ክፍያ የሚቀርብን የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ወኪል ሆኖ በሚሠራ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት አገናኝ አማካኝነት

የሚያቀርብ በሚሆንበት ጊዜ ለቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎቱ ከሚከፈለው ዋጋ ላይ ለአገናኙ የሚከፈለው ኮሚሽን ተቀናሽ አይደረግም::

## 39. የሠራተኞች ጥቅማ ጥቅም

1/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ የተመዘገበው ሰው ሠራተኞችን ቀጥሮ የሚያሰራ ከሆነ እና ታክስ የሚከፈልበትን አቅርቦት ለሠራተኞች የሚሰጥ ጥቅማ ጥቅም አንድ ክፍል በማድረግ የሚያቀርብ ከሆነ፣ አቅርቦቱ ክፍያን በመቀበል በትክክለኛ የገበያ ዋጋ እንደተፈፀመ ይቆጠራል::

2/ አሠሪው ለሠራተኞቹ ለሚያከናውነው አቅርቦት እንዲውል በፈፀመው ተቀናሽ የሚሆን ግዢ ላይ የታክስ ተቀናሽ ሊያገኝ የማይችል ከሆነ አቅርቦቱን ለሠራተኞቹ ያለክፍያ እንደፈፀመ ይቆጠራል::

## 40. ጠቅላላ መድን ስራ

1/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የውሉ አካል ቢሆንም ባይሆንም የተመዘገበ ሰው ታክስ የሚከፈልበትን የሥራ እንቅስቃሴ በማከናወን ሂደት በደረሰ ጉዳት ምክንያት የጠቅላላ መድን ካሣ የተቀበለ እንደሆነ፣ የዚህ ዓይነቱ ክፍያ የተመዘገበው ሰው ታክስ የሚከፈልበትን የሥራ እንቅስቃሴ በማከናወን ሂደት ለአገልግሎቱ አቅርቦት እንደተከፈለው ዋጋ ይቆጠራል::

2/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የሚከተሉትን በተመለከተ ተፈፃሚ አይሆንም:-

ሀ) ክፍያ የተፈፀመበት የጠቅላላ የመድን ውል አቅርቦት ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነፃ ወይም ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈፃሚ የሚደረግበት ከሆነ፣ ወይም

ለ) የካሣ ክፍያው የተፈፀመው በሰው አካል ላይ በደረሰ ጉዳት ምክንያት ከሆነ::

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የተከናወነው አቅርቦት የተመዘገበው ሰው ክፍያውን በተቀበለ ቀን እንደተፈፀመ የሚቆጠር ሲሆን፣ የአቅርቦቱ ዋጋ ነው የሚባለው የተመዘገበው ሰው ከተቀበለው ገንዘብ ላይ የታክሱ ክፍልፋይ የገንዘብ መጠን ከተቀነሰ በኋላ የሚቀረው ሒሣብ ነው::

4/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) እንደተጠበቀ ሆኖ የተመዘገበ የኢንሹራንስ ኩባንያ በአንድ ሌላ ሰው ላይ በደረሰ ጉዳት ምክንያት በጠቅላላ መድን ውል መሠረት የካሣ ክፍያ የከፈለ እንደሆነ፣ ከዚህ በታች የተመለከቱት ተሟልተው ሲገኙ ከተከፈለው የካሣ ክፍያ ውስጥ የታክሱ ክፍልፋይ የግብአት ታክስ ተቀናሽ እንዲሆን ይደረጋል::

ሀ) የጠቅላላ መድን አቅርቦት ዜሮ የማስከፈያ መጣኔ ተፈፃሚ ከሚደረግበት ውጪ ያለ ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ከሆነ፣ እና

ለ) ክፍያው የተፈፀመው በኢትዮጵያ ነዋሪ ለሆነ ወይም በኢትዮጵያ ነዋሪ ላልሆነ የተመዘገበ ሰው ከሆነ፣ እና

ሐ) ክፍያው የተፈፀመው የኢንሹራንስ ኩባንያው ለሚያከናውነው አቅርቦት ወይም ወደአገር የማስገባት ተግባር ካልሆነ።

5/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት የግብአት ታክስ ተቀናሽ የሚደረገው የኢንሹራንስ ኩባንያው ክፍያውን በፈፀመበት የሒሣብ ጊዜ ነው።

6/ የተመዘገበው የኢንሹራንስ ኩባንያ ለሞራል ወይም በቅጣት መልክ ከሚከፈል ካሣ በስተቀር በአጠቃላይ የመድኑ ውሉ መሠረት በተፈፀመ መዳረግ ምክንያት የከፈለውን ካሣ መልሶ የተቀበለ እና በዚህ መልክ መልሶ በተቀበለው ገንዘብ ላይ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) ድንጋጌ ተፈፃሚ የሚሆን ከሆነ፣ መልሶ የተቀበለው ገንዘብ የተመዘገበው የኢንሹራንስ ኩባንያ ታክስ የሚከፈልበትን የሥራ እንቅስቃሴ በማከናወን ሂደት ካቀረበው አገልግሎት የተቀበለው ገንዘብ እንደሆነ ይቆጠራል።

7/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (6) የተመለከተው አቅርቦት የኢንሹራንሱ ኩባንያ የከፈለውን የካሣ ገንዘብ መልሶ በተቀበለበት ቀን እንደተከናወነ ይቆጠራል።

8/ ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም፡-

**"ጠቅላላ መድን ስራ"** የሚለው ሐረግ በመድን ስራ አዋጅ ቁጥር 746/2004 (እንደተሻሻለ) የተሰጠውን ትርጉም የሚይዝ ሲሆን፤ ሆኖም በዚያው አዋጅ በተተረጎመው መሠረት አነስተኛ የመድን ንግድ ስራ ማከናወንን አይጨምርም፤ እና

**"የጠቅላላ መድን ስራ ውል"** ማለት የጠቅላላ መድን የንግድ ሥራን በማከናወን ሂደት የተፈፀመ የመድን ውል ነው።

## 41. <u>በወኪሎች ወይም ለወኪሎች የተፈፀመ አቅርቦት</u>

1/ ማናቸውም ወኪል ወካዩን (ከዚህ በኋላ "ወካይ") በመወከል የሚያከናውነው የዕቃ ወይም የአገልግሎት አቅርቦት በወካዩ የተከናወነ አቅርቦት እንደሆነ ተደርጎ ይቆጠራል፡

2/ ለታክስ አስተዳደር አዋጅ አፈፃፀም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሰው ወኪል የታክስ እንደራሴ እንደሆነ ይቆጠራል።

3/ ወኪል ለሆነ ሰው የሚቀርብ ዕቃ ወይም አገልግሎት ለወካዩ የተደረገ አቅርቦት እንደሆነ ይቆጠራል።

4/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (3) ድንጋጌ ወኪሉ ለወካዩ የሚሰጠውን አገልግሎት በሚመለከት ተፈፃሚ አይሆንም።

## 42. <u>የባለዕዳ ዕቃ አቅርቦት</u>

1/ የተመዘገበ ቢሆንም ባይሆንም ባለዕዳ ለባለገንዘብ መክፈል የሚገባውን ዕዳ በሙሉ ወይም በከፊል ለማስከፈል ባለገንዘቡ የባለዕዳውን ዕቃ ለሦስተኛ ወገን የሸጠ እንደሆነ፣

ሀ) ለሦስተኛ ወገን የተከናወነው ሽያጭ በባለዕዳው የተፈፀመ እንደሆነ ተደርጎ የሚቆጠር ሲሆን፣ የግብይቱ ባህሪ በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት የሚወሰን ይሆናል፣ እና

ለ) ባለዕዳው ለባለገንዘቡ አቅርቦቱ ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነፃ መሆኑን በጽሑፍ እስካላረጋገጠለት ድረስ ባለገንዘቡ በዕቃው ላይ ሊከፈል የሚገባውን ታክስ የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)(ለ) መሠረት ባለዕዳው ለባለገንዘቡ የሚሰጠው ማረጋገጫ አቅርቦቱ ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነፃ የተደረገበትን ምክንያት የሚገልጽ መሆን አለበት፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)(ለ) መሠረት ማረጋገጫ ያልተሰጠው ባለገንዘብ በእጁ ያለውን ማናቸውንም መረጃ መሠረት በማድረግ አቅርቦቱ በባለዕዳው ቢከናወን ኖሮ ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነፃ ይሆን እንደነበር አድርጎ መውሰድ ይችላል፡፡

4/ የባለዕዳውን ዕቃ የሚሸጥ ባለገንዘብ የከፈለው የግብአት ታክስ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)(ለ) መሠረት ከሚሰበሰበው የውጤት ታክስ ላይ እንዲቀነስለት ማድረግ አይችልም፡፡

5/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የተጨማሪ እሴት ታክስ የመክፈል ግዴታ ያለበት ባለገንዘብ ፡

(ሀ) በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ በሚወሰነው ጊዜ እና አኳኋን መሠረት የሰበሰበውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቅ እና ገቢ ማድረግ፤ እና

(ለ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 55(2) የተደነገገው ቢኖርም፤ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ የተመለከተውን ዝርዝር የያዘ የታክስ ደረሰኝ የአገልግሎቱ ተቀባይ ለሆነው የተመዘገበ ሰው መስጠት፤ አለበት፡፡

6/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌ በታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀጽ 40 መሠረት ባለገንዘቡን ወክሎ የሚሠራን ንብረት ተረካቢን በሚመለከትም ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ስምንት

## ማስተካከያ ስለማድረግ

43. <u>የተከፈለው የተጨማሪ እሴት ታክስ መጠን በማነሱ ምክንያት የሚደረግ ማስተካከያ</u>

1/ ይህ አንቀጽ ተፈፃሚ የሚሆነው:-

ሀ) የተመዘገበ ሰው አቅርቦት ሲያከናውን፣

ለ) በአቅርቦቱ ላይ ማስተካከያ ማድረግ የሚያስገድድ ሁኔታ ሲፈጠር፣ እና

ሐ) ማስተካከያ ማድረግ የሚያስገድድ ሁኔታ በመፈጠሩ ምክንያት የተመዘገበው ሰው በአቅርቦቱ ላይ ሊከፍል የሚገባው ትክክለኛው የተጨማሪ እሴት ታክስ መጠን ለታክስ ባለስልጣኑ ገቢ ለማድረግ ከተሰበሰበው የገንዘብ መጠን የበለጠ በሚሆንበት ጊዜ ነው::

2/ ይህ አንቀጽ ተፈፃሚ በሚሆንበት ጊዜ፣ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)(ሐ) መሠረት በተጨማሪነት የተሰበሰበው ታክስ ማስተካከያው በተደረገበት የሒሣብ ጊዜ የአቅራቢው የውጤት ታክስ ሆኖ ይወሰዳል::

3/ ይህ አንቀጽ ተፈፃሚ የሚሆነው በተመዘገበ ሰው ላይ በሚሆንበት እና አቅራቢው ለገዥው ዋነኛውን የታክስ ደረሰኝ የሰጠ በሚሆንበት ጊዜ፣

ሀ) አቅራቢው በአቅርቦቱ ላይ በተጨማሪነት የተከፈለውን የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚያሳይ የዴቢት ሰነድ ለገዥው መስጠት አለበት፣

ለ) የአዋጁ አንቀጽ 30 ተፈጻሚ የማይደረግ ሆኖ፤ ገዥው አቅርቦቱን ታክስ ለሚከፈልበት አቅርቦት እስካዋለው ድረስ በዴቤት ሰነዱ ለተመለከተው በተጨማሪነት ለተከፈለው የተጨማሪ እሴት ታክስ የግብአት ተቀናሽ ማግኘት፤ ይፈቀድለታል፤ እና

ሐ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ለ) በተመለከተው የገንዘብ መጠን ገዥው የዴቢት ሰነዱን በተቀበለበት የሒሣብ ጊዜ የግብዓት ታክስ ተቀናሽ ማግኘት አለበት::

44. <u>የተከፈለው የተጨማሪ እሴት ታክስ በመብዛቱ ምክንያት የሚደረግ ማስተካከያ</u>

1/ ይህ አንቀጽ ተፈፃሚ የሚሆነው:-

ሀ) የተመዘገበ ሰው አቅርቦት ሲያከናውን፣

ለ) በአቅርቦቱ ላይ ማስተካከያ ማድረግ የሚያስገድድ ሁኔታ ሲፈጠር፣ እና

ሐ) ማስተካከያ ማድረግ የሚያስገድድ ሁኔታ በመፈጠሩ ምክንያት የተመዘገበው ሰው ለታክሱ ባለስልጣን ገቢ ለማድረግ የሰበሰበው የተጨማሪ እሴት ታክስ በአቅርቦቱ ላይ ሊከፈል ከሚገባው ትክክለኛው የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚበልጥ ሆኖ ሲገኝ ነው::

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ አንቀጽ ተፈፃሚ በሚሆንበት ጊዜ አቅራቢው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)(ሐ) የተመለከተው በብልጫ የከፈለው ታክስ ድርጊቱ በተፈፀመበት የሒሣብ ጊዜ ውስጥ የግብአት ታክስ ተቀናሽ ሆኖ ይያዛል፡፡

3/ ይህ አንቀጽ ተፈፃሚ የሚሆንበት ግኘር ፈፃሚው የተመዘገበ ሰው በሚሆንበት እና አቅራቢው ለገኘሪው ዋነኛውን የታክስ ደረሰኝ የሰጠ በሚሆንበት ጊዜ፣

ሀ) አቅራቢው በአቅርቦቱ ላይ ተከፋይ ሊሆን የሚገባውን የተጨማሪ እሴት ታክስ የቀነሰበትን መጠን የሚያሳይ የክሬዲት ሰነድ ለገኘሪው መስጠት፣ እና

ለ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) የተመለከተው የገንዘብ መጠን ገኘሪው የክሬዲት ሰነድ በተቀበለበት የሒሣብ ጊዜ የውጤት ታክስ ሆኖ መያዝ አለበት፡፡

4/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ተፈፃሚ የሚሆንበት ገዢ ያልተመዘገበ ሰው በሚሆንበት ጊዜ አቅራቢው ለገዢው በብልጫ የተከፈለውን የተጨማሪ እሴት ታክስ በጥሬ ገንዘብ እስከሚመልስ ወይም ገኘሪው ለአቅራቢው ሊከፍል ለሚገባው ሌላ ሒሣብ ማካካሻ እስከሚያውል ድረስ በዚህ አንቀጽ የተመለከተውን የግብአት ታክስ ተቀናሽ ሊያገኝ አይችልም፡፡

## 45. ሊሰበሰብ ለማይችል ዕዳ ስለሚደረግ ማስተካከያ

1/ ይህ አንቀጽ ተፈፃሚ የሚሆነው የሚከተሉት ተሟልተው ሲገኙ ይሆናል፡፡

ሀ) የተመዘገበው ሰው ባከናወነው ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ላይ ለታክሱ ባለስልጣን የውጤት ታክስ ገቢ አድርጎ ከሆነ፣ እና

ለ) ለአቅርቦቱ ሊከፈል የሚገባው ዋጋ በፋይናንስ ሪፖርት አዋጅ በተመለከተው የፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ ደረጃ መሰረት በሙሉ ወይም በከፊል በተመዘገበው ሰው የሒሣብ መግለጫ ውስጥ ሊሰበሰብ የማይችል ዕዳ ተብሎ የተያዘ ከሆነ፣እና

(ሐ) ዕዳውን ለማስከፈል የህግ እርምጃ የተወሰደ ቢሆንም ዕዳው ሊከፈል የማይችል ሆኖ ከተገኘ፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከቱት ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የተመዘገበው ሰው ሊሰበሰብ የማይችል ዕዳ ነው ከተባለው አቅርቦት ጋር በተያያዘ ለታክሱ ባለሥልጣን ገቢ ባደረገው የውጤት ታክስ መጠን የግብአት ታክስ ተቀናሽ ያገኛል፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የግብዓት ታክስ ተቀናሽ ሊደረግ የሚችለው ከሚከተሉት በዘገየው ቀን ነው፤

የገንዘብ የሪፎርም አስተዳደር አገልግሎት

ሀ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ተሟልተው በተገኙበት ቀን፤ ወይም

ለ) የተመዘገበው ሰው በአቅርቦቱ ላይ የሚከፈለውን የውጤት ታክስ ለታክሱ ባለስልጣን ገቢ ካደረገበት የሂሳብ ጊዜ መጨረሻ ጀምሮ ከሚቆጠር የ12 ወራት ጊዜ በኋላ፡፡

4/ ይህ አንቀጽ ተፈፃሚ የሚሆንበትን ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት የገዛው ሰው የተመዘገበ ሰው ከሆነ እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት የግብአት ታክስ ተቀናሽ በሚደረግበት ጊዜ ያለ ከሆነ፣ የግብአት ታክስ ተቀናሽ ሊደረግ የሚችለው አቅራቢው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት በሚሰላው ሊሰበሰብ የማይችል ዕዳ ላይ የተከፈለውን የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚያሳይ የክሬዲት ሰነድ የሰጠ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡

5/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት የክሬዲት ሰነድ የተሰጠው ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ገዥ በክሬዲት ሰነዱ ለተገለፀው የተጨማሪ እሴት ታክስ የግብአት ታክስ ተቀናሽ የጠየቀ ከሆነ፣ በክሬዲት ሰነዱ የተገለፀውን የተጨማሪ እሴት ታክስ የክሬዲት ሰነዱ በተሰጠበት የሒሣብ ጊዜ ውስጥ በገዥው የሚከፈል የውጤት ታክስ እንደሆነ አድርጎ መያዝ አለበት፡፡

## 46. መልሶ ሊሰበሰብ ከማይችል ዕዳ ውስጥ የተሰበሰበ ገንዘብ

1/ የተመዘገበ ሰው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 45 መሠረት የግብአት ታክስ ተቀናሽ ያገኘበትን አቅርቦት ዋጋ በሙሉ ወይም በከፊል መልሶ የሰበሰበ እንደሆነ፣ ሊሰበሰብ የማይችለውን ዕዳ መልሶ በሰበሰበበት የሒሣብ ጊዜ ከዚህ በታች በተመለከተው ቀመር መሠረት የውጤት ታክስ እንደተቀበለ ይቆጠራል፡፡

$$ሀ \times {}^{ለ}/_{ሐ}$$

ለዚህ ቀመር አፈፃፀም

ሀ) በዚህ አዋጁ አንቀጽ 45(2) መሠረት የተፈቀደው የግብአት ታክስ ተቀናሽ የገንዘብ መጠን፣

ለ) መልሶ የተሰበሰበው ሊሰበሰብ የማይችል ዕዳ፣

ሐ) ከሒሣብ መዝገብ የተሰረዘው ሊሰበሰብ የማይችል ዕዳ፣

2/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ተፈፃሚ የሚሆነው የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲሟሉ ይሆናል፡-

ሀ) የአዋጅ አንቀጽ 45 ድንጋጌ ተፈፃሚ የተደረገው ታክስ ለሚከፈልበት አቅርቦት ከሆነ (ከዚህ በኋላ "ዋንኛው ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት")፣

ለ) ቀጥሎም የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ተፈፃሚ የሚሆነው የዋንኛው ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት አቅራቢ ከዋንኛው ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ገገር በተቀበለው የገንዘብ መጠን ላይ ሲሆን፣ እና

ሐ) የዋነኛው ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ገገር ዋነኛው ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት በተከናወነበት ጊዜ እና በዚህ አንቀጽ ተራ ፊደል (ለ) በተጠቀሰው መሠረት ሊሰበሰብ የማይችለው ዕዳ መልሶ በተሰበሰበበት ጊዜ የተመዘገበ ሰው ከሆነ።

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ተሟልተው የተገኙ ከሆነ፡-

ሀ) አቅራቢው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሰውን የውጤት ታክስ የገንዘብ መጠን በመግለፅ ለገገርው የዴቢት ሰነድ መስጠት፣ ወይም

ለ) ገገርው የመጀመሪያውን ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ታክስ ለሚከፈልበት አቅርቦት ያዋለው እና የዚህ አዋጅ አንቀጽ 30 ተፈፃሚ የማይደረግ ከሆነ በዚህ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) ለተገለፀው የውጤት ታክስ የግብአት ታክስ ተቀናሽ እንዲያገኝ መደረግ፣ አለበት።

4/ የተመዘገበው ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3)(ሀ) መሠረት የዴቢት ሰነድ በተቀበለበት የሒሣብ ጊዜ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3)(ለ) መሠረት የግብአት ታክስ ተቀናሽ ማግኘት አለበት።

## ክፍል ዘጠኝ

## <u>የተጨማሪ እሴት ታክስን የተጣራ ተከፋይ ሒሣብ ስለማስላት</u>

### 47. <u>በአንድ የሒሣብ ጊዜ የተጣራ ተከፋይ የሚሆን የተጨማሪ እሴት ታክስ</u>

የተመዘገበ ሰው በአንድ የሒሣብ ጊዜ ሊከፍል የሚገባው የተጣራ የተጨማሪ እሴት ታክስ በሚከተለው ቀመር መሠረት ይሰላል።

ሀ-ለ

ለዚህ ቀመር አፈፃፀም፡-

ሀ) የሚከተሉት ድምር ይሆናል።

(i) በአንድ የሒሣብ ጊዜ የተመዘገበው ሰው ካከናወነው ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ላይ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 62(3) መሠረት ተቀናሽ ሊደረግ የሚገባው ከተከፋይ ሒሣብ ላይ የሚቀነስ የተጨማሪ እሴት ታክስ ከተቀነሰ በኋላ ታክስ በሚከፈልበት አቅርቦት ላይ የሚሰበሰበው የውጤት ታክስ ጠቅላላ ድምር፣

(ii) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 8(1) ፊደል ተራ (ሐ) እና አንቀተሰ 8(8) መሠረት የተመዘገበው ሰው በሂሳብ ጊዜው በቀረበለት በገቢው ተይዞ ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ላይ በቀጥታ ሊከፍል የሚገባው የተጨማሪ እሴት ታክስ ጠቅላላ ድምር፣

(iii) በዚህ አዋጅ መሠረት በሂሳብ ጊዜው የተመዘገበው ሰው የውጤት ታክስ ሆኖ የሚወሰደው ሂሳብ ጠቅላላ ድምር፤ እና

(iv) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 28 መሠረት በሂሳብ ጊዜው የተፈቀደ የተመዘገበው ሰው ወደአገር ባስገባቸው የካፒታል ዕቃዎች ላይ የሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ::

(ለ) የሚከተሉት ድምር ይሆናል::

(i) የግብአት ታክስ ተቀናሽ ሊደረግላቸው ለሚችል በሒሣብ ጊዜው የተመዘገበው ሰው ለገዛቸው ተቀናሽ የሚሆኑ ግዥዎች የከፈለው የግብአት ታክስ ጠቅላላ ድምር፣ እና

(ii) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 31(1)፣ 33(2) (ሐ)፣ 37(6)፣ 40(4)፣ 43(3)፣ 44(2)፣ 45(2)፣ 46(3) እና 48(1) ወይም በተጨማሪ እሴት ታክስ ደንብ በተመለከተው መሠረት በአንድ የሒሣብ ጊዜ ለተመዘገበው ሰው ተቀናሽ እንዲሆን የተፈቀደ የግብዓት ታክስ::

## ክፍል አሥር

## ተመላሽ

## 48. በብልጫ የተከፈለን የግብዓት ታክስ ወደፊት ስለማሸጋገር

1/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) እና በዚህ አዋጅ አንቀጽ 49 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፤ በአንድ የተመዘገበ ሰው የሒሣብ ጊዜ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 47 የተመለከተው ቀመር “ለ” ሂሳብ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵፯ በተመለከተው ቀመር “ሀ” ሒሣብ በልጦ የተገኘ እንደሆነ፣ በልጦ የተገኘው የገንዘብ መጠን ወደፊት እንዲሸጋገር ተደርጐ የሚቀጥለው የሒሣብ ጊዜ የተመዘገበው ሰው የግብአት ታክስ ሆኖ ተቀናሽ ይደረጋል:: በሚቀጥለው የሒሣብ ጊዜ ተቀናሽ ያልተደረገው በብልጫ የተገኘው ማናቸውም ሒሣብ፣ ወደሚቀጥለው የሒሣብ ጊዜ እንዲሸጋገር ተደርጐ በዚያ የሒሣብ ጊዜ የግብአት ታክስ ተቀናሽ እንዲሆን ይደረጋል:: በዚህ መንገድ በብልጫ የተገኘው

የግብአት ታክስ ተመላሽ ሙሉ በሙሉ ተቀናሽ እስከሚሆን ድረስ ወደሚቀጥለው የሒሣብ ጊዜ እንዲሸጋገር ይደረጋል።

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የተመዘገበው ሰው በብልጫ የከፈለው እና ከአንድ የሒሣብ ጊዜ በላይ እንዲሸጋገር የተደረገ ሒሣብ ያለው እንደሆነ፣ ቀደም ሲል እንዲሸጋገር የተደረገው በብልጫ የተከፈለው ሒሣብ በቅድሚያ እንዲቀነስ ይደረጋል።

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም የተመዘገበ ሰው በአንድ የሒሣብ ጊዜ ውስጥ ያለው በብልጫ የከፈለው ታክስ ለስድስት የሒሣብ ጊዜ ያህል የተሸጋገረ ቢሆንም ሙሉ በሙሉ ተቀናሽ ያልተደረገ ከሆነ፣ የተመዘገበው ሰው የፀደቀ ቅጽን በመጠቀም ተቀናሽ ያላደረገው የገንዘብ መጠን ተመላሽ እንዲደረግለት ለታክሱ ባለሥልጣን ሊያመለክት ይችላል።

4/ የተመዘገበው ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት ማመልከቻ ያቀረበ እንደሆነ እና የታክሱ ባስለልጣን የቀረበው ጥያቄ ተገቢ መሆን ያለመሆኑን አጣርቶ፣ የተመላሽ ጥያቄ ማመልከቻው በቀረበለት በ45 ቀናት ውስጥ ተመላሹን ገንዘብ መክፈል አለበት።

5/ በዚህ አንቀጽ መሠረት የተመዘገበ ሰው የሚያቀርበው የተመላሽ ጥያቄ ስድስተኛው የሒሣብ ጊዜ በተጠናቀቀ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ መቅረብ አለበት።

6/ የተመዘገበው ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) መሠረት ጥያቄውን ካላቀረበ ተመላሽ የማግኘት መብቱን እንደተወ ይቆጠራል።

## 49. <u>ወደፊት ሳይሸጋገር ተመላሽ የሚደረግ በብልጫ የተከፈለ የግብዓት ታክስ</u>

1/ የተመዘገበው ሰው በአንድ የሒሣብ ጊዜ ካከናወነው አቅርቦት ዋጋ ውስጥ 50 በመቶ ወይም ከዚያ በላይ ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈፃሚ የሚደረግበት ከሆነ፣ የተመዘገበው ሰው የሒሣብ ጊዜውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ካስታወቀበት ጊዜ ጀምሮ በሚቆጠር የአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የታክሱ ባለሥልጣን በሒሣብ ጊዜው በብልጫ የተከፈለውን የግብአት ታክስ ተመላሽ ማድረግ አለበት።

2/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ተፈፃሚ የሚሆነው የሚከተሉት ተሟልተው ሲገኙ ይሆናል፤

ሀ) ዓመታዊው ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦቱ ከብር 100,000,000 በላይ የሆነ የተመዘገበ ሰው ተቀናሽ የሚደረግ የካፒታል ዕቃዎች ግዢ የፈፀመ እንደሆነ፣

ለ) የተመዘገበው ሰው ተቀናሽ ለሚደረገው የካፒታል ዕቃዎች ግዢ የግብዓት ታክስ ተቀናሽ የማግኘት መብት ያለው ከሆነ፣ እና

ሐ) ተቀናሽ የሚደረገው ግዥ በተከናወነበት የሒሣብ ጊዜ የግብዓት ታክሱ የገንዘብ መጠን ሙሉ በሙሉ ተቀናሽ ያልተደረገ ከሆነ፡፡

3/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌዎች ተሟልተው ሲገኙ የታክሱ ባለስልጣን የተመዘገበው ሰው የካፒታል ዕቃው ለተገዛበት የሂሳብ ጊዜ ተመላሽ እንዲፈቀድለት ማመልከቻ ካቀረበበት ቀን ጀምሮ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ተመላሹን መክፈል አለበት፡፡

4/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 48 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፤ በአንቀጽ 16 ወይም 17 መሠረት ምዝገባው የተሰረዘበት ሰው ምዝገባው በተሰረዘበት እለት ያልተቀናነሰለት እና ለወደፊት እንዲሸጋገር የተደረገው የግብአት ታክስ ተመላሽ እንዲደረግለት ለታክሱ ባለስልጣን በጽሁፍ ጥያቄ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

5/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት የሚቀርብ ማመልከቻ ታክስ ከፋዩ ለተመዘገበበት የመጨረሻ የሂሳብ ጊዜ የሂሳብ ማስታወቂያ ማቅረብ በሚገባው ጊዜ ውስጥ ወይም በታክሱ ባለሥልጣን በሚፈቀድ ሌላ ቀን ለታክሱ ባለሥልጣን መቅረብ አለበት፡፡

6/ የታክሱ ባለስልጣን ምዝገባው የተሰረዘ ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) እና (5) መሠረት ተቀናሽ ያልተደረገ የግብዓት ተመላሽ እንዲደረግለት ያቀረበው ማመልከቻ በበቂ ማስረጃ የተደገፈ ሆኖ ሲያገኘው ማመልከቻው በቀረበለት በ60 ቀን ጊዜ ውስጥ ተመላሹን መክፈል አለበት፡፡

7/ ምዝገባው በተሰረዘበት እለት ተቀናሽ ያልተደረገ የግብአት ታክስ ያለው ሰው ተቀናሽ ያልተደረገው የግብአት ታክስ ተመላሽ እንዲደረግለት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) እና (5) መሠረት ማመልከቻ ያላቀረበ እንደሆነ መብቱ የሚቋረጥ ሲሆን፤ ተቀናሽ ያልተደረገው የግብአት ታክስ ተመላሽ ሊደረግለት አይችልም፡፡

## 50. <u>ዘግይቶ በተከፈለ የተመላሽ ሒሣብ ላይ ስለሚከፈል ወለድ</u>

1/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 48(5) ወይም 49 በተደነገገው መሠረት የታክሱ ባለሥልጣን የተመላሹን ሒሣብ ያልከፈለ ከሆነ፣ የተመላሹ ሒሣብ መከፈል ከነበረበት አግባብነት ካለው ጊዜ መጨረሻ ጀምሮ ተመላሹ ሒሣብ እስከተከፈለ ድረስ ላለው ጊዜ የታክሱ ባለሥልጣን ወለድ መክፈል አለበት፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚከፈለው ወለድ መጣኔ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ከተመለከተው ጊዜ በፊት ባለው የሩብ ዓመት በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ ባንኮች የንግድ ብድር የሚሰጡበት ከፍተኛው የወለድ መጣኔ ይሆናል፡፡

የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት 2 ማኔጅር

51. <u>ለዲፕሎማቲክ ሚሲዮኖች፣ለዓለም ዐቀፍ ድርጅቶች እና ለኢንቬስተሮች የሚከፈል ተመላሽ ሒሣብ</u>

1/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የታክሱ ባለሥልጣን የሚቀርብለትን ጥያቄ መሠረት በማድረግ የሚከተሉት አካላት የከፈሉትን የተጨማሪ እሴት ታክስ በሙሉ ወይም በከፊል ተገቢው ማስረጃ ተሟልቶ በቀረበበት በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ተመላሽ ማድረግ አለበት::

ሀ) በቪዬና የዲፕሎማቲክ ግንኙነት ኮንቬንሽን ለሚሲዮን፣ ለዲፕሎማት ወይም ለቆንስላ የሚፈፀም ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነፃ እስከሆነ ድረስ፣ ለውጭ አገር የዲፕሎማቲክ ወይም ለኮንስላር ሚሲዮኖች ወይም ለውጭ አገር ዲፕሎማቶች እና ቆንስላዎች፣

ለ) በዓለም ዐቀፍ ስምምነት ለዓለም ዐቀፍ ድርጅቱ የሚፈፀም ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነፃ እስከሆነ ድረስ ለዓለም ዐቀፍ ድርጅት፣

ሐ) የውጭ አገር መንግሥት በፋይናንስ፣ በቴክኒክ፣ በሰብአዊ ዕርዳታ ወይም አስተዳደራዊ ድጋፍን በሚመለከት አለምአቀፍ ስምምነት ለውጭ አገር መንግስት የሚፈፀም ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነፃ የተደረገ ከሆነ፣ ወይም

መ) በሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ደንብ ቁጥር 517/2014 ለኢንቨስተር የሚፈፀም ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነፃ የተደረገ ወይም ታክሱ ተመላሽ እንዲደረግ የተፈቀደ ከሆነ::

2/ ለኢትዮጵያ ዜጎች ወይም በኢትዮጵያ ቋሚ ነዋሪ ለሆኑ ሰዎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ተመላሽ ማድረግ አይቻልም::

3/ የታክሱ ባለስልጣን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የተመላሽ ሒሣብን የሚከፍለው እንደአግባብነቱ በሁኔታ ወይም በገደብ ሊሆን ይችላል::

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚቀርበው የተመላሽ ጥያቄ:-

ሀ) የተመላሽ ጥያቄ የቀረበበት አቅርቦት ከተከናወነበት ቀን አንስቶ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ወይም የታክሱ ባለስልጣን በሚፈቅደው ተጨማሪ ጊዜ ውስጥ የፀደቀውን ቅጽ በመጠቀም መቅረብ፣ እና

ለ) ከሚከተሉት ደጋፊ ማስረጃዎች ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት:-

(i) የተመላሽ ጥያቄ የቀረበበት የተጨማሪ እሴት ታክስ ከተከፈለበት የታክስ ደረሰኝ ወይም ሌላ ተመሳሳይ ማስረጃ፣

(ii) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት አመልካቹ የተመላሽ ጥያቄ እንዲያቀርብ የሚያስችለው ማስረጃ፣ እና

(iii) የታክሱ ባለስልጣን በሚያወጣው መመሪያ ሚጠየቀውን ማናቸውም ሌላ ማስረጃ፡፡

## ክፍል አሥራ አንድ

## የተጨማሪ እሴት ታክስ ሰነዶች

### 52. የታክስ ደረሰኞች

1/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ታክስ የሚከፈልበትን አቅርቦት የሚያከናውን የተመዘገበ ሰው አቅርቦቱን ባከናወነበት ጊዜ አቅርቦቱን ለገዛው ሰው መደበኛውን የታክስ ደረሰኝ መስጠት አለበት፡፡

2/ ታክስ የሚከፈልበትን አቅርቦት የገዛው ሰው ካልጠየቀ በስተቀር የተመዘገበ ሰው የአቅርቦቱ ጠቅላላ ዋጋ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ከሚወሰነው የገንዘብ መጠን ላልበለጠ እና በጥሬ ገንዘብ ለሚፈፀም ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ክፍያ መደበኛውን የታክስ ደረሰኝ እንዲሰጥ አይገደድም፡፡

3/ ለሚከተሉት ታክስ የሚከፈልባቸው አቅርቦቶች የተመዘገበው ሰው በቀላል መንገድ የሚዘጋጅ የታክስ ደረሰኝ ሊሰጥ ይችላል፡-

ሀ) የአቅርቦቱ ጠቅላላ ዋጋ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ከሚወሰነው የገንዘብ መጠን ላልበለጠ እና በጥሬ ገንዘብ ለሚፈፀም ክፍያ፣ እና

ለ) አቅርቦቱ የተከናወነው በችርቻሮ ንግድ ሥራ ላይ በተሠማራ የተመዘገበ ሰው ከሆነ፡፡

4/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 8(1)(ሐ) እና ንዑስ አንቀጽ 8 በተመለከተው መሠረት በቀጥታ በገገርው ታክስ በሚከፈልበት አቅርቦት ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ የመክፈል ግዴታ ያለበት የተመዘገበ ሰው አገልግሎቱን ባገኘበት ጊዜ ለአቅርቦቱ በገኘው የሚዘጋጅ የታክስ ደረሰኝ ማዘጋጀት አለበት፡፡

5/ የታክስ ደረሰኝ፣ በቀላል መንገድ የሚዘጋጅ የታክስ ደረሰኝ፣ እና በገኘው የሚዘጋጅ የታክስ ደረሰኝ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ የሚወሰነውን ዝርዝር መያዝ አለበት፡፡

የሪከርድ እስተዳደር አገልግሎት 2 ሚኒስቴር

## 53. የክሬዲት እና የዴቢት ሰነዶች

1/ በዚህ አዋጅ ክፍል ስምንት የተመለከቱት ሁኔታዎች በሚሟሉበት ጊዜ የተመዘገበው ሰው ለሌላው የተመዘገበ ሰው እንደሁኔታው የክሬዲት ሰነድ ወይም የዴቢት ሰነድ መስጠት አለበት፡፡

2/ የተመዘገበው ሰው ለአቅርቦቱ ገዢ የክሬዲት ወይም የዴቢት ሰነድ የሚሰጠው ሰነዱ እንዲሰጥ ምክንያት የሆነው የማስተካከያ ተግባር በተፈፀመበት የሒሣብ ጊዜ መጨረሻ ሊሆን ይገባል፡፡

3/ የክሬዲት ሰነድ ወይም የዴቢት ሰነድ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ የተዘረዘሩ መረጃዎችን የሚይዝ መሆን አለበት፡፡

4/ ለዚህ አንቀጽ እንዲሁም ለአዋጁ አንቀጽ 55 እና 56 አፈፃፀም "**የማስተካከያ ተግባር**" የሚለው ሐረግ በአዋጁ አንቀጽ 45 እና 46 መሠረት የማይሰበሰብ ዕዳ በመኖሩ ምክንያት የሚደረግን ማስተካከያ ይጨምራል፡፡

## 54. የተጨማሪ እሴት ታክስ ሰነድ እንዲሰጥ ስለመጠየቅ

1/ በዚህ የአዋጁ ክፍል መሠረት በማናቸውም ምክንያት ዋንኛው የታክስ ደረሰኝ፣ የክሬዲት ሰነድ ወይም የዴቢት ሰነድ ያልተሰጠው የተመዘገበ ሰው አቅራቢው የታክስ ደረሰኝ፣ የክሬዲት ሰነድ ወይም የዴቢት ሰነድ እንዲሰጠው በጽሑፍ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚቀርበው ጥያቄ፡-

ሀ) የታክስ ደረሰኝን በሚመለከት የታክሱ ደረሰኝ እንዲሰጥ ምክንያት የሆነው አቅርቦት ከተከናወነበት ቀን አንስቶ በ60 ቀናት ውስጥ፣ ወይም

ለ) የክሬዲት ሰነድ ወይም የዴቢት ሰነድን በሚመለከት የክሬዲት ሰነዱ ወይም የዴቢት ሰነዱ እንዲሰጥ ምክንያት የሆነው ሁኔታ ካጋጠመበት ቀን ጀምሮ በ60 ቀናት ውስጥ፣

መቅረብ አለበት፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ጥያቄ የቀረበለት የተመዘገበ ሰው ጥያቄው ከቀረበለት ቀን አንስቶ በ14 ቀናት ውስጥ በጥያቄው መሠረት መፈፀም አለበት፡፡

4/ የተመዘገበው ሰው ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት የተከናወነበት ዋንኛ የታክስ ደረሰኝ ወይም ማስተካከያ የተደረገበት የክሬዲት ወይም የዴቢት ሰነድ ዋንኛ ቅጂ የጠፋበት

መሆኑን የገለፀ ከሆነ አቅርቦቱን ያከናወነው የተመዘገበው ሰው የዋንኛውን የታክስ ደረሰኝ ወይም የክሬዲት ሰነዱን ወይም የዴቢት ሰነዱን ቅጂ ሊሰጠው ይችላል።

5/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት ለተመዘገበው ሰው የሚሰጠው የታክስ ደረሰኝ፣ የክሬዲት ሰነድ ወይም የዴቢት ሰነድ ቅጂ በላዩ ላይ "ቅጂ" በሚል ሊፃፍበት ይገባል።

## 55. የተጨማሪ እሴት ታክስ ሰነዶች አያያዝ

1/ የተመዘገበ ሰው ለአንድ ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ሊሰጥ የሚችለው አንድ ደረሰኝ ብቻ ሲሆን፣ ማስተካከያ ማድረግ ለሚያስገድድ አንድ ሁኔታ ሊሰጥ የሚችለው አንድ የክሬዲት ሰነድ ወይም አንድ የዴቤት ሰነድ ነው። ሆኖም ዋነኛው ቅጂ ጠፍቶብኛል ለሚል የተመዘገበ ሰው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 54(4) መሠረት "ቅጂ" የሚል ጽሑፍ የሰፈረበት ቅጂ ሊሰጠው ይችላል።

2/ የተመዘገበ ሰው በዚህ የአዋጁ ክፍል ከተመለከተው ውጪ የታክስ ደረሰኝ፣ የክሬዲት ሰነድ ወይም የዴቢት ሰነድ ሊሰጥ አይችልም።

3/ ለዚህ አዋጅ እና ለታክስ አስተዳደር አዋጅ አፈፃፀም የተመዘገበ ሰው የሚከተሉትን ሰነዶች መያዝ አለበት።

ሀ) የተቀበላቸውን ዋንኛ የታክስ ደረሰኞች፣ የክሬዲት ሰነዶች እና የዴቢት ሰነዶች በሙሉ፣

ለ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 54(4) መሠረት የተቀበላቸውን የታክስ ደረሰኞች፣ የክሬዲት ሰነዶች እና የዴቤት ሰነዶች ቅጂዎች በሙሉ፣

ሐ) የሰጣቸውን የታክስ ደረሰኞች፣ የክሬዲት ሰነዶች እና የዴቢት ሰነዶች ቅጂዎች በሙሉ፤

መ) ወደአገር ካስገባቸው ወይም ወደውጭ ከላካቸው ዕቃዎች ጋር የተያያዙ የጉምሩክ ሰነዶች፣ እና

ሠ) የአገልግሎቱ ተቀባይ በሆነ የተመዘገበ ሰው የተዘጋጁ ከሆነ ይህ ሰው በቀጥታ በገዢው ታክስ የሚከፈልበትን አቅርቦት የሚመለከቱ የታክስ ደረሰኞች።

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3)(ሐ) የተጠቀሱት ሰነዶች በቅደም ተከተላቸው መሠረት መያዝ አለባቸው።

የገንዘብ
የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት 2
ሚኒስቴር

## 56. በወኪሎች አማካኝነት የተከናወኑ አቅርቦቶች የተጨማሪ እሴት ታክስ ሰነዶች

1/ ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት የተከናወነው በተመዘገበው ወካይ ስም በተወካዩ አማካኝነት የሆነ እንደሆነ እና ወካይ እና ተወካይ ሁለቱም የተመዘገቡ ሰዎች ከሆኑ ወካዩ ለታክስ ለአቅርቦቱ ሊሰጥ የሚገባውን ማናቸውንም የታክስ ደረሰኝ፣ የክሬዲት ሰነድ ወይም የዴቢት ሰነድ ተወካዩ የወካዩን ስም፣ አድራሻ እና የተጨማሪ እሴት ታክስ የምዝገባ ቁጥር በመጠቀም መስጠት ይችላል።

2/ የተመዘገበ ሰው በተወካዩ አማካኝነት ለወካዩ ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ያከናወነ እና ወካይ እና ተወካይ ሁለቱም የተመዘገቡ ከሆነ፣ ከአቅርቦቱ ጋር በተያያዘ ለወካዩ ሊሰጥ የሚገባውን የታክስ ደረሰኝ፣ የክሬዲት ሰነድ እና የዴቢት ሰነድ የተወካዩን ስም፣ አድራሻ እና የተጨማሪ እሴት ታክስ የምዝገባ ቁጥር በመጠቀም ለተወካዩ መስጠት ይችላል።

3/ ተወካይ በተመዘገበ ወካይ ስም ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ያከናወነ እንደሆነ፣ እና ወካዩ የተመዘገበ ሰው ሆኖ ተወካዩ ያልተመዘገበ ከሆነ ከአቅርቦቱ ጋር በተያያዘ በወካዩ ሊሰጥ የሚገባውን የታክስ ደረሰኝ፣ የክሬዲት ሰነድ እና የዴቢት ሰነድ የወካዩን ስም፣ አድራሻ እና የተጨማሪ እሴት ታክስ የምዝገባ ቁጥር በመጠቀም ተወካዩ ሊሰጥ ይችላል።

4/ የተመዘገበ ሰው ለወካዩ በተወካዩ አማካኝነት ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ያከናወነ እንደሆነ፣ እና ወካዩ የተመዘገበ ሰው ሆኖ ተወካዩ ያልተመዘገበ ከሆነ ከአቅርቦቱ ጋር በተያያዘ ለወካዩ ሊሰጥ የሚገባው የታክስ ደረሰኝ የወካዩን ስም፣ አድራሻ እና የተጨማሪ እሴት ታክስ የምዝገባ ቁጥር በመጠቀም ለተወካዩ መስጠት ይችላል።

5/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) መሠረት ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት በወካዩ ስም ለተወካዩ የቀረበ ወይም በወካዩ ስም በተወካዩ የቀረበ እንደሆነ፣ ከአቅርቦቱ ጋር በተያያዘ በዚህ አዋጅ መሠረት ሊሰጥ የሚገባው የታክስ ደረሰኝ፣ የክሬዲት ሰነድ ወይም የዴቢት ሰነድ አንድ ጊዜ ብቻ መስጠት ያለበት ሲሆን፣ ለወካዩ እና ለተወካዩ ወይም በወካዩ እና ለተወካዩ ሊሰጥ አይችልም።

6/ በዚህ አንቀጽ መሠረት በተወካዩ የተሰጠ ወይም ለተወካዩ የተሰጠ የታክስ ደረሰኝ፣ የክሬዲት ሰነድ እና የዴቢት ሰነድ ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም በወካዩ እና ለወካዩ እንደተሰጠ ይቆጠራል።

7/ በዚህ አንቀጽ መሠረት በወካዩ ወይም ለተወካዩ የታክስ ደረሰኝ፣ የክሬዲት ሰነድ ወይም የዴቢት ሰነድ የተሰጠ እንደሆነ፣ ተወካዩ የወካዩን ስም፣ አድራሻ እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ቁጥር ማረጋገጥ የሚያስችል በቂ መረጃ መያዝ አለበት።

የገንዘብ ሚኒስቴር
አስተዳደር አገልግሎት 2

## ክፍል አሥራ ሁለት

## የአስተዳደር እና የሥነ - ሥርዓት ደንቦች

### 57. የታክስ አስተዳደር አዋጅ ተፈፃሚነት

የዚህ ክፍል ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የታክስ አስተዳደር አዋጅ የዚህን አዋጅ አስተዳደር በተመለከተም ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

### 58. የተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ

1/ ማናቸውም የተመዘገበ ሰው የእያንዳንዱን የሒሣብ ጊዜ የተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ የሒሣብ ጊዜው ከተጠናቀቀ በኂላ ቀጥሎ ባለው ወር የመጨረሻ ቀን ድረስ ማቅረብ አለበት፡፡

2/ ማናቸውም የተመዘገበ ሰው በሒሣብ ጊዜው ውስጥ ተከፋይ የሆነ የተጨማሪ እሴት ታክስ ገቢ ቢኖረውም ባይኖረውም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሒሣብ ጊዜውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡

3/ በአንድ ወር ውስጥ በቀጥታ በገገርው ታክስ በሚከፈልበት አቅርቦት ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ የመክፈል ግዴታ ያለበት ከፍተኛ ግብይት ያለው ያልተመዘገበ ሰው ወይም ያልተመዘገበ የመንግሥት ተቋም ለዚህ ወር ግብይቱ በሚቀጥለው ወር የመጨረሻ ቀን ለታክሱ ባለስልጣን የታክስ ማስታወቂያ ማቅረብ አለበት፡፡

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት በከፍተኛ ያልተመዘገበ ሰው ወይም በመንግሥት ተቋም ሊቀርብ የሚገባው የታክስ ማስታወቂያ ለታክስ አስተዳደር አዋጁ አፈፃፀም“ የታክስ ማስታወቂያ” እና “የራስ የታክስ ማስታወቂያ” ሆኖ ይቆጠራል፡፡

### 59. የተጨማሪ እሴት ታክስ የመክፈያ ጊዜ

1/ የተመዘገበ ሰው በሒሣብ ጊዜው የሚኖረውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ተከፋይ የተጣራ ሒሣብ ታክሱን ሊያስታውቅ በሚገባው ጊዜ ውስጥ መክፈል አለበት፡፡

2/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 58(3) የተመለከተው በቀጥታ በገገርው ታክስ በሚከፈልበት አቅርቦት ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ የመክፈል ግዴታ ያለበት ከፍተኛ ግብይት ያለው ያልተመዘገበ ሰው ወይም ያልተመዘገበ የመንግሥት ተቋም በገገርው ተይዞ ታክስ የሚከፈልበትን ግብይት በፈጸመበት ወር ውስጥ ታክሱን የመክፈል ግዴታው የሚቋቋም ሲሆን፤ ይህ ሰው የታክስ ማስታወቂያ ማቅረብ ባለበት ጊዜ ውስጥ ታክሱን መክፈል አለበት፡፡

3/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 28 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ማናቸውም አስመጪ ወደ አገር ባስገባቸው ዕቃዎች ላይ ሊከፈል የሚገባውን ታክስ ዕቃዎቹን ወደአገር ባስገባበት ጊዜ መክፈል አለበት።

60. <u>ወደአገር በሚገቡ ዕቃዎች ላይ ታክሱን ስለመሰብሰብ</u>

1/ ኮሚሽኑ፣

ሀ) ወደአገር በሚገቡ ዕቃዎች ላይ ዕቃዎቹ ወደአገር በሚገቡበት ጊዜ ታክሱን መሰብሰብ፣

ለ) የአስመጪውን የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር (ካለ) እና የዕቃዎቹን የዋጋ ኢንቮይስ መቀበል፣ እና

ሐ) የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት በፖስታ ቤት በኩል ከሚመጡ ዕቃዎች ላይ ኮሚሽኑን በመወከል በዚህ አንቀጽ ተራ ፊደል (ሀ) የተመለከተውን ተግባር መፈፀም እንዲችል ሁኔታዎችን ማመቻቸት አለበት።

2/ በዚህ አዋጅ ወይም በሚኒስቴሩ በሚወጣ መመሪያ የተመለከተው ማስተካከያ ወይም የተለየ አሠራር እንደተጠበቀ ሆኖ፣ አግባብነት እስካላቸው ድረስ በጉምሩክ አዋጅ ወደአገር ስለሚገቡ እና በትራንዚት ላይ ስላሉ ዕቃዎች፣ ወደአገር ስለሚገቡ ዕቃዎች ክሊራንስ፣ የጉምሩክ ቀረጥን ስለመክፈል እና ታክሱን ስለማስመለስ የተደነገጉት ድንጋጌዎች ወደአገር በሚገቡ ዕቃዎች ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ ለመሰብሰብም ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል።

3/ ወደአገር በሚገቡ ዕቃዎች ላይ የሚከፈለውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ለመሰብሰብ ሲባል ኮሚሽኑ በጉምሩክ አዋጅ የተሰጠውን ሥልጣን በዚህ አዋጅ መሠረት ወደአገር በሚገቡ ዕቃዎች ላይ ስለሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ ጭምር እንደተሰጠው በመቁጠር ሊሰራበት ይችላል።

4/ ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም "የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት" ማለት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 165/2009 የተቋቋመው የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት ነው።

61. <u>ከአቅርቦቱ ተጠቃሚ ላይ ስለሚጠየቅ ታክስ</u>

1/ ይህ አንቀጽ ተፈፃሚ የሚሆነው የአቅርቦቱ ተጠቃሚ በሰጠው የተሳሳተ መረጃ ወይም በፈፀመው የማጭበርበር ድርጊት ምክንያት የተመዘገበው ሰው፦

ሀ) አቅርቦቱ ከታክስ ነፃ እንዲሆን፣

የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት 2 ማንስቴር

ለ) በአቅርቦቱ ላይ ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈፃሚ እንዲሆን፣ ወይም

ሐ) የተጨማሪ እሴት ታክስ እንዳይከፈልበት ያደረገ፣

እንደሆነ ነው፡፡

2/ ይህ አንቀጽ ተፈፃሚ በሚሆንበት ጊዜ የታክሱ ባለሥልጣን የአቅርቦቱ ተጠቃሚ ተገቢ ባልሆነ የተጨማሪ እሴት ታክስ አወሳሰን ምክንያት በአቅርቦቱ ላይ ያልከፈለውን የተጨማሪ እሴት ታክስ፣ ክፍያው በመዘግየቱ የሚከፈለውን ወለድ፣ ክፍያው በዘገየበት የሚጣለውን መቀጫ እንዲከፍል ሊጠይቀው ይችላል፡፡

3/ የታክሱ ባለሥልጣን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የአቅርቦቱ ተጠቃሚ ታክሱን እንዲከፍል ሲጠይቅ በደንቡ የተመለከቱትን ዝርዝር ሁኔታዎች የሚገልጽ ማስታወቂያ መስጠት አለበት፡፡

4/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ የታክሱ ባለሥልጣን የተጨማሪ እሴት ታክሱን በሙሉ ወይም በከፊል፣ ክፍያ በመዘግየቱ የሚከፈል ወለድ እና ክፍያው በመዘግየቱ ከሚጣል መቀጫ ጋር አቅርቦቱን ካከናወነው ከተመዘገበው ሰው ላይ ከመጠየቅ አያግደውም፡፡ ሆኖም የታክሱ ባለስልጣን በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚጠይቀው ታክስ በአቅርቦቱ ላይ ሊከፈል ከሚገባው የተጨማሪ እሴት ታክስ፣ ክፍያ በመዘግየቱ ከሚከፈል ወለድ እና በዘገየበት ከሚጣል መቀጫ የበለጠ ሊሆን አይችልም፡፡

5/ በዚህ አንቀጽ መሠረት ከአቅርቦቱ ተጠቃሚ የሚሰበሰበው ታክስ አቅራቢው በአቅርቦቱ ላይ ሊከፈል ከሚገባው ታክስ ላይ ይቀነሳል እንዲሁም ከአቅራቢው የሚሰበሰበው ማናቸውም ገንዘብ የአቅርቦቱ ተጠቃሚ ሊከፍል ከሚገባው ታክስ ላይ ይካካሳል፡፡

6/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በአቅርቦቱ ተጠቃሚ ሊከፈል የሚገባውን የተጨማሪ እሴት ታክስ፣ ክፍያ በመዘግየቱ የሚከፈል ወለድ እና በዘገየበት የሚጣል መቀጫ የከፈለ አቅራቢ የከፈለውን ገንዘብ ከአቅርቦቱ ተጠቃሚ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

7/ ለዚህ አዋጅ እና ለታክስ አስተዳደር አዋጅ አፈፃፀም በዚህ አንቀጽ መሠረት የተወሰነ ታክስ በዚህ አዋጅ መሠረት የተጠየቀ የተጨማሪ እሴት ታክስ ሆኖ ይቆጠራል፡፡

8/ የታክስ አስተዳደር አዋጅ ድንጋጌዎች የታክሱ ባለሥልጣን የዚህን አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) ተፈፃሚ ለማድረግ የታክስ ከፋዩን የገቢ ማስታወቂያ ጨምሮ ማናቸውንም ውሳኔ ከማሻሻል አያግዱትም፡፡

9/ ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም፡-

**"ክፍያ በመዘግየቱ የሚከፈል ወለድ"** ማለት በታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀጽ 37 መሠረት የታክስ ክፍያ በመዘግየቱ ምክንያት የሚከፈል ወለድ ነው፡፡

"ክፍያ በመዘግየቱ የተጣለ መቀጫ" ማለት በታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀጽ 104 መሠረት የታክስ ክፍያ በመዘግየቱ የሚጣል መቀጫ ነው::

## 62. ከተከፋይ ሒሣብ ላይ የሚቀነስ የተጨማሪ እሴት ታክስ

1/ የተመዘገበ ሰው ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ያከናወነው ለመንግሥት ተቋም የሆነ እንደሆነ፣ አቅርቦቱ የተፈፀመለት የመንግሥት ተቋም:-

ሀ) በአቅርቦቱ ላይ ሊከፈል የሚገባውን የተጨማሪ እሴት ታክስ 50 በመቶ ቀንሶ የማስቀረት፣

ለ) ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ በሚወሰነው አኳኋን ቀንሶ ያስቀረውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ለታክሱ ባለስልጣን ገቢ የማድረግ፣ እና

ሐ) በአቅርቦቱ ላይ ሊከፈል የሚገባውን ቀሪውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ሒሣብ 50 በመቶ ለተመዘገበው ሰው የመክፈል፣ ግዴታ አለበት::

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በመንግሥት ተቋም ተቀንሶ የተያዘ ማናቸውም የተጨማሪ እሴት ታክስ አቅርቦቱን ባከናወነው የተመዘገበ ሰው ለታክሱ ባለስልጣን እንደተከፈለ ይቆጠራል::

3/ ለመንግሥት ተቋም ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ያከናወነ እና በዚህ አንቀጽ መሠረት የተጨማሪ እሴት ታክሱ ሒሣብ ከተከፋይ ሒሣብ ላይ ተቀንሶ የተያዘበት የተመዘገበ ሰው፣ አቅርቦቱ በተከናወነበት ወቅት ባለው የሒሣብ ጊዜ ከተከፋይ ሒሣብ ላይ ተቀናሽ ለተደረገበት የገንዘብ መጠን ተቀናሽ የማግኘት መብት ይኖረዋል::

4/ ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም "የመንግሥት ተቋማት" ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 2(20) በተሰጠው ትርጉም ውስጥ የሚወድቅ እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (ለ) በተጠቀሰው መመሪያ መሠረት ከተከፋይ ሂሳብ ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስን ቀንሶ እንዲያስቀር በሚኒስቴሩ ኃላፊነት የተሰጠው የመንግሥት ተቋም ነው::

## 63. ዕቃዎችን በመመዝገብ ረገድ ስለተጣለ ገደብ

1/ የባለቤትነት ምዝገባ የሚያስፈልጋቸውን ወደአገር የሚገቡ ዕቃዎች የመመዝገብ ሥልጣን የተሰጠው አካል እነዚህን ዕቃዎች ወደኢትዮጵያ ያስገባው ሰው የሚከተሉትን ማስረጃዎች ካላቀረበ በስተቀር መመዝገብ የለበትም :-

ሀ) ወደአገር በገቡት ዕቃዎች ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ የተከፈለ መሆኑን የሚያረጋግጥ የጉምሩክ ዲክላራሲዮን፣ ወይም

ለ) ወደአገር የገቡት ዕቃዎች ከታክሱ ነፃ መሆናቸውን የሚገልጽ የጉምሩክ ሰነድ፤

ሐ) የአዋጁ አንቀጽ 28 ተፈጻሚ በሚሆንበት ሁኔታ ወደአገር በገቡት እቃዎች ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ የተከፈለ መሆኑን የሚያረጋግጥ በታክሱ ባለስልጣን የተሰጠ የምስክር ወረቀት፤

2/ መመዝገብ ያለባቸውን ዕቃዎች የመመዝገብ ሥልጣን የተሰጠው አካል አቅርቦቱ የተፈፀመለት ሰው ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ማስረጃዎች ካላቀረበ በስተቀር መመዝገብ የለበትም፡

ሀ) አቅርቦቱን ያከናወነው የተመዘገበ ሰው በታክሱ ባለሥልጣን የፀደቀውን ቅጽ በመጠቀም የሰጠውን በአቅርቦቱ ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ የተከፈለ ወይም የሚከፈል መሆኑን የሚያረጋግጥ ዋንኛውን ደረሰኝ፣ ወይም

ለ) የታክሱ ባለስልጣን የሰጠውን አቅርቦቱ ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነፃ መሆኑን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት።

3/ ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም፡-

**"የመመዝገብ ሥልጣን የተሰጠው አካል"** በሕግ የመመዝገብ ግዴታ የተጣለባቸውን ዕቃዎች የመመዝገብ ኃላፊነት የተሰጠው አካል ነው።

**"መመዝገብ ያለባቸው ዕቃዎች"** ማለት በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት መመዝገብ ያለባቸው ዕቃዎች ናቸው።

## 64. <u>የውጭ አገር አገልግሎት ሰጪ ግዴታዎች</u>

1/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ፤ የታክሱ ባለስልጣን በዚህ አዋጅ አንቀጽ 12 መሠረት የመመዝገብ ግዴታ ያለበት እና ከኢትዮጵያ ውጪ ታክስ የሚከፈልበትን እንቅስቃሴ የሚያከናውን በኢትዮጵያ ውስጥ በቋሚነት የሚሰራ ድርጅት የሌለው ሰው በታክስ አስተዳደር አዋጅ በተደነገገው መሠረት ለታክሱ መክፈል ዋስትና እንዲያቀርብ ሊጠይቅ ይችላል።

2/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ተፈፃሚ የሚሆነው የታክሱ ባለሥልጣን የውጭ አገር አገልግሎት ሰጪው በዚህ አዋጅ የተጣሉበትን ግዴታዎች የማይወጣ መሆኑን የሚያሳምን በቂ ምክንያት ሲኖረው ነው።

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ዋስትና ያቀረበ ሰው በዚህ አዋጅ በተጣለበት ግዴታ መሠረት ያልፈፀመ እንደሆነ የታክሱ ባልስልጣን ይህ ሰው በኢትዮጵያ ውስጥ ለተጨማሪ እሴት ታክስ ወኪል እንዲሰይም ሊያስገድደው ይችላል።

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት የተጨማሪ እሴት ታክስ ወኪል የሆነ ሰው ለተጨማሪ እሴት ታክስ ለመመዝገብ ማመልከቻ ማቅረብን፤ የታክስ ማስታወቂያ

ማቅረብን፤ የተጨማሪ እሴት ታክስ መክፈልን ጨምሮ በወከለው ሰው ስም በዚህ አዋጅ የተመለከቱ ተግባሮችን የመፈጸም ኃላፊነት አለበት፡፡

5/ የተጨማሪ እሴት ታክስ ወኪል ምዝገባ የሚከናወነው በወካዩ ስም ነው፡፡

6/ አንድ ሰው ለብዙ ሰዎች የተጨማሪ እሴት ታክስ ወኪል መሆን የሚችል ሲሆን፤ ሆኖም ለእያንዳንዱ ለሚወክለው ሰው የተለያየ ምዝገባ መፈፀም አለበት፡፡

7/ በዚህ አንቀጽ መሠረት የተጨማሪ እሴት ታክስ ወኪል የሚሆን ሰው፤

ሀ) ለታክስ አስተዳደር አዋጅ አፈጻጸም የወካዩ የታክስ እንደራሴ ሆኖ ይቆጠራል፤ እና

ለ) ለሚወክለው ሰው የተጨማሪ እሴት ታክስ ግዴታ የግል ተጠያቂነት ይኖርበታል፡፡

8/ የታክሱ ባለስልጣን የተጨማሪ እሴት ታክስ ወኪል የሚሾምበትን መንገድ፣ አኳኋን እና ተፈላጊ ሁኔታዎች በመመሪያ ሊወስን ይችላል፡፡

## 65. <u>በገቢው ታክስ በሚከፈልበት አቅርቦት ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ የመክፈል ግዴታ ያለበት ሰው</u>

1/ በኢትዮጵያ ውስጥ ዘላቂ ድርጅት ሳይኖረው ከውጭ አገር ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ከሚያከናውን የተመዘገበ ሰው ግብይት የሚፈፅም የተመዘገበ ሰው፤የመንግሥት ተቋም ወይም ከፍተኛ ግብይት ያለው ያልተመዘገበ ሰው በሚፈፅመው

በቀጥታ በገቢው ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ የመክፈል ግዴታ ያለበት መሆኑን በታክስ ባለስልጣኑ የጸደቀውን ቅጽ በመጠቀም ለአቅራቢው ማሳወቅ አለበት፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ለአቅራቢው የሚላከው ማስታወቂያ አቅርቦቱ በተፈፀመ ጊዜ ወይም ከመፈፀሙ በፊት መሰጠት አለበት፡፡

## 66. <u>የተጨማሪ እሴት ታክስ ቅጣት</u>

1/ ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገበ ሰው ከዚህ በታች ለተመለከተው ለእያንዳንዱ ጥፋት ብር 100,000 (አንድ መቶ ሺህ ብር) አስተዳደራዊ ቅጣት ይቀጣል፤

ሀ) በአዋጁ አንቀጽ 15(1) በተደነገገው መሠረት የተጨማሪ እሴት ታክስ የምዝገባ የምስክር ወረቀቱን ዋነኛ ቅጂ ታክስ የሚከፈልበትን ግብይት በሚያከናውንበት ዋና መስሪያ ቤት እንዲሁም የምዝገባ የምስክር ወረቀቱን ቅጂ ታክስ የሚከፈልበትን ግብይት በሚያከናውንበት በእያንዳንዱ የስራ ቦታ ያልለጠፈ እንደሆነ፤

ለ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 15(2) በተደነገገው መሠረት ታክስ የሚከፈልበትን ግብይት በሚያከናውንበት ማናቸውም ዌብሳይት፤ የማህበራዊ ሚዲያ ገጽ ወይም ሌላ

የኤሌክትሮኒክ መድረክ የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባውን ዝርዝር መረጃ ያልገለጸ እንደሆነ፤

ሐ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 15(3) በተመለከተው መሠረት በስራው ላይ የተደረገውን ለውጥ ያላሳወቀ እንደሆነ፤

መ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 16(1) በተደነገገው መሠረት ለታክስ ባለሥልጣኑ መረጃ ያልሰጠ እንደሆነ፤

ሠ) ታክስ የሚከፈልበትን አቅርቦት በማከናወን ላይ እያለ ለታክሱ ባልስልጣን በአዋጁ አንቀጽ 16 መሠረት ማመልከቻ ያቀረበ ወይም ለተጨማሪ እሴት ታክስ የመመዝገብ ግዴታው ፀንቶ ባለበት ሁኔታ ምዝገባው እንዲሰረዝለት በአዋጁ አንቀጽ 17 መሠረት ጥያቄ ያቀረበ እንደሆነ፤

ረ) በአዋጁ አንቀጽ 18(1) (ሀ) ወይም (ሐ) የተመለከተውን ግዴታውን ያልተወጣ እንደሆነ፤

ሰ) በአዋጁ አንቀጽ 52(4) በተደነገገው መሠረት በተቀባዩ የሚዘጋጅ ደረሰኝ ባልቆረጠበት በእያንዳንዱ ግብይት፤

ሸ) በዚህ አዋጅ መሠረት የዴቢት ኖት ወይም የክሬዲት ኖት ባልቆረጠበት በእያንዳንዱ ግብይት፤

ቀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 54 መሠረት በቀረበለት ጥያቄ መሰረት ያልፈጸመ እንደሆነ፤ ወይም

በ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 68(1) መሠረት ያልፈጸመ እንደሆነ፤

2/ በዚህ አዋጅ ከተደነገገው ውጪ የታክስ ደረሰኝ፤ የክሬዲት ኖት ወይም የዴቢት ኖት የሰጠ ማናቸውም ሰው ለእያንዳንዱ ድርጊት ብር 50,000 የገንዘብ መቀጫ ይቀጣል፡፡

3/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 65 በተደነገገው መሠረት ያልፈፀመ የተመዘገበ ሰው፤ ከፍተኛ ግብይት ያለው ያልተመዘገበ ሰው ወይም የመንግሥት ተቋም ብር 50,000 የገንዘብ መቀጫ ይቀጣል፡፡

## ክፍል አሥራ ሦስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 67. ቅርንጫፎች እና የሥራ ክፍሎች

1/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣

የገንዘብ ሚኒስቴር የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት 2

ሀ) ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም በቅርንጫፎች እና በሥራ ክፍሎች የተከናወነ ታክስ የሚከፈልበት የሥራ እንቅስቃሴ እንደ አንድ ታክስ የሚከፈልበት የሥራ እንቅስቃሴ ይቆጠራል፣ እና

ለ) በቅርንጫፎች እና በሥራ ክፍሎች ታክስ የሚከፈልበት የሥራ እንቅስቃሴ የሚያከናውን ሰው መመዝገብ ያለበት በራሱ ስም እንጂ በቅርንጫፉ እና በሥራ ክፍሎቹ ስም ሊሆን አይችልም።

2/ የታክሱ ባለስልጣን የተመዘገበው ሰው በጽሑፍ የሚያቀርበውን ጥያቄ መሰረት በማድረግ የተመዘገበው ሰው ለእያንዳንዱ ቅርንጫፍ ወይም የስራ ክፍል ወይም በተናጠል ለሚያከናውነው ታክስ የሚከፈልበት እንቅስቃሴ ራሱን የቻለ የሂሳብ አያያዝ ስርአት ያለው መሆኑን እና በሚያከናውነው የስራ እንቅስቃሴ የተለየ ባህሪ ወይም ባለበት አድራሻ ተለይቶ የሚታወቅ መሆኑን ሲያምንበት የተመዘገበው ሰው በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች በግለሰብ ደረጃ የሚከናውነውን አንድ ወይም ከአንድ በላይ ቅርንጫፍ ወይም የስራ ክፍል ወይም በተናጠል የሚያከናውነውን ታክስ የሚከፈልበት እንቅስቃሴ ራሱን የቻለ የተመዘገበ ሰው አድርጎ እንዲያስመዘግብ ሊፈቅድ ይችላል።

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ቅርንጫፍ፣ የሥራ ክፍል ወይም የተለየ ታክስ የሚከፈልበት እንቅስቃሴ ራሱን ችሎ እንዲመዘገብ የሚፈቀደው የታክሱ ባለስልጣን ለተመዘገበው ሰው በሚሰጠው የጽሑፍ ማስታወቂያ የተመለከቱ ሁኔታዎች እና ገደቦች እንደተጠበቁ ይሆናል።

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የተመዘገበ ሰው ያሉት ቅርንጫፎች፤ የሥራ ክፍሎች ወይም የተለዩ ታክስ የሚከፈልባቸው የስራ እንቅስቃሴዎች ራሳቸውን ችለው እንዲመዘገቡ ከተደረገ፣

ሀ) ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም ቅርንጫፉ፤ የሥራ ክፍሉ ወይም የተለየው ታክስ የሚከፈልበት እንቅስቃሴ ራሱን እንደቻለ ሰው ይቆጠራል፣ እና

ለ) የተመዘገበው ሰው እና የዚህ ሰው ቅርንጫፎች፤ የሥራ ክፍሎች እና የተለየው ታክስ የሚከፈልበት እንቅስቃሴ ግንኙነት ያላቸው ሰዎች እንደሆኑ ይቆጠራል።

## 68. <u>የተጨማሪ እሴት ታክስ የታከለበት ዋጋ</u>

1/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የተመዘገበ ሰው ታክስ ለሚከፈልበት የሥራ እንቅስቃሴ የሚያስተዋውቀው ወይም የሚሰጠው ዋጋ የተጨማሪ እሴት ታክስን ማካተት ያለበት ሲሆን፣ ይህም በማስታወቂያው ወይም በሚሰጠው ዋጋ በግልጽ መመልከት አለበት።

2/ በሚከተሉት ሁኔታዎች የተመዘገበ ሰው የሚያስተዋውቀው ወይም የሚሰጠው ዋጋ የተጨማሪ እሴት ታክስን የማይጨምር ሊሆን ይችላል፤

የገንዘብ ሚኒስቴር የሪከርድ አስተዳደር ክፍል 2

ሀ) ማስታወቂያው ወይም የሚሰጠው ዋጋ በአቅርቦቱ ላይ ሊከፈል የሚገባው የተጨማሪ እሴት እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ሲታከል የሚኖረውን የዕቃውን ዋጋ ጭምር የሚገልጽ ከሆነ፣እና

ለ) የተጨማሪ እሴት ታክስ የታከለበትን ዋጋ እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ያልታከለበትን ዋጋ በሚመለከት የሚወጣው ማስታወቂያ ወይም የሚሰጠው ዋጋ የሚኖረው ተፈላጊነት ወይም ውጤት እኩል ከሆነ።

3/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የተመዘገበ ሰው የሚያቀርባቸው ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ማስታወቂያ የተመዘገበው ሰው ታክስ የሚከፈልበትን የሥራ እንቅስቃሴ በሚያከናውንበት ቦታ የመግቢያ በሮች ወይም ደንበኞች ክፍያ በሚፈፅሙበት ቦታ በተገቢው ሁኔታ እስከተገለፀ ድረስ በክፍያ መቀበያ ቲኬቶች ላይ ዋጋው የተጨማሪ እሴት ታክስ የታከለበት መሆኑን መግለጽ አስፈላጊ አይሆንም።

4/ የታክሱ ባለሥልጣን ማናቸውም የተመዘገበ ሰው ወይም የተመዘገቡ ሰዎች ቡድን የሚያቀርቡትን ዕቃ ወይም አገልግሎት ዋጋ የሚገልፁበትን ሌላ ዘዴ ሊወሰን ይችላል፡ ፡

5/ ለተጨማሪ እሴት ታክስ ያልተመዘገበ ሰው በጨረታ ተሳታፊ የሆነ እንደሆነ፣

ሀ) በጨረታው የመወዳደሪያ ዋጋውን የሚያቀርበው የተጨማሪ እሴት ታክስን ሳይጨምር መሆን አለበት፣ እና

ለ) በጨረታው አሸናፊ ከሆነ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 12 መሠረት ለተጨማሪ እሴት ታክስ መመዝገብ ያለበት ሲሆን፣ በጨረታው መሠረት በሚያከናውነው ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ መሰብሰብ አለበት።

69. <u>የተመዘገበ ሰው መሞት፤ ክፍያ መፈጸም ያለመቻል ወይም መክሰር እና ንብረት በመያዣነት የተቀበለ ሰው</u>

1/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ ተፈፃሚ የሚሆነው የሚከተሉት ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ ይሆናል፤

ሀ) የተመዘገበው ሰው ሲሞት፣ ወይም ክፍያ መፈፀም ያለመቻሉ ወይም መክሰሩ ሲረጋገጥ እና

ለ) ከሚከተሉት አንዱ ሲያጋጥም፣

(i) ቀደም ሲል በተመዘገበው ሰው ሲካሄዱ የነበሩ ታክስ የሚከፈልባቸውን እንቅስቃሴዎች የሞተውን፤ ክፍያ መፈጸም ያቋረጠውን ወይም የከሰረውን የተመዘገበ ሰው ሀብት የሚያስተዳድረው ሰው ሲያካሂድ፣ ወይም

(ii) የተመዘገበውን ሰው ታክስ የሚከፈልበት የሥራ እንቅስቃሴ የሚያቋርጥ ማናቸውም ተግባር ሲፈፀም፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ የተመዘገበው ሰው ሀብት አስተዳዳሪ ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም የተመዘገበውን ሰው ታክስ የሚከፈልበት እንቅስቃሴ በማከናወን ተግባር እንደቀጠለ ይቆጠራል፡፡

3/ ንብረት በመያዣነት የተቀበለ ሰው ቀደም ሲል ንብረቱን በመያዣነት የሰጠውን የተመዘገበ ሰው የመሬት ይዞታ ወይም ሌላ ንብረት የተረከበ እና በመያዣነት የሰጠው ሰው ሲያካሂድ የነበረውን ታክስ የሚከፈልበት የሥራ እንቅስቃሴ ማካሄድ የቀጠለ እንደሆነ ታክስ የሚከፈልበትን የሥራ እንቅስቃሴ ማካሄድ እስከቀጠለበት ጊዜ እና በዚያው መጠን መሬቱን ወይም ንብረቱን በመያዣ እንደሰጠው ሰው ሆኖ ይቆጠራል፡
፡

## 70. <u>የተጨማሪ እሴት ታክስ ያለመክፈል ዕቅድ</u>

1/ ይህ አንቀጽ ተፈፃሚ የሚሆነው የሚከተሉት ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ ይሆናል፡
፡

ሀ) ታክስ ያለመክፈል ዕቅድ የተዘረጋ ወይም ተግባራዊ የተደረገ ከሆነ፣

ለ) ማናቸውም ሰው ታክስ ያለመክፈሉን ዕቅድ በመጠቀም የታክስ ጥቅም ያገኘ እንደሆነ፣ እና

ሐ) ታክስ ያለመክፈሉ ዕቅድ ይዘት ሲመረመር፣ ታክስ ባለመክፈሉ ዕቅድ የተሳተፈ ወይም ተግባራዊ ያደረገው ሰው ወይም ካደረጉት ሰዎች አንዱ ይህንን ድርጊት የፈፀመበት ብቸኛ ዓላማ ወይም ዋነኛ ዓላማ በዚህ አንቀጽ ተራ ፊደል (ለ) የተጠቀሰውን የታክስ ጥቅም ለማግኘት ከሆነ፣ ነው፡፡

2/ በዚህ አዋጅ የተደነገገው ቢኖርም ይህ አንቀጽ ተፈፃሚ በሚሆንበት ጊዜ የታክሱ ባለሥልጣን ዕቅዱ ያልተዘረጋ ወይም ተግባራዊ እንዳልሆነ በመቁጠር የተገኘውን የታክስ ጥቅም ለማስቀረት ወይም ለመቀነስ ያስችላል ብሎ የሚያምንበትን እርምጃ በመውሰድ በተዘረጋው ዕቅድ ታክስ ላለመክፈል የቻለው ሰው እና ከተዘረጋው ዕቅድ ጋር ግንኙነት ያለው ማናቸውም ሰው የሚኖርበትን ተጨማሪ እሴት ታክስ የመክፈል ግዴታ ሊወስን ይችላል፡፡

3/ የታክሱ ባለሥልጣን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ውሳኔ ሲሰጥ በታክስ አስተዳደር አዋጅ በተደነገገው መሠረት የታክስ ውሳኔ ማሻሻያን ጨምሮ በውሳኔው ምክንያት የተጨማሪ እሴት ታክስ የመክፈል ግዴታ የተጣለበትን ሰው ወይም ሰዎች ግዴታ የሚገልጽ የውሳኔ ማስታወቂያ እንዲደርስ ማድረግ አለበት።

4/ ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም፣

**"ዕቅድ"** የሚከተሉትን ይጨምራል፡-

ሀ) በግልጽ የተደረገ ወይም በግልፅ ሳይነገር የተደረገ ቢሆንም ባይሆንም፣ በክርክር ሂደት ሕጋዊ አስገዳጅነት ቢኖረውም ባይኖረውም ስምምነት፣ ማመቻቸት ወይም ቃልኪዳን፣ ወይም

ለ) በአንድ ሰው ወይም በሁለት እና ከሁለት በላይ በሆኑ ሰዎች የተፈፀመ ማናቸውም ግዴታ፣ ዕቅድ፣ የውሳኔ ሀሳብ፣ የድርጊት መርሀ ግብር፣ ወይም የድርጊት ስልት፣ እና

**"የታክስ ጥቅም"** ማለት

ሀ) አንድ ሰው ሊከፍል የሚገባውን ተጨማሪ እሴት ታክስ መጠን መቀነስ፣

ለ) ሊያገኝ የሚገባውን የግብአት ታክስ ተቀናሽ መጨመር፣

ሐ) ሊያገኝ የሚገባውን ተመላሽ መጨመር፣

መ) ሊከፍል የሚገባውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ማዘግየት፣

ሠ) ሊያገኝ የሚገባውን የግብአት ታክስ ተቀናሽ ማፋጠን፣

ረ) ሊከፍል የሚገባውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ከማዘግየት ወይም ሊያገኝ የሚገባውን የግብአት ታክስ ተቀናሽ ከማፋጠን የሚገኝ ማናቸውም ሌላ ጥቅም፣

ሰ) ታክስ ሊከፈልበት የሚገባው አቅርቦት፣ ወደአገር የሚገባ ዕቃ ወይም በቀጥታ በገዢው ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት፤ እንደሁኔታው፤ ታክስ የማይከፈልበት አቅርቦት፣ ታክስ የማይከፈልበት ወደአገር የሚገባ ዕቃ ወይም ታክስ የማይከፈልበት በቀጥታ በገዢው ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት እንዲሆን የሚያስችል ማናቸውም ድርጊት፣ ወይም

ሸ) ታክስ የሚከፈልበትን አቅርቦት ከማከናወን ውጪ ባለ ድርጊት ጥቅም ላይ የዋለው ወይም የሚውለው ተቀናሽ የሚሆን የግዢ የግብአት ታክስ ተቀናሽ እንዲገኝበት ማድረግ።

የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት 2 ሚኒስቴር

## 71. የገንዘብ ምንዛሪ

1/ የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 5 እንድተጠበቀ ሆኖ፤ ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም ማናቸውም የገንዘብ መጠን በብር መገለጽ አለበት።

2/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የገንዘብ መጠን የተገለፀው በብር ሳይሆን በሌላ የገንዘብ ዓይነት የሆነ እንደሆነ፣

ሀ) ወደአገር የገቡ ዕቃዎችን በሚመለከት፣ በዕቃው ላይ ሊከፈል የሚገባውን የጉምሩክ ቀረጥ ለማስላት በጉምሩክ አዋጅ ጥቅም ላይ እንዲውል የተፈቀደውን የውጭ ገንዘብ ምንዛሪ ተመን መሠረት በማድረግ የገንዘቡ መጠን ወደብር እንዲቀየር ይደረጋል።

ለ) በሌሎች ማናቸውም ሁኔታዎች የገንዘቡ መጠን ወደብር የሚለወጠው የገንዘቡ መጠን ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም በሒሣብ ስሌት ውስጥ መካተት በሚገባው ቀን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ሥራ ላይ ባዋለው በውጭው አገር ገንዘብ እና በኢትዮጵያ ብር መካከል ባለው የውጭ ገንዘብ የምንዛሪ ተመን ይሆናል።

3/ የውጭ አገር አቅራቢ የውጭ አገር ገንዘብን ወደብር ለመለወጥ ከሚከተሉት አንዱን ዘዴ ሊጠቀም ይችላል።

ሀ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) (ለ) የተመለከተውን አሠራር፣

ለ) አግባብነት ባለው የሒሣብ ጊዜ የመጨረሻ ቀን በኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ጸንቶ የሚሰራበትን በውጭ አገር ገንዘብ እና በኢትዮጵያ ብር መካከል ያለውን የምንዛሪ ተመን፣ ወይም

ሐ) ከታክሱ ባለሥልጣን ጋር ስምምነት የሚደረስበትን ሌላ ዘዴ።

4/ የውጭ አገር አቅራቢ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት የሚመርጠው አሠራር አቅራቢው ለሚፈፅመው አቅርቦት ሁሉ ተፈፃሚ የሚደረግ ሲሆን፣ የታክሱ ባለስልጣን ካልተስማማ በስተቀር አቅራቢው ምርጫውን ከአንድ ዓመት በፊት ሊስርዝ አይችልም፡

5/ በሚኒስትሮች ም/ቤት በሚወጣ የተጨማሪ እሴት ታክስ ደንብ የውጭ አቅራቢ የታክስ ማስታወቂያውን እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ክፍያን በውጭ ምንዛሪ እንዲፈጽም ሊፈቅድ ይችላል።

6/ ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም " የውጭ አገር አቅራቢ" ማለት ፡-

ሀ) የዚህ አዋጅ አንቀጽ 23(2) (ሐ) ተፈጻሚ የሚሆንበት በኤሌክትሮኒክ ዘዴ የሚታዘዝ እቃ አቅራቢ፤ ወይም

ለ) የዚህ አዋጅ አንቀጽ 24(2) (ሐ) ተፈጻሚ የሚሆንበት ከሩቅ የሚሰጥ አገልግሎት አቅራቢ፤

ሐ) የዚህ አዋጅ አንቀጽ 23(3) እና (25) ተፈጻሚ የሚሆንበት የኤሌክትሮኒክ ማከፋፈያ ገበያ አስተዳዳሪ፤

የሆነ ሰው ነው።

## 72. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

1/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ጨምሮ ለአዋጁ ትክክለኛ አፈፃፀም የሚረዱ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፦

ሀ) የተወሰኑ የአቅርቦት ዓይነቶችን ወይም የግብዓት ታክስ ተቀናሽ አፈቃቀድን፣

ለ) በዚህ አዋጅ ከተደነገገው በተለየ ለአንድ አቅርቦት የተጨማሪ እሴት ታክስ ተፈፃሚ የሚደረግበትን አግባብ፣

ሐ) ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነጻ ሊሆኑ የሚችሉ ሌሎች እቃዎች እና አገልግሎቶችን፤ ወይም

መ) የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎችን የሚመለከቱ ደንቦችን።

2/ ሚኒስቴሩ ለአዋጁና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ለሚወጣው ደንብ ትክክለኛ አፈፃፀም የሚያግዙ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

## 73. የተሻሩ እና ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጎች

1/ ይህ አዋጅ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት ወይም ይህ አዋጅ ሥራ ላይ ከዋለ በኋላ በወጣ ሕግ ውስጥ ያለ አንድ አቅርቦት ወይም አቅርቦቶች ወይም ወደአገር የሚገባ ዕቃ ወይም ወደአገር የሚገቡ ዕቃዎች ወይም ከውጭ አገር የሚሰጡ አገልግሎቶች ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነፃ እንደሆኑ ወይም ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈፃሚ እንደሚደረግላቸው የሚደነግግ አንቀጽ በዚህ አዋጅ ይህ መብት ካልተቋቋመ በስተቀር ተፈፃሚነት አይኖረውም።

2/ ይህ አዋጅ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት ወይም ይህ አዋጅ ሥራ ላይ ከዋለ በኋላ በወጣ ሕግ ውስጥ ያለ አንድ ሰው ወይም ሰዎች ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነፃ የተደረጉ መሆኑን የሚደነግግ አንቀጽ በዚህ አዋጅ ይህ መብት ካልተቋቋመ በስተቀር ተፈፃሚነት አይኖረውም።

3/ የዚህ አዋጅ አንቀጽ 74 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 ከነማሻሻያዎቹ በዚህ አዋጅ ተሽሯል።

4/ ማናቸውም ሕግ ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን እስከሆነ ድረስ በዚህ አዋጅ በተደነገጉ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

## 74. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

1/ የተሻረው አዋጅ ይህ አዋጅ ተፈፃሚ ከመሆኑ በፊት ስራ ላይ የቆዩ ነባር የሒሣብ ጊዜዎችን በሚመለከት ተፈፃሚነት ይኖረዋል።

2/ በዚህ አዋጅ "ነባር የሒሣብ ጊዜዎች" በሚል የተጠቀሰው አግባብነት እስካለው ድረስ በተሻረው አዋጅ የነበረውን የሒሣብ ጊዜ ይጨምራል።

3/ በተሻረው አዋጅ መሠረት የወጡ ደንቦችና መመሪያዎች ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረኑ እስካልሆነ እና በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ ደንብና መመሪያ እስከሚተኩ ድረስ ተፈፃሚነታቸው ይቀጥላል።

4/ ይህ አዋጅ ከመወጣቱ በፊት በተሰጠ የባንክ ፈቃድ አዋጁ ከፀናበት ቀን ጀምሮ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ወደአገር የሚገቡ ዕቃዎች በተሻረው አዋጅ መሠረት ይስተናገዳሉ።

5/ የገቢዎች ሚኒስቴር በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሰረት የተጨማሪ እሴት ታክስን የመሰብሰብ ውክልና አሰጣጥን እና የአፈፃፀም ሥርዓቱን እስከሚዘረጋ ድረስ ቀደም ሲል በተሻረው አዋጅ መሠረት ለክልል የታክስ ባለሥልጣናት የሰጠው ውክልና ተፈፃሚነት ይቀጥላል።

6/ የመኖሪያ ቤቶችን ገንብቶ በመሸጥ ስራ ላይ የተሰማራ እና ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት በግንባታ ላይ ላሉ የመኖሪያ ቤቶች በሚውሉ ግብአቶች ላይ የከፈለውን የግብአት ታክስ ያቀናነሰ የተመዘገበ ሰው የሚሸጠው የመኖሪያ ቤት ከታክሱ ነፃ እንዲሆን ለማድረግ የሚቻለው በእነዚህ የግንባታ ዕቃዎች ላይ ያቀናነሰውን የግብዓት ታክስ ለባለሥልጣኑ ተመላሽ ሲያደርግ ነው።

7/ በዚህ አዋጅ የተደነገገው ቢኖርም በቱሪስት አስጎብኚነት የንግድ ስራ ላይ የተሰማራ የተመዘገበ ሰው ይህ አዋጅ ከፀናበት ቀን አንስቶ ለሦስት ዓመታት ያህል የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚከፍለው በአገር ውስጥ ጥቅል የቱሪዝም አገልግሎት ለመስጠት ከተቀበለው ክፍያ ላይ ለመኝታ፤ ለምግብ እና ለትራንስፖርት የሚያወጣው ወጪ ተቀንሶ በሚቀረው ሂሳብ ወይም በሚከፈለው ኮሚሽን ላይ ይሆናል።

8/ በዚህ አንቀጽ "የተሻረው አዋጅ" ማለት የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 ከነማሻሻያዎቹ ነው።

የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት 2 ማ.ኒ.ስ.ቴ.ር

## 75. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

*አዲስ አበባ፣ ሰኔ 27 ቀን 2016 ዓ.ም*

*ሳህለወርቅ ዘውዴ*
*የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ*
*ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት*

## አባሪ አንድ

## (አንቀጽ 9)

## ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈፃሚ የሚሆንባቸው አቅርቦቶች

## ክፍል 1

## ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ ዕቃዎች

1. የሚከተሉት የዕቃ አቅርቦቶች ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈፃሚ ይደረግባቸዋል፡፡

   ሀ/ ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ አቅርቦቶች፣

   ለ/ ከኢትዮጵያ ውጪ በሚጓዝ አውሮፕላን፣ ተሽከርካሪ ወይም ባቡር ላይ የተጫኑ ከኢትዮጵያ ውጪ ለጥቅም ወይም ለፍጆታ የሚውሉ የጉዞ ዕቃዎች፣

   ሐ/ ለጥገና፣ ለዕድሳት፣ ለማሻሻያ ወይም ለማስተካከያ ተግባር በጉምሩክ አዋጅ መሠረት በጊዜያዊነት ወደአገር የሚገቡ ዕቃዎች፣ እነዚህ ዕቃዎች፡-

   i) በጊዜያዊነት ወደአገር በገቡ ዕቃዎች ላይ ሊገጠሙ፣ ከእነዚህ ዕቃዎች ጋር ሊያያዙ ወይም በማናቸውም መልክ የእነዚህ ዕቃዎች አንድ ክፍል የሚሆኑ እስከሆነ ድረስ፣ ወይም

   ii) ለጥገና፣ ለዕድሳት፣ ለማሻሻያ ወይም ለማስተካከያ ተግባር የዋሉ በመሆኑ ምክንያት ለሌላ አገልግሎት የማይውሉ ወይም ዋጋ የማይኖራቸው ከሆነ፡፡

2. ዕቃዎቹ ተመልሰው ወደኢትዮጵያ የገቡ ወይም የሚገቡ እስከሆነ ድረስ የዕቃ አቅርቦት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ) ወይም (ለ) መሠረት ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈፃሚ ሊደረግበት አይችልም፡፡
3. በጊዜያዊነት ወደአገር የገቡ ዕቃዎች ወደአገር የገቡት ከ12 ወራት በላይ ለሆነ የቆይታ ጊዜ ከሆነ የዕቃው አቅርቦት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1(ሐ) መሠረት ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈፃሚ ሊደረግለት አይችልም፡፡

የገንዘብ
የሪከርድ
አስተዳደር
አገልግሎት
2
ሚኒስቴር

## ክፍል 2

## ለውጭ አገር የሚቀርቡ አገልግሎቶች

1. ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ሲሟሉ ለውጭ አገር የሚቀርቡ አገልግሎቶች ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈፃሚ ይደረግባቸዋል፡፡

ሀ/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ የሚዘረዘሩ የሰነድ ማስረጃዎች አገልግሎቱ ጥቅም ላይ የሚውለው ከኢትዮጵያ ውጪ መሆኑን የሚያረጋግጡ ከሆነ፣

ለ/ አገልግሎቱ በተሰጠበት ጊዜ በቀጥታ የሚገናኘው ኢትዮጵያ ውጪ ከሚገኝ ዕቃ ጋር ሲሆን፣

ሐ/ በጊዜያዊነት ወደአገር የገቡት ዕቃዎች ከ6 ወራት በላይ በኢትዮጵያ ውስጥ የማይቆዩ እስከሆነ ድረስ አገልግሎቱ የተሰጠው በቀጥታ ከእነዚህ ዕቃዎች ጋር በተያያዘ ከሆነ፣

መ/ አገልግሎቱ የተሰጠው በኢትዮጵያ ነዋሪ ላልሆነ ያልተመዘገበ ሰው ከሆነ እና አገልግሎቱ በዚህ አባሪ አንቀጽ 1(ሀ) ወይም (ለ) የተዘረዘሩትን እቃዎች አቅርቦት ማመቻቸትን የሚመለከት ከሆነ፤

ሠ/ አገልግሎቱ በአካል የተሰጠው ከኢትዮጵያ ውጪ ከሆነ፤

ረ/ የትራንስፖርት ደጋፊ አገልግሎቶችን ሳይጨምር አገልግሎቱ የዓለም ዐቀፍ የትራንስፖርት አገልግሎት ከሆነ፣

ሰ/ አገልግሎቱ ሰዎችን በኢትዮጵያ ውስጥ ካለ ቦታ ወደ ኢትዮጵያ ውስጥ ወዳለ ሌላ ቦታ በአውሮፕላኖች ማጓጓዝ ሲሆን እና ይህም ትራንስፖርት በአለም አቀፍ የሲቪል አቪዬሽን ኮንቬንሽን አንቀጽ ፰ እንደተገለጸው "አለም አቀፍ ጉዞ" በሚለው የተሸፈነ ከሆነ፤

ሸ/ አገልግሎቱ በዚህ ንኡስ አንቀጽ (ረ) ተፈፃሚነት ባለው የአገልግሎት አቅርቦት አካል ሆኖ የሚቀርበው በአንድ አቅራቢ እስከሆነ ድረስ በኢትዮጵያ ውስጥ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ዕቃዎችን ማጓጓዝ ነው፤

ቀ/ አገልግሎቱ የዚህ አንቀጽ ተራ ፊደል (ሀ) ተፈፃሚ ለሚደረግባቸው አገልግሎቶች የሚውል የመድን አገልግሎት፣ የመድን አገልግሎትን ማመቻቸት ወይም መንገደኞችን እና ዕቃዎችን የማጓጓዝ አገልግሎት ከሆነ፣

በ/ አገልግሎቱ ረዳት የትራንስፖርት አገልግሎት ሆኖ ከኢትዮጵያ ውጭ ላሉ እና ኢትዮጵያ ውስጥ ቋሚ የንግድ አድራሻ ለሌላቸው ሰዎች የሚቀርብ ከሆነ፡፡

2. ለሚከተሉት አገልግሎቶች አቅርቦት በዚህ ክፍል 1(ሀ) መሠረት ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈፃሚ አይደረግም፡-

ሀ/ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚከናወን የቱሪዝም አገልግሎት ሲሆን፣

የገንዘብ ሚኒስቴር የታክስ አስተዳደር አገልግሎት 2

ለ/ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚከናወን የቱሪዝም አገልግሎት እንቅስቃሴን ማመቻቸትን የሚመለከቱ ሲሆን፣ እና

ሐ/ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝን የማይንቀሳቀስ ንብረት የሚመለከቱ ሲሆን።

3. ለዚህ ክፍል አንቀጽ 2(ለ) አፈፃፀም "በኢትዮጵያ ውስጥ የሚከናወን የቱሪዝም አገልግሎት እንቅስቃሴን ማመቻቸት" የሚባለው በኢትዮጵያ ውስጥ በጥቅል የሚሰጡ አንድ ወይም ከአንድ በላይ የቱሪዝም ውጤቶች ወይም አገልግሎቶችን እና ከኢትዮጵያ ውጪ ላለ ላልተመዘገበ ሰው መሸጥ ማለት ነው።

## ክፍል 3

## ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈፃሚ የሚደረግባቸው የአገር ውስጥ አቅርቦቶች

1. የሚከተሉት የአገር ውስጥ አቅርቦቶች ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈፃሚ ይደረግባቸዋል።

ሀ/ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ተሟልተው ሲገኙ አንድ የተመዘገበ ሰው በመንቀሳቀስ ላይ ያለውን ድርጅቱን ታክስ የሚከፈልበት የሥራ እንቅስቃሴ በሙሉ ወይም በከፊል በማስተላለፍ ሂደት የዕቃ ወይም የአገልግሎት አቅርቦት ሲያከናውን፣

(i) የንግድ ሥራው የተላለፈለት ሰው ታክስ የሚከፈልበትን የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ በቀጣይነት ማከናወን እንዲችል የሚያስፈልጉ ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች የተላለፈው የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ወይም የተላለፈው ከፊል የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ አካል ሆነው የተላለፉ ከሆነ፣

(ii) አስተላላፊው የማስተላለፉ ተግባር እስከተከናወነበት ቀን ድረስ ታክስ የሚከፈልበትን የሥራ እንቅስቃሴ ሲያከናውን የነበረ ከሆነ፣

(iii) የተላለፈለት ሰው ታክስ የሚከፈልበትን የሥራ እንቅስቃሴ ከታክስ ነፃ የሆነ አቅርቦቶችን ለማከናወን የሚጠቀምበት ካልሆነ ወይም ዕቃዎቹ እና አገልግሎቶቹ ለግል ጥቅም የማይውሉ ከሆነ፣

(iv) የተላለፈለት ሰው እና አስተላላፊው የማስተላለፉ ተግባር በተከናወነበት ዕለት ወይም ከዚህ ጊዜ በፊት የማስተላለፉ ተግባር ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም በመንቀሳቀስ ላይ ያለን ታክስ የሚከፈልበት የሥራ እንቅስቃሴን በሙሉ ወይም በከፊል የማስተላለፍ ተግባር ሆኖ እንደሚቆጠር በፅሑፍ የተስማሙ ከሆነ፣ እና

(v) አስተላላፊው የማስተላለፉ ተግባር በተከናወነ በ45 ቀን ጊዜ ውስጥ ወይም የታክሱ ባለስልጣን በሚፈቅደው ተጨማሪ ጊዜ ውስጥ የፀደቀውን ቅጽ በመጠቀም ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኘው ድርጅት የማስተላለፍ ተግባር ታክስ

የሚከፈልበትን የሥራ እንቅስቃሴ በሙሉ ወይም በከፊል ማስተላለፍ ተደርጐ ሊወሰድ እንደሚገባ ከገለፀ፣ እና

ለ/ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የሚቀርብ ወርቅ፡፡

2. ታክስ የሚከፈልበትን የንግድ እንቅስቃሴ በከፊል በማስተላለፍ ሂደት የተከናወነ የእቃ ወይም አገልግሎት አቅርቦት ላይ የዚህ አባሪ አንቀጽ 1(ሀ) ተፈፃሚ የሚሆነው የተላለፈው የንግድ እንቅስቃሴ ራሱን ችሎ ሊሰራ የሚችል ከሆነ ነው፡፡

3. በዕቃ ወይም አገልግሎት አቅርቦት ላይ የዚህ አባሪ አንቀጽ 1(ሀ) ተፈፃሚ ከሆነ እና አቅርቦቱ ከተከናወነ በኋላ ተቀባዩ የተላለፈለትን ዕቃ እና አገልግሎት ከታክስ ነፃ የሆኑ አቅርቦቶችን ለማቅረብ ያዋለ ወይም የተላለፉለትን ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ለግል ጥቅም ያዋለ እንደሆነ፣ የዚህ አባሪ አንቀጽ 1(ሀ) ተፈፃሚ የሆነባቸውን ዕቃዎች እና አገልግሎቶች በተመለከተ ተቀባዩ ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት እንዳከናወነ በመቁጠር፤

ሀ/ ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ታክስ የሚከፈልበት ግብይት በተከናወነበት ጊዜ ከታክሱ ነፃ ለሆነ አቅርቦት ወይም የተላለፈው ዕቃ ወይም አገልግሎት ለግል ጥቅም እንደዋለ ይቆጠራል፤ እና

ለ/ ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ዋጋ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 3(ሀ) በተገለፀው ጊዜ የዕቃዎቹ ወይም የአገልግሎቶቹ ትክክለኛ የገበያ ዋጋ ነው፡፡

## ክፍል 4

## አባሪ 1- ትርጓሜ

በዚህ አባሪ ውስጥ፡-

**"የትራንስፖርት ደጋፊ አገልግሎት"** ማለት ጭነት መጫንና ማውረድ፣ ጭነትን የመመርመር አገልግሎት፣ የጉምሩክ ሰነዶችን ማዘጋጀት፣ ኮንቴይነሮችን የማስተናገድ አገልግሎት፣ እና ለተጓጓዙ ዕቃዎች ወይም ለሚጓጓዙ ዕቃዎች የመጋዘን መስጠት ነው፡፡

**"መላኪያ አገር"** ማለት ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ የመላኪያ አገር ተብሎ እንዳይቆጠር ከሚወስነው አገር ወይም ግዛት በስተቀር ከኢትዮጵያ ውጪ ያለ ማናቸውም አገር ወይም ግዛት ነው፡፡

**"ዕቃዎችን ወደውጭ መላክ"** ማለት ዕቃዎችን ፡-

ሀ. የሚከተሉት ሁለት ሁኔታዎች በተሟሉበት ሁኔታ ማቅረብ ነው፦

i/ በጉምሩክ አዋጅ በተደነገገው መሠረት አቅራቢው ዕቃዎችን ወደውጭ አገር ለመላክ ሲያቀርብ፣ እና

ii/ የገቢዎች ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ በሚወስነው የሰነድ ማስረጃ ዕቃዎቹ መላኪያ አገር የደረሱ መሆኑ ሲረጋገጥ፣

ለ. ዕቃዎቹ አስቀድሞ ወደውጭ ገበያ ለመላክ ያልቀረቡ ቢሆንም የታክሱ ባለስልጣን እቃዎቹ ከኢትዮጵያ ውጪ የተላኩ መሆኑን ሲያምንበት፤

ሐ. የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፫ ንኡስ አንቀጽ (2) ተፈጻሚ የሚሆንባቸውን ዕቃዎች ሳይጨምር በጉምሩክ አዋጅ በተደነገገው መሰረት አቅርቦቱ በተከናወነበት ጊዜ እቃዎቹ በኢትዮጵያ ውስጥ የሌሉ ወይም አቅራቢው ለአገር ውስጥ ፍጆታ እቃዎቹን ወደኢትዮጵያ የማያስገባ ከሆነ፤

**“ዓለም ዐቀፍ የትራንስፖርት አገልግሎት”** ማለት በአየር፣ በየብስ ወይም በባቡር ዕቃዎችን ወይም መንገደኞችን፣

ሀ/ አስፈላጊ እስከሆነ ድረስ ከፊል የጉዞው መስመር የኢትዮጵያ የግዛት ክልል ማቋረጥን የሚጨምር ሆኖ፣ ከኢትዮጵያ ውጪ ከሚገኝ አንድ ቦታ ከኢትዮጵያ ውጪ ወደሚገኝ ሌላ ቦታ፣

ለ/ ከኢትዮጵያ ውጪ ከሚገኝ አንድ ቦታ የመጨረሻ መዳረሻው ወደሆነ በኢትዮጵያ ውስጥ ወደሚገኝ ቦታ፣ ወይም

ሐ/ የጉዞው መነሻ ከሆነው በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኝ አንድ ቦታ ከኢትዮጵያ ውጪ ወደሆነ ቦታ፣

ማጓጓዝ ነው፡፡

**“የጉዞ ዕቃዎች”** ማለት በጉምሩክ አዋጅ ምዕራፍ ስድስት የተመለከቱት ዕቃዎች ናቸው፡፡

**“በጊዜያዊነት ወደአገር የሚገቡ ዕቃዎች”** ማለት በጉምሩክ አዋጅ አንቀጽ 71 መሠረት በጊዜያዊነት ወደአገር የገቡ ዕቃዎች ናቸው፡፡

**“የቱሪዝም ውጤቶች ወይም አገልግሎቶች”** የሚለው ሐረግ መኝታን፣ የትራንስፖርትን፣ ጉዞን ወይም ሌሎች በኢትዮጵያ ውስጥ የሚካሄዱ የቱሪዝም እንቅስቃሴዎችን ይጨምራል፡፡

የገንዘብ ሚኒስቴር
የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት 2

## አባሪ ሁለት
## (አንቀጽ 10)

## ከታክስ ነፃ የሆኑ አቅርቦቶች

1. የሚከተሉት አቅርቦቶች ከታክሱ ነፃ ተደርገዋል፣

ሀ/ በመኖሪያ ቤትነት ለሁለት ዓመት እና ከዚያ በላይ ያገለገለ የመኖሪያ ቤት ሽያጭ

ለ/ ከሁለት ወራት በታች ለሆነ ጊዜ የተከራየን ሳይጨምር የመኖሪያ ቤት ኪራይ፣

ሐ/ ፈቃድ በተሰጠው ባንክ ወይም የፋይንናስ ተቋም ወይም በሌላ ማናቸውም ሰው የሚሰጥ የፋይናንስ አገልግሎት አቅርቦት፣

መ/ አቅራቢው የትምህርት ፕሮግራም ለሚከታተሉ ተማሪዎች የሚያቀርባቸውን ዋጋቸው ለፕሮግራሙ የሚከፈለው ዋጋ ውስጥ የተካተተ የመማሪያ መፃህፍት፣ ቁሳቁሶች ወይም መሣሪያዎችን ጨምሮ የትምህርት ፕሮግራሞች አቅርቦት፣

ሠ/ ፈቃድ በተሰጠው አገልግሎት ሰጪ የሚከናወን የህፃናት ማቆያ አገልግሎት፣

ረ/ የሕክምና አገልግሎት አቅርቦት፣

ሰ/ በሐኪም የሚታዘዙ መድኃኒቶች አቅርቦት፣

ሸ/ የብዙሐን ትራንስፖርት አገልግሎት አቅርቦት፣

ቀ/ ቅዱሳን መጻህፍትን ማቅረብን ጨምሮ በእምነት ተቋማት የሚሰጡ ከእምነቱ ወይም ከኃይማኖቱ ሥርዓት ጋር በቀጥታ የተያያዙ አገልግሎቶች

በ/ የሕክምና መገልገያ፣ የሕክምና መሣሪያ፣ የወባ አጐበር አቅርቦት፣

ተ/ ለትርፍ ባልተቋቋሙ ድርጅቶች የሚቀርቡ በእርዳታ የሚሰጡ ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች፣

ቸ/ ለግብርና አገልግሎት ብቻ የሚውል የምርጥ ዘር፣ ማዳበሪያ፣ የፀረ - ተባይ፣ የፀረ - አረም፣ የአፈርን አሲዳማነት ለመከላከል የሚውል ካልሲየም ሃይድሮክሳይድ (ውህድ ኖራ) ወይም የፈንገስ መከላከያ ኬሚካሎች፣

ኀ/ በሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ደንብ በተደነገገው መሠረት ኢንቨስተሮች ወደአገር የሚያስገቡት ወይም ከአገር ውስጥ የሚገዙት ዕቃ፣

ነ/ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ከሚወሰን ወርሃዊ ፍጆታ ያልበለጠ የኤሌክትሪክ ኃይል እና የታሸገ ወሃን ሳይጨምር የውሃ አቅርቦት፣

ኘ/ 60 በመቶና ከዚያ በላይ ሠራተኞቹ አካል ጉዳተኛ የሆነ ሰው የሚያቀርባቸው ማናቸውም አቅርቦቶች፣

አ/ ሚኒስቴሩ በሚያቀርበው ሃሳብ መሰረት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ከታክስ ነጻ የሚደረጉ እቃዎች፤

ከ/ አምቡላንስ እና የእሳት አደጋ ተሽከርካሪዎች እና መሣሪያዎች አቅርቦት፡፡

2. ለዚህ አባሪ አፈፃፀም፣

**"በእርዳታ የሚሰጡ ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች"** ማለት ለትርፍ ያልተቋቋሙ ድርጅቶችን በሚመለከት ለእነዚህ ድርጅቶች በስጦታ የሚቀርቡ ወይም በስጦታ በተገኘ የሚገዙ እና ድርጅቱ የተቋቋመበትን ዓላማ ለማስፈፀም የሚውሉ ዕቃዎች እና አገልግሎቶች፣

**"የትምህርት ፕሮግራም"** በሚከተሉት የሚሰጥ የትምህርት ፕሮግራም ነው፡-

ሀ/ አግባብ ባለው ክልል የትምህርት ቢሮ ፈቃድ የተሰጠው ቅድመ - አንደኛ ደረጃ፣ አንደኛ ደረጃ ወይም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣

ለ/ በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 152/2011 መሠረት በትምህርት ሚኒስቴር ዕውቅና የተሰጠው ዩኒቨርሲቲ፣ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ፣ ኮሌጅ ወይም ኢንስቲትዩት፣ ሆኖም የትምህርት ፕሮግራሙ ዲግሪ ወይም ተመሳሳይ የብቃት ማስረጃ የሚያስገኝ ከሆነ፣

ሐ/ በቴክኒክ እና ሙያ ትምህርት እና ሥልጠና አዋጅ ቁጥር 954/2008 መሠረት ዕውቅና የተሰጠው የሥልጠና ተቋም፣ ሆኖም የትምህርት ፕሮግራሙ በአዋጁ መሠረት ዕውቅና የተሰጠው የቴክኒክ ወይም የሙያ ሥልጠና ፕሮግራም ከሆነ፣

መ/ የልዩ ፍላጎት ትምህርት ተቋም፤

**"የፋይናንስ አገልግሎት"** ማለት፡-

ሀ/ በአበዳሪው የሚከናወንን ብድር፣ ክሬዲት ወይም የክሬዲት ዋስትናን ማስተዳደርን ጨምሮ ብድር መስጠት፣ መደራደር፣ ወይም በብድር፣ በክሬዲት፣ በክሬዲት ዋስትና ወይም ለገንዘብ በሚሰጥ ዋስትና መነገድ፣

ለ/ ዕዳ መሰብሰብን እና ተሰብሳቢ ሒሣብን መሸጥን ሳይጨምር ገንዘብ፣ ተቀማጭ ሒሣብን፤ ቁጠባን እና ሌሎች ተመሳሳይ ሂሳቦችን፣ ክፍያዎችን፣ የገንዘብ ማስተላለፍ ተግባራትን (የፋይናንስ ቴክኖሎጂ አገልግሎትን ሳይጨምር)፣ ዕዳን፣ ቼክን ወይም የሚተላለፉ የገንዘብ ሰነዶችን የሚመለከቱ ተግባራት፣

የሬቨኑ አስተዳደር አገልግሎት 2 ሚኒስቴር

ሐ/ የፋይናንስ ዴሪቬቲቭ ሀብትን የመግዛትና የመሸጥ ውሎች፣ የፋይናንስ ሀብትን ወደፊት በሚውል ቀን ለመግዛት ወይም ለመሸጥ የሚደረግ ስምምነት፣ የፋይናንስ ሰነዶችን ለመግዛት የሚኖር ምርጫን የመግዛትና የመሸጥ ውሎች እና ተመሳሳይ ተግባራትን፣

መ/ የአደራ አገልግሎት ሳይጨምር በአክሲዮን፣ ድርሻ፣ ቦንድ እና ሌሎች የግዴታ ምስክር ወረቀቶች መገበያየት እና ከእነዚህ ጋር የተያያዘ ማናቸውም ምርጫ ወይም ዋስትና፤

ሠ/ የኢንቨስትመንት ፈንድን ማስተዳደር፣

ረ/ የረዥም ጊዜ የመድን ውል መስጠት ወይም የባለቤትነት መብት ማስተላለፍ ወይም ለዚህ ዓይነቱ ውል የጠለፋ መድን መስጠት ወይም አነስተኛ የመድህን ውል መስጠት፣

ሰ/ የጡረታ ፈንድ፣ የፕሮቪደንት ፈንድን ወይም ሌላ ተመሳሳይ የጥቅም ፈንድ፤ የመድን ጡረታ ፈንድ፤ የጡረታ ሂሳብን ለማስጠበቅ የሚቋቋም ፈንድ ማቋቋም ወይም የባለቤትነት መብትን ማስተላለፍ፣

ሸ/ ለዕቃው በሚሰጠው ብድር ላይ የተለየ ክፍያ የሚጠየቅ እና ክፍያው ለዕቃው ተጠቃሚ የተገለፀ እስከሆነ ድረስ በኪራይ ግዥ ስምምነት ወይም በፋይናንስ ሊዝ መሠረት የሚከናወን አቅርቦት፣

ቀ/ ብር ወይም የውጭ ምንዛሪ የመግዛት ወይም የመሸጥ ውል፣

በ/ ከፊደል ተራ (ሀ) እስከ (ቀ) የተዘረዘሩትን አገልግሎቶች ማመቻቸት፣ ወይም

ተ/ በሚኒስቴሮች ምክር ቤት ደንብ በሚወሰነው መሠረት የእስልምና ባንክ አገልግሎት መስጠት፡፡

**"የእረፍት ጊዜ ወይም የሆቴል መስተንግዶ"** ማለት

ሀ/ በሆቴል፣ በሞቴል፣ በኢን፣ በመኝታ ቤቶች፣ በእንግዳ ማረፊያ፣ በሆስቴል ወይም በተመሳሳይ ሌላ ተቋም በተለምዶ በሚሰጥ መስተንግዶ ለበርካታ ሰዎች በቀን፣ በሣምንት፣ በወር ወይም በሌላ በተወሰነ የጊዜ ልዩነት በሚፈፀም ክፍያ አገልግሎት መስጠት፣ ወይም

ለ/ በዚህ የትርጉም ክፍል ፓራግራፍ (ሀ) ከተመለከተው የመስተንግዶ አቅርቦት ውጪ በግለሰቦች ለአጭር ጊዜ ለሚደረግ ቆይታ የሚሰጥ መስተንግዶ፣ ነው፡፡

**"የረዥም ጊዜ የመድን ስራ"** የሚለው ሐረግ በመድን ስራዎች አዋጅ ቁጥር 746/2004 (እንደተሻሻለ) የተሰጠው ትርጉም ይኖረዋል፡፡

**"የረዥም ጊዜ የመድን ስራ ውል"** ማለት የረዥም ጊዜ የመድን ስራ በማከናወን ሂደት የሚፈፀም የመድን ስራ ውል ነው፡፡

**"የሕክምና አገልግሎት"** ማለት በምግብ፣ መድኃኒትና የጤና እንክብካቤ አስተዳደር እና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 1112/2012 መሠረት ፈቃድ በተሰጠው የጤና ባለሙያ ወይም የሕክምና ባለሙያ በታወቀ የህክምና ተቋም ውስጥ የሚሰጥ የህክምና ሙያ አገልግሎት ነው፡፡

**"አነስተኛ መድህን ውል"** የሚለው ሐረግ በመድን ስራዎች አዋጅ ቁጥር 746/2012 (እንደተሻሻለ) የተሰጠው ትርጉም ይኖረዋል፡፡

**"ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት"** ማለት በፌደራል ገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 አንቀጽ 65(1) (ነ) አፈፃፀም ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት ሆኖ የሚቆጠር አካል ነው፡፡

**"በሐኪም የሚታዘዝ መድኃኒት"** ማለት በምግብና መድኃኒት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 1112/2011 መሠረት በሐኪም ትዕዛዝ ብቻ የሚወሰድ መድኃኒት ነው፡፡

**"የብዙሐን ትራንስፖርት አገልግሎት"** ማለት ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት በስተቀር ለመንገደኞች እና ለግል መገልገያ ዕቃዎቻቸው እንዲሁም ለጭነት ዕቃዎች በኢትዮጵያ ውስጥ በመንገድ፣ በባቡር ወይም በጀልባ በክፍያ የሚሰጥ የትራንስፖርት አገልግሎት ነው፡ ፡

ሀ/ ባለሦስት እግር ተሽከርካሪን ሳይጨምር፣ አሽከርካሪውን ጨምሮ ከስምንት ሰው በታች የመጫን ዐቅም ያለው ተሽከርካሪን በመጠቀም የሚሰጥ የትራንስፖርት አገልግሎት፣

ለ/ ከነሹፌሩ ቢሆንም ባይሆንም የሚሰጥ የተሽከርካሪ ኪራይ አገልግሎት፣ እና

ሐ/ ቱሪስቶችን ማጓጓዝ፡፡

**"የታወቀ የህክምና ተቋም "** ማለት በደንቡ የተመለከተው የህክምና ተቋም ነው፡፡

**"የህክምና ሙያ አገልግሎት"** ማለት በደንቡ የተመለከተው የህክምና አገልግሎት ነው፡፡

**"የመኖሪያ ቤት"** ማለት ሆቴልን ወይም የእረፍት ጊዜ መኖሪያን ሳይጨምር ለግል መኖሪያነት በማገልገል ላይ የሚገኝ ወይም የሚያገለግል የማይንቀሳቀስ ንብረት ነው፡፡

**"ሽያጭ"** ማለት ከመኖሪያ ሕንፃዎች ጋር በተያያዘ የረጅም ጊዜ የሊዝ ውል መስጠትን ወይም ማስተላለፍን ያጠቃልላል፡፡

የገቢ * የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት 2 * ሚኒስቴር

## አባሪ ሦስት
## (አንቀጽ 11)

## ከታክስ ነፃ የሆኑ ወደአገር የሚገቡ ዕቃዎች

ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ወደአገር የሚገቡ ዕቃዎች ከታክሱ ነፃ ተደርገዋል፡፡

ሀ. በቪዬና የዲፕሎማቲክ ግንኙነት ኮንቬንሽን ሚሲዮኖች፣ ዲፕሎማቶች ወይም የኩንሱላር ጽ/ቤቶች ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነፃ እስከሆኑ ድረስ እነዚህ ሚሲዮኖች፣ ዲፕሎማቶች ወይም የኩንሱላር ጽ/ቤቶች ወደ አገር የሚያስገቡዋቸው ዕቃዎች፣

ለ. በዓለም ዐቀፍ ስምምነት ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነፃ የተደረጉ ዓለም ዐቀፍ ድርጅቶች ወደአገር የሚያስገቧቸው ዕቃዎች፣

ሐ. በፋይናንስ፣ በቴክኒክ፣ በሰብዓዊ ዕርዳታ ወይም በአስተዳደር ድጋፍ የዓለም ዐቀፍ ስምምነት ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነፃ እስከተደረገ ድረስ የውጭ አገር መንግሥት ወደአገር የሚያስገባቸው ዕቃዎች፣

መ. በጉምሩክ ደንብ ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ እስከተደረገ ድረስ መንገደኛው ይዞት የሚመጣ የግል መገልገያ ዕቃ፣

ሠ. ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ከሚወስነው እስካልበለጠ ድረስ ተመላሾች ወደ አገር የሚያስገቧቸው ዕቃዎች፣

ረ. ወደአገር የሚገባ ለግብርና ሥራ ብቻ የሚውል ምርጥ ዘር፣ ማዳበሪያ፣ የተባይ ማጥፊያ፣ የአረም ማጥፊያ ወይም የፈንገስ ማጥፊያ፣

ሰ. ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የሚቀርብ ወደ አገር የሚገባ ወርቅ፣

ሸ. የውሃ ማከሚያ፤ አጉበር፣ የሕክምና መገልገያ፣ እና የሕክምና መሣሪያ፣

ቀ. በአባሪ 2 ትርጉም የተሰጠው ወደአገር የሚገባ በሐኪም የሚታዘዝ መድኃኒት፣

በ. በሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ደንብ ቁጥር 517/2014 በተደነገገው መሠረት ኢንቨስተሮች ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆነው ወደአገር የሚያስገቡት ዕቃ፤

ተ. ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ሆነው ወደ አገር እንዲገቡ የተፈቀዱ የካፒታል ዕቃዎች፣

ቸ. በጉምሩክ ታሪፍ ደንብ ከጉምሩክ ቀረጥና ከማናቸውም ታክስ ነፃ የሆኑ ያልተመደቡ ወደ አገር የሚገቡ ዕቃዎች፣ እና

ኀ. አምቡላንስ እና የእሳት አደጋ ተሽከርካሪዎችና መሣሪያዎች ወደ አገር ማስገባት፤

ነ. ሚኒስቴሩ በሚያቀርበው ሃሳብ መሰረት በጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት ከታክስ ነጻ የሚደረጉ እቃዎች፤


የገንዘብ
የሪከርድ
አስተዳደር
አገልግሎት
2
ሚኒስቴር